አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የጠልሰም ባህላዊ ዕውቀትና መድኃኒትነት በፃታ ወረዳ

በ

ፍሬህይወት ወንድሙ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

**2014** ዓ.ም.

# የጠልሰም ባህላዊ ዕውቀትና መድኃኒትነት በፃታ ወረዳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ

ፍሬህይወት ወንድሙ

አማካሪ

ዓለሙ ካሳዬ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

**2014 ዓ.ም**

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የዐማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የጠልሰም ባህላዊ ዕውቀትና መድኃኒትነት በየጻታ ወረዳ

ፍሬህይወት ወንድሙ

**2014** ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ ስም | ፊርማ |
| ---------------------- | --------------------- |
| ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| ---------------------- | ----------------------- |

----------------------- -----------------------

# ምሥጋና

የምስጋና ዕዝነ ህሊናየ የሚጀመረው በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ የተሰራ የጥናት ጽሁፍ ነውና በሁሉ የሚቀድም ለሁሉ የሚራራ ቸር የሆነ ትላንትን በርህራሄ ጠብቆ ዛሬን በቸርነቱ አሻግሮ ነገን በተስፋ ለሚሞላ ልዑል እግዚያብሔር ምስጋና ሁሉ ለሱ ይሁን ። በምልጃ በበረከቱ ሁሌም የማትለየኝ አዛኝቶ እሙብርሀን እሙብዙሃን ምስጉን የተመሰገነች ትሁን።

በመቀጠል ከውድ ግዚያቸው ላይ ሰፊውን ስዓት በመስጠት አንዳንዴ በሚያስገርመኝ ፍጥነት ጽሁፌን ሲያርሙ ሲያቃኑ አቅጣጫ ሲያኖሩ የነበሩት ከመጀመሪያ ዲግሪየ ጀምሮ አስተማሪየ የነበሩት በቀጠልኩት ሁለተኛ ዲግሪየ ወቅትም ከአስተማሪነታቸው በተጨማሪ አማካሪየ ሆነው የረዱኝ ዶ/ር አለሙ ካሳየ ምስጋናየን መግለጫ ባጣ እንጅ አመሰግናለሁ ብየ ማቆሜ መሰሰቴ አይደለም ክብረት ይሥጥልኝ እላለሁ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የነፃ ትምህርት ዕድል ሰቶኝ ለዚህ ስላበቃኝ አመሰግናለሁ።

መረጃ አቀባዮቼ መምህር አይመረ ፀሀይ፣ መምህር አፈወርቅ ነጋሽ፣ መሪጌታ ደሳለኝ ገ/ሚካኤል፣ ቄስ ኪሮስ አሰፋውና ንዑሳን መረጃ ሰጭዎች ለዚህ ጥናት ዕውን መሆን ቀና ትብብራችሁ ዋጋው ትልቅ ነውና አመሰግናለሁ።

መምህሬ ዶ/ር መሀመድ አሊ ስታበረታታኝና በብዙ እንድተጋ ምክርህ አልተለየኝም ነበር ምስጋናየ ይድረስህ። ጓደኛየ እህቴ ኤልሳቤጥ ሽመልስ በሁሉም ድካምና ጥንካሬየ ውስጥ በሚደንቅ ቅንነትና ትብብር በብዙ መንገድ ከኔ ጋር ነበርሽ ምስጋናየ ይድረስሽ። እንዲሁም ከመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ድረስ ብዙ የረዳሽኝ ጓደኛየ አንተነህ ጌታቸው(ሳውላ) እጅጉን አመሰግናለሁ።

ባለመቻሌም በመቻሌም ውስጥ ሁሌም ኩራትና ዕምነት በኔ ላላችሁ ያላችሁን ብቻ ሳይሆን ከሌላቸሁ ላይም ለመስጠት ሁሌም ለደከማችሁ ደግ ወላጆቼ አባቴ ወንድሙ ቸኮለ (እምባዬ) እናቴ ጠጄ ቢምረው (ጣጀዋ) ዕድሜ ከጤና ጋር ያድልልኝ።

ወንድምና እህቶቼ ደሱ፣ ሲሳይ፣ አብርሽ፣ ሃይማኖት፣ ቅድስት፣ ሁላችሁም ለዚህ ስራ እዚህ መድረስ ብዙ አስተዋጾ አበርክታችኃልና አመሰግናለሁ።

ውድ ባለቤቴ ሔኖክ በኔ የሚሰማህ ጥንካሬ እስኪገርመኝ ድረስ አጠንክሮኝ እዚህ አድርሶኛል። ያለሁበትንና የደረስኩበትን ሳይሆን ያላየሁት ወደ ፊት የሚመጡ ትልልቅ ነገሮች የሚገባኝ ሰው እንደሆንኩ እንዲሰማኝ የምትነግረኝ ሁሉ ሀይሌ ነበርና አመሰግናለሁ።

## ማውጫ

ይዘት ገጽ i


**አጠቃሎ...........................................................................................................iv**

**ምዕራፍ አንድ......................................................................................................1**

1.1 የጥናቱ ዳራ.........................................................................................................1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.......................................................................................3

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች.................................................................................................4

1.3.1. የጥናቱ ዓብይ ዓላማ.........................................................................................4

1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች....................................................................................4

1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች................................................................................5

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ.......5
1.6. የጥናቱ ወሰን.......5
1.7. የጥናቱ ዘዴ.......6
1.7.1. ምልከታ.......6
1.7.2. ቃለ መጠይቅ.......8
1.7.3. የሰነድ ማስረጃዎች.......9
1.7.4. መረጃ መሰነጃ መንገድ.......9
1.7.5. የናሙና መረጣ ዘዴ.......10
1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው.......10
**ምዕራፍ ሁለት.......11**
2.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝት.......11
2.1.1. የጠልሰም ምንነት.......11
2.1.2. የጠልሰም አጀማመር.......13
2.1.3. ቃላዊነትና ሃይል (አስማት).......17
2.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ.......18
2.2.1. ተግባራዊ ወይም ጠቀሜታዊ ንድፈ ሐሳብ.......18
2.2.2. ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሐሳብ.......21
2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.......24
**ምዕራፍ ሶስት.......33**
3.1 የፃታ ወረዳ አካባቢያዊ ስያሜ እና የህዝብ አሰፋፈር.......33
3.2. የፃታ ወረዳ መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የኢኮኖሚ ሁኔታ.......34
3.3 የፃታ ወረዳ ማህበረሰብ ቋንቋና ሀይማኖት.......34
3.4 የቱሪዝም ሀብቶች በፃታ.......35
3.4.1 ታሪካዊ መስህቦች.......35
3.4.2 መንፈሳዊ መስህቦች.......37
3.4.3. ማህበራዊ መስህብ.......39
3.4.4 ባህላዊ መስህቦች.......40
**ምዕራፍ አራት.......44**
4.1 የጠልሰም ግብዓቶችና የሚገኙበት ሥርዓት.......44

4.2 የጠልሰም ዓይነቶች........................................................................................................49
4.3. የጠልሰም ስዕል የመሳል ማዕከላዊ እሳቤ..............................................................................50
4.4. በሽታን የመለያ ዘዴ..........................................................................................................51
4.5. የጠልሰም መድሃኒትነት......................................................................................................53
4.5.1. ሾተላይ.....................................................................................................................53
4.5.2 ለዓይነ ጥላ ወይም ለገርጋሪ መንፈስ...............................................................................58
4.5.3 ለደመ ከቲር.................................................................................................................65
4.5.4. ለመግረሬ ጸር ወይም መድፍነ ጸር..................................................................................67
4.5.5. ለዛር መለመኛ፣ ማውገዣ እና ማስታረቂያ.........................................................................70
4.5.6. ለማዕሰረ አጋንንት.....................................................................................................73
4.5.7 ለመፍትሔ ስራይ.........................................................................................................76
4.6. የፃታ ወረዳ ጠልሰም ከሌሎቹ አካባቢዎች የሚለይበት መልክ....................................................79
4.7 የማህበረሰቡ አመለካከት......................................................................................................80
4.8. የጠልሰም ዕውቀት ተስተላልፎ በፃታ ወረዳ.............................................................................81
**ምዕራፍ አምስት.........................................................................................................83**
ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------------------------------------ 82
**ዋቢ ጽሑፎች.............................................................................................................85**

የሰንጠረዥ እና የፎቶግራፍ ማውጫ

ይዘት ገፅ

**አባሪዎች.................................................................................................................89**
**አባሪ አንድ፡- የቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረጃ.......................................................................89**
**አባሪ ሁለት፡- መድኃኒቱን የተጠቀሙ ህመምተኞች መረጃ.....................................................89**

አባሪ ሶስት፡- የፃታ ወረዳን የሚመለከቱ መረጃዎችን የሰጡ የቢሮ ኃላፊዎችና የቀየው ነዋሪዎች መረጃ......**91**

አባሪ አራት፡- ለቁልፍ መረጃ ሰጪዎች (ለጠልሳሚዎችና አዋቂዎች) የቀረበ የመስክ ምልከታ..................**92**

አባሪ አምስት፡- ለሕመምተኞች (ለጠልሰም መድኃኒት ተጠቃሚዎች) የቀረበ ጥያቄ ቅጽ......................**93**

አባሪ ስድስት፡- የፎቶ ማስረጃዎች.........................................................................................**94**

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት "የጠልሰም ባህላዊ ዕውቀትና መድኃኒትነት በጻታ ወረዳ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የአካባቢውን ማህበረሰብ ባሕላዊ የህክምና እውቀት መመርመር ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የጠልሰምን ባህላዊ እውቀት እና መድህኒትነት ማሳየት ሲሆን የጠልሰም መስሪያ ግብዓቶችና አዘገጃጀቱን ማብራራት፤ የጠልሰም ዓይነቶችን ለይቶ ማሳየት፤ በጠልሰም ላይ የሚሳሉ መንፈሳዊ ሥዕሎች ለመድኃኒትነቱ ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት፤ ለጠልሰም መስሪያ የሚሆን ቆዳ መረጣ ሥርዓት ክዋኔን ማብራራት፤ የሕመም መለያ መንገዶችን መጠቆም፤ ማህበረሰቡ ስለ እውቀቱ ያለውን አመለካከት መመርመር እና መድኃኒት አዘጋጆቹን ወይም ጠልሳሚያኑ እውቀቱን ያገኙበትን ተስተላልፏዊ ሂደት መመርመር ደግሞ የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች ናቸው። እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን በእነዚህ መንገዶች የተሰበሰበው መረጃም በፎቶ፣ በማስታወሻ መያዣ፣ በምስልና ድምጽ መቅረጫ መሳርያ እንዲሁም በመቅረጸ ድምጽ መሳሪያ ተሰብስበው ተሰንደዋል። የመስክ መረጃ ሰጪዎች ዓላማ ተኮር የመረጣ ዘዴን መሰረት በማድረግ የተመረጡ ሲሆን ከጠልሰም መድኃኒት ጠልሳሚያን፤ በጠልሰም መድኃኒት ሕክምና አግኝተው ከተፈወሱ የመድኃኒቱ ተጠቃሚ ሰዎችና በመንደሩ አዋቂ ከሆኑ ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች እንዲሁም ከቁልፍና አጋዥ የመረጃ ሰጪ አካላት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተግባራዊና ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ በገላጭና ተንታኝ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል። ጥናቱ በተመረጠው ፃታ ወረዳ ውስጥ ይህ የጠልሰም እውቀት በስፋት ተተግባሪ የሚደረግባቸውን "ዳምትኩነ" እና "አርመር" የተባሉ ሁለት ቀበሌዎች በናሙናነት የመረጠ ሲሆን በእነዚህ ቀበሌዎች በተደጋጋሚ የሚስተዋሉት ሕመሞችም ሾተላይ፣ ዓይነ ጥላ (ሕጻናትን ገዳይ በሽታ)፣ ገርጋሪ፣ ደም መፍሰስ፣ ማዕሰረ አጋንንት፣ መግረሬ ጸር፣ ዛር መለመኛ ማውገዣና ማስታረቂያ፣ መፍትሔ ስራይ እና መድፍነ ጸር መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። ለእነዚህ ሕመሞች በቁመት ልክ ከሚሰራ ቁም ክታብ፣ በወገብ እና በግንባር ከሚታሰር ጠልሰም በአንዱ መድኃኒቱ እንደሚሰጥና መድኃኒት ከመስጠት በፊትም ዓይን በማየት አሊያም ዓውደነገስት ገልጦ ኮከብ በማንበብ ሕመም የመለየት ተግባር እንደሚከወን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል። እነዚህ ሕመሞች የየራሳቸው የሆነ ጸሎት ያላቸውና እኩይ መንፈስ ማራቂያ አስማት ያሉበት እንደሆነም በጥናቱ ተስተውሏል። መናፍሰቱን ግዘፍ አስነስቶ ሥዕላቸውን በመሳል ሕመምተኛው መናፍስቱን እንዳይፈራ የሚያደርግ ሥነ ልቡናዊ ሕክምና እንደሚታከልበት ጥናቱ አረጋግጧል። ይህ እውቀት በቃል እና በጽሑፍ ሲተላለፍ የመጣ ቢሆንም አልፎ አልፎ ጥበቡን እኩይ ለሆኑ ተግባራት የሚጠቀሙ ጠልሳሚዎች በመኖራቸው ማህበረሰቡ በተወሰነ ሁኔታ ጥበቡን የመፍራት ጠልሳሚያንንም የመሸሽ ሁኔታ በመኖሩ ዕውቀቱ ለሀገር እና ለማህበረሰብ የሚጠቅመውን ያህል ማደግ አለመቻሉን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል። ሆኖም ይህ ጥበብ እኩይ የማሕበረሰቡን ሕመም ከመፈወስ፤ ከመናፍስት ጋር የተያያዙ ሕመሞችን ከመፈወስ አንጻር ሀገራችን ያላትን ጥበባዊ ዕውቀት የማሳየት ድርሻው የጎላ በመሆኑ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጀምሮ የሚመለከታቸው አካላት እውቀቱን በማጎልበትና በማስተዋወቅ የራሳቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል።

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዕውቀት በፎክሎር የጥናት ዘርፍ ከሚዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ ዘርፍ በርካታ ሀገር በቀል የሆኑ ዕውቀቶችን ከጥበባዊ ትግበራቸው እስከ ተስተላልፏቸው ብሎም ለውጣቸው ጭምር ሲያጠና የቆየና አሁንም እያጠና ያለ ዘርፍ ነው። ይህ የምርምር ዘርፍ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገር በቀል እውቀቶችና ባህልን ከልማድ ጋር በማቆራኘት ዘመናትን መዝለቅ ለቻሉ ሀገራት አይነተኛ የባህል፣ ወግና ልማድ መመርመሪያ ዘርፍ ነው።

በዚህ የምርምር ዘርፍ ውስጥ የሚካሔዱ ጥናትና ምርምሮች በሥራቸው በሚያቅፏቸው ከጊዜ ወደጊዜ እያደጉና እራሳቸውን እያዳበሩ በሚሄዱ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች መነሻነት ይካሔዳሉ። በዚህ የዕውቀት ዘርፍ ውስጥ ከሚጠኑ እሳቤዎች መካከል ሀገር በቀል የሆነ ባህላዊ ህክምና አንዱ ነው። ይህ የህክምና አይነት ከዘመናዊ ህክምና ቀድሞ የመጣ ዕውቀት ነው (Andrae, 2017)። ባሕላዊ ህክምና ደግሞ በርካታና ዓይነቱም ብዙ ነው። ከነዚህ መካከል መንፈሳዊ ለሆኑ ሕመሞች የሚደረግ ህክምና አንዱ ነው።

በሀገራችን ከባህላዊ ህክምና ጋር ተያይዘው ከሚሰሩ ጥበባዊ የህክምና ዕውቀቶች አንዱ ጠልሰም ይገኝበታል። ጠልሰም ከረቂቅ መንፈሳዊ ኃይል እንዲሁም ቁሳዊ ጉዳዮች ጋር የሚዛመድ ዳራ አለው። በመሆኑም በዚህ ጥናት የረቂቅ ባህላዊ ዕውቀት ትግበራን በቁስ አካል ላይ በመጫን መንፈሳዊ ኃይልን የማላበስ ዕውቀታዊ ትግበራ ይታያል።

ይህ ጥናት በቁሳዊ ባህልና በሀገረሰባዊ ልማድ አበይት ርዕሰ ስር ሊካተት የሚችል ርዕሰ ጉዳይን የያዘ ነው። ቁሳዊ ባህል ሰዎች ተጨባጭ የሆኑ መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የጥበብ ጥማቸውን ለማርካት የሚሰሯቸውም ሆኑ የሚከልሏቸው በአይን የሚታዩ በእጅ የሚዳሰሱ ቁሶችን የሚያካትት ዘርፍ ነው። የጠልሰም ትውፊታዊ ዕውቀት ከቁሳዊነት ባሻገር መንፈሳዊና ረቂቅ የዕውቀት ዘርፍም ይታከልበታል። ይህም ባህላዊ ዕውቀት የፎክሎር ዘውጎች እያንዳንዳቸው ያላቸውን ጥብቅ ግንኙነት የሚያሳይ ነው። በመሆኑም የአጠናን ሂደቱም ቁሳዊነትን ከመንፈሳዊ እሴት ጋር አስተሳስሮ የሚመረምር ይሆናል።

ጠልሰም በባህላዊና እምነታዊ ትግበራ በአስማታዊ ጥበብ ታግዞ አንድ መንፈሳዊ ኃይልን፤ ስልጣንና የተለየ ብቃትን ቁሱን ለያዘው ሰው ያጎናጽፋል ወይም ያላብሳል። ይህ ባህላዊና እምነታዊ እውቀት በበርካታ የጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤት በሆኑ የዓለማችን ክፍሎች የሚታወቅና የሚተገበር እውቀት ነው ። ይታወቃል ይተገበራል።

ጠልሰም ባህላዊ እውቀቱን በቁስ በመግለጽ ረቂቅ የእምነት እሴትን በተጨባጭ የመግለጥ ዕውቀት ከአራቱ የፎክሎር ዘውጎች በአንዱ የሚካተት እውቀት በመሆኑ በይናዊነትና ፎክሎራዊ ተወራራሽነትን ያጣመረ ርዕሰ ጉዳይ በመሆኑ የጥናቱ እሳቤ ልዩ ትኩረትን የሚሻና መሰረታዊ የምርምር ጥያቄን የሚጠይቅ ይሆናል። ይህም ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ ቁሳዊ ባህል ከአራቱ ሰበዞች አንዱ ነው። በተጨማሪም የጠልሰም ባህላዊ ዕውቅት መንፈሳዊ ይዘትን አዛንቆ በመያዙ በህገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ይካተታል።

በዚህ ብቻ ሳይወስን መንፈሳዊ መድኃኒትና ባህላዊ ፈውስን ያካተተ ገጽታም አለው። ይህም ረቂቅ ፎክሎራዊ ዕውቀትን ገላጭ ሆኖ እናገኘዋለን። የአቀራረቡ ባህላዊ ዕውቀት በአብዛኛው ምስጢራዊነትን የተከተለ እንዲሁም እደጥበባዊ ዕውቀትን የያዘ ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው እይታ ሌላኛው የትውፊታዊ ዕውቀቱ መገለጫና ልዩ ባህሪ ነው።

የጠልሰም መኃኒትነት በፃታ ወረዳ በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ ጥናት ጠልሰም ባህላዊና ልማዳዊ ከመሆኑም በላይ ምስጢራዊና መንፈሳዊ ጥበባት የተሞሉበት እውቀት መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ ዕውቀት በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች ጥንታዊ ልማድና ወጉን ጠብቆ የሚተገበር ቢሆንም በአንዳንድ አሉታዊ አመለካከቶች ሳቢያ ትኩረት የተነፈገው ዕውቀት መሆኑን ማስተዋል ይቻላል። ጠልሰም በእስልምናውም በክርስትናውም እምነት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ ሀገራትም የሚገኝ ጥበብ መሆኑን የተለያዩ የውጭ ሀገራት ጥናቶችን በመቃኘት ማስተዋል ተችሏል። ትኩረታቸውን ጠልሰም ላይ አድርገው የተሰሩ የምርምር ስራዎች የጥበቡን ምስጢራዊነት፣ ጥበባዊነት ብሎም ከመንፈሳዊ እምነት ጋር የተያያዘ መድኃኒትነት እንዳለው ያመለክታሉ። ከዚህ ባለፈም ባደረኳቸው ቅኝቶች የዚህን ጥበብ ስእላዊ እሳቤ ከአስማታዊ ኃይሉ በመነጠል ዘመናው በሆነ መንገድ በመሳል በተለያዩ የሥዕል ዓውደርዕዮች ላይ የማሳየት ሁኔታ ቢስተዋልም አስማታዊ ኃይሉን በመጠቀም ለመድኃኒትነት የመዋል ጥበቡ እየተዘነጋና እንደ ዕውቀቱ ረቂቅነት ያላደገ ጥበብ መሆኑን ማስተዋል ችያለሁ።

ጠልሰምን ጉዳይ አድርገው የተካሔዱ የምርምር ሥራዎች ሰፊውን የጠልሰም ጥበብ በአንድ ውስን ቦታ ነጥሎ ከማጥናት ይልቅ በአንድ ሃገር ደረጃ የሚገኘውን ጥበባዊነቱን በተወሰኑ ቁንጽል ገጾች ለመመርመር የሞከሩ፤ ከክዋኔው ይልቅ በሚጠለሰሙት አስማቶች ቋንቋ ላይ ያተኮሩና የስዕላቱን ረቂቅነትና ውበት በማድነቅና ምስጢራዊነታቸውን በመንገር ላይ ያተኮሩ ሆነው አግኝቻቸዋለው። ስለሆነም እነዚህ ቀዳሚ ጥናቶች አንድም የኢትዮጵያን የጠልሰም ጥበብ በትኩረት ያልቃኙ፤ አንድም መድኃኒትነቱን ከአሰራርና አሰጣጥ ብሎም የአጠለሳሰም ሂደት አንጻር ያልዳሰሱና ማህበረሰቡ ለዚህ ጥበብ የሚሰተውን ሥፍራ እና አመለካከት ያልቃኙ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። ስለሆነም ይህንን ክፍተት መነሻ በማድረግ ይህ ጥበብ በተለየ መልኩ ይተገበርበታል ተብሎ የታመነበትን ሥፍራ በመምረጥ ከአዘገጃጀቱ እስከ አሰጣጥ እና አመራረጥ ክዋኔው ብሎም የህመም መለያውና የማህበረሰቡን አመለካከት ጭምር በማካተት ይህ ጥናት ተካሂዷል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የመጀመሪያ ዲግሪ መመረቂያ ጥናታዊ ጽሁፍ በማዘጋጅበት ወቅት ሀገር በቀል መድሃኒቶችን የሚመለከቱ ጥናቶቸ ለማየት ችያለሁ። በዚሁ አጋጣሚ ጠልሰም ምን እንደሆነ እና በመድሃኒትነቱ አንድ ጎን ብቻ ልዩ ገጽታ እንዳለው አንድ መጽሐፍ ላይ መረጃ አገኘሁ ነገር ግን በወቅቱ የጥናት ትኩረቴ በቀጥታ ጠልሰምን የሚመለከት ስላልነበር ዕውቀቱ እንዳለ ብቻ የማወቅ ዕድል ሰጥቶኝ አለፈ። በቀደመው የጥናት ስራዬ ሀገር በቀል መድኃኒትና ፈውስን የዳሰሰኩ ቢሆንም ከግዜያት በኋላ ባደረኩት ፍለጋ የጠልሰም ሙያዊና ጥበባዊ ገጽታ ከመድሃኒትነቱ እንዲሁም ከሀገር በቀል እውቀትነቱ አንጻር ምንም አይነት ጥናት አለመካሄዱን ለማስተዋል ቻልኩ። በመሆኑም ጠልሰምን እንደ አንድ ራሱን የቻለ የምርምር ርዕሰ ጉዳይ ማድረግ እንደሚቻል ተገነዘብኩ። በዚህም መነሻ ሀሳብ ጥናቱን እንዳካሂድ ምክንያት ሆነኘ።

ከዚህ በተጨማሪ በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ከሚሰጡ ትምህርቶች አንዱ በሆነው "Research Method for Literary Study- ELFO" በተሰኘ ትምህርት ላይ አጭር የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ያደረኩት በዚሁ ጠልሰም ጥናት ላይ ቢሆንም የጥናት ርዕሱ ብዙ ምርምሮች ያልተካሄደበት መሆኑን አስተዋልኩ። በተለይም በውስጡ ያለውን ፎክሎራዊ እይታ ያየ ጥናት አለማግኘቴና የነበረውን የጥናት ክፍተት መመልከቴ የዘርፉን አስፈላጊነት ለመገንዘብ ከነበረኝ የቀደመ መነሻ ሀሳብ የበለጠ እንዳውቅ ስላረገኝ ጥናቱን ለመሰራት ይበልጥ ተጨማሪ አነሳሽ ምክንያት ሆኖኛል። ይህ ባህላዊ ዕውቀት በመጥፋት ላይ የሚገኝና ሊጠፋ ያለ ከመሆኑ አንጻር ሰንዶ ለማስቀመጥ ካለኝ ጥብቅ ፍላጎት የተነሳም ነው። በተለይም ይህን ቋስ ከረቂቅ መንፈሳዊ ጉዳይ ጋር አስተሳስሮ የያዘ ዕውቀት ማጥናት አዎንታዊ ረቡ ከፍ ያለ ነው። ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በርካታ ባህላዊ ዕውቀቶችን እየቀደመ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ማህበረሰቡ በዘመናት ያዳበረው ዕውቀት ከትግበራ ውጭ እየሆነ ይገኛል። በመሆኑም ቴክኖሎጂና ዘመናዊነት የአቀራረቡን ፈርጅ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ ከማጥፋቱ በፊት መሰነዱ ተገቢ መሆኑ ሌላኛው አነሳሽ ምክንያት ሆኖኛል።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት አበይትና ንዑሳን ዓላማዎች አሉት። እነዚህም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 1.3.1. የጥናቱ ዓብይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በፃታ ወረዳ አካባቢ የሚገኘውን የጠልሰም ዕውቀትና መድኃኒትነት ማሳየት ነው። ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችም አሉት።

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- ✓ የጠልሰም ዓይነቶችን ለይቶ ማሳየት
- ✓ ጠልሰምን ለማዘጋጀት የሚውሉ ግብዓቶችን እና አዘገጃጀት ማሳየት
- ✓ የጠልሰም ማዘጋጃ ግብዓቶችን ለመለየት የተመረጡ ቀናትንና የአመራረጥ ሥርዓት ክዋኔን መግለጽ
- ✓ መናፍስታዊ የጠልሰም ሥዕላትን የመሳል እሳቤ ፋይዳን መግለጽ
- ✓ ማህበረሰቡ ለጠልሰም እውቀት ያለውን አመለካከት እና ጠልሳሚያን እውቀቱን ያገኙበትን መንገድ መግለጽ የሚሉት ናቸው።

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በዋናነት በፃታ ወረዳ አካባቢ የሚገኘው የጠልሰም ዕውቀትና መድኃኒትነት እንደምን ያለ ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ሲሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎችም በንዑስነት ይመለስሳል።

- የጠልሰም ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
- ጠልሰምን ለማዘጋጀት የሚውሉ ግብዓቶች ምን ምን ናቸው? አዘገጃጀቱስ?
- ጠልሰምን ለማዘጋጀት የሚውሉ ግብዓቶችን ለመለየት የሚመረጡ ቀናት የትኞቹ ናቸው? የአመራረጥ ሥርዓቱስ እንደምን ያለ ነው?
- ጠልሰም ላይ የሚሳሉ የመናፍስት ሥዕሎች ለመድኃኒቱ ምን ፋይዳ አላቸው?
- የጠልሰም ልማዳዊ ዕውቀት በምን መንገድ ይተላለፋል?
- ማህበረሰቡ ለጠልሰም ዕውቀት ምን አይነት አመለካከት አለው?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ብዙም ትኩረት በማይደረግበት የጠልሰም እውቀት ላይ በማተኮሩ ብቻ ስለ እውቀቱ ከማሳወቅና መረጃ ከመስጠት አንጻር በርከት ያሉ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። ጠልሰም ምን አይነት እውቀት እንደሆነ ከማሳወቅ አንስቶ ለምን አገልግሎት እንደሚውልና አባቶቻችን በዚህ ጥበብ አማካይነት ረቂቅ የሆኑ ለሕመም እና ለስቃይ የሚዳርጉ መናፍስትን በምን መንገድ እንደሚያክሙ ከማሳወቅ ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ ባሻገርም ይህን ሊጠፋ የተቃረበ እውቀት የሚመለከቱ መረጃዎችን በመሰነድ ጥበቡ ምን

አይነት አዘገጃጀት እና ሥርዓታዊ ክዋኔ እንዳለው ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ብሎም ለማሳወቅ ከማስቻል አንጻር ከፍተኛ የሆነ ሚና አለው።

እንዲሁም ከዚህ በኋላ ለሚሰሩ ጥናቶች መነሻ በመሆን ረቂቅ መንፈሳዊ ህክምናዎች ላይ ተጨማሪ ምርምር በማድረግና ዕውቀቱን መመርመር ለሚፈልጉ ግብዓት በመሆን ያገለግላል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ጊዜን ገንዘብን እና ይህ ጥናት በተካሔደበት ወቅት በሀገራችን ውስጥ የነበሩ ሁኔታዎችን መነሻ በማድረግ በሚከተሉት እሳቤዎች ላይ ብቻ ተገድቧል። ፎክሎር በርካታ የጥናት ዘርፎች ቢኖሩትም ይህ ጥናት ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር በጠልሰም ዕውቀትና የመድኃኒትነት እሳቤ ላይ ብቻ አተኩሯል። የጠልሰም እውቀት በኢትዮጵያ በሚገኙ ጥቂት አካባቢዎች የሚታወቅና የሚተገበር ቢሆንም የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በዋግምራ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዷ በሆነችው ፃታ ወረዳ ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ አካባቢ የሚሰራው የጠልሰም መድኃኒት በሌሎች ስፍራዎች ከሚሰሩ የጠልሰም መድኃኒቶች ልዩ ባህሪይና የአሰራር ሂደት አለው። በተለይም ለመድኃኒትነት የሚውለው የጠልሰም ዓይነት በግንባር ላይ የሚታሰር፤ በእጅ ላይ የሚደረግ እንዲሁም ሰውነትን የሚሸፍን የጠልሰም አሰራርን የሚከተል መሆኑ የተለየ ያደርገዋል። ከዚህም አንጻር በሀገራችን ከሚገኙ ጥቂት የጠልሰም ስራ ባለሙያዎች በተለየ ጥናቱ በፃታ ወረዳ ላይ አተኩሯል።

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የጠልሰምን ዕውቀትና መድኃኒትነት ለመመርመር ጥቅም ላይ የዋሉ የመስክና የሰነድ ዘዴዎች ምንነትና በጥናቱ ያገለገሉበት ሁኔታ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል። "የመስክ ምርምር በሦስት ልዩ ልዩ መንገዶች ሊካሄድ ይችላል። እነዚህ ሶስት ዋና ዋና መንገዶችም ምልከታ (observation)፣ ቃለ መጠይቅ (interview)፣ እና መጠይቅ (questionnaire) ናቸው (ፈቃደ፣1991)። የሰነድ ፍተሻ ደግሞ ከመስክ ውጪ ያሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ይውላል በመሆኑም ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች በተለያዩ የምርምር ማስሔጃ ዘዴዎች አማካይነት የተሰበሰቡ ሲሆን ለዚህም ከመዛግብት (የተለያዩ መጻህፍት እና መጣጥፎች) ዳሰሳ ባሻገር የመስክ ምልከታ እና ቃለመጠይቅ ቀዳሚ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሆነው አገልግለዋል።

### 1.7.2. ቃለ መጠይቅ

ከስሙ እንደምንረዳው ቃለ መጠይቅ በቃል የሚቀርብ መጠይቅ ነው። ከጽሑፍ መጠይቅ የሚለይበት ትልቁ ነጥብም ይህ ቃላዊነቱ ነው። በጠያቂውና በተጠያቂው መካከል የሚደረግ የፊት ለፊት ምልልስ ነው። በተለይ ከጽሑፍ መጠይቅ አንጻር ሲታይ ይህ ቃላዊነቱ ይዟቸው ብቅ የሚላቸው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችም አሉ። Catherine "Interview method requires a person known as the interviewer asking questions generally in a face-to-face contact to the other person or persons." በማለት ታስረዳለች (Khotari፣ 1990):: የቃለ መጠይቅ ፊትለፊትነት (በጠያቂና በተጠያቂ የፊት ለፊት ግንኙነት የሚቀርብ መሆኑ) ከግልጽነት፤ የተብራራ ምላሽን ከማስገኘት እንዲሁም የፊት ገጽታን ለማንበብ ከማስቻል ረገድ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

አንድ መረጃ ሰብሳቢ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ቃለ መጠይቅ ዘዴን ቢመርጥ እንኳ በየትኛው የቃለ መጠይቅ ዓይነት መረጃውን እንደሚሰበስብ ጭምር መወሰን አለበት። በምርምር ስራ ስነ ዘዴ ላይ ዳሰሳ ያደረጉና የተለያዩ መጻህፍትን የጻፉ ምሁራን የቃለ መጠይቅ ዓይነቶችን በራሳቸው መንገድ በተለያየ መንገድ ከፍለዋል። Catherine Dawson እና ያለው እንዳወቅ የተለመዱና በብዛት አገልግሎት ላይ የሚውሉ የቃለ መጠይቅ ዓይነቶች structured interview (ውስን ቃለ መጠይቅ)፣ semi structured (ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ) እና unstructured interview (ነጻ ቃለ መጠይቅ) በመባል በሦስት እንደሚከፈሉ ይገልጻሉ (dawson፣ 2002፣ ያለው፣ 2009)። David E.gray ደግሞ የቃለ መጠይቅ አይነቶች አምስት መሆናቸውን በመግለጽ ውስን እና ከፊል ነጻ ከሚሉት የቃለ መጠይቅ ዓይነቶች በተጨማሪ Non-directive interview (ኢ-ቀጥተኛ ቃለ መጠይቅ)፣ Focused interview (ተተኳሪ ቃለ መጠይቅ) እና Informal conversational interviews (ኢ-መደበኛ ምልልስ ቃለ መጠይቅ) የሚባሉ የቃለ መጠይቅ ዓይነቶች እንዳሉ ያብራራል (E.gray, 2004)። እነዚህ የቃለ መጠይቅ አይነቶች አንዳቸውን ከአንዳቸው የሚለያቸው ብሎም የጋራ የሚደርጋቸው ነጥቦች አሏቸው። ከእነዚህ የቃለ መጠይቅ አይነቶች ውስጥ ለዚህ ምርምር መረጃ መሰብሰቢያነት ተመራጭ የሆነው የቃለ መጠይቅ ዓይነት ነጻ ቃለ መጠይቅ ነው።

ነጻ ቃለ መጠይቅ ጠያቂው መላሹ በሚሰጠው ምላሽ ላይ ተመስርቶ በአእምሮው የሚጫሩበትን ቅጽበታዊ ጥያቄዎች እዚያው የመጠየቅ መብትን የሚሰጥ የቃለ መጠይቅ ዓይነት ነው። በዚህ መነሻነትም በዚህ የምርምር ስራ ጥናቱ የተካሔደበትን ወረዳ የሚመለከቱ አጠቃላይ መረጃዎች፣ የጠልሰምን ምንነት፣

የአዘገጃጀት ሂደት፣ የመድሀኒቱ አሰጣጥ ሂደት፣ የጠልሰምን አይነት፣ የህመም መለያ ዘዴዎችና የህመም ዓነቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ከጠልሳሚዎች፤ ከአካባቢው ነዋሪዎችና ከተለያዩ የወረዳው ሃላፊዎች በነጻ ቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

### 1.7.1. ምልከታ

ምልከታ በዘፈቀደ የሚከናወን ተግባር አይደለም። ሆን ብሎ ተዘጋጅቶ በመገኘት፣ በስልት የሚከወን ሁሉንም የሰሜት ህዋሳት ትብብራዊ ጥምረት የሚሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። በምልከታ የምንሰበስበው መረጃ በአይናችን የምናየውን ብቻ ሳይሆን የምናሽተውን፣ የምንቀምሰውን፣ የምንዳስሰውን፣ የምንሰማውን ነገር ሁሉ የሚመለከት ነው። ምልከታ ዘመን በወለዳቸው መሳሪያዎች ይከናወናል። ምልከታ በሩቅ ተመልካችነት ወይም በቅርብ ተሳታፊነት ሊከናወን ይችላል። አንድ አጥኚ በሩቅ ተመልካችነት ከዳር ሆኖ ክዋኔውን ያስተውላል፣ ይመለከታል፣ ይመዘግባል። አሊያም ደግሞ በተሳታፊነት በክዋኔው እየተሳተፈ ምልከታውን ያከናውናል። እነዚህ ሁለት ዘዴዎች የየራሳቸው ጠንከራና ደካማ ጎን ቢኖራቸውም ቅሉ እንደ ጠልሰም ላሉ ጥናቶች ምልከታ አይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። በተለይም አጥኚው በጥናቱ ቦታ ከተጠኝዎቹ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ አብሮ ቆይቶ አጠቃላይ ሂደቱን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በመከታተልና ማስታወሻ በመያዝ አጠቃላይ የተጠኝዎቹን ክዋኔና ባሕርይ ለመገምገም የሚችልበት የምልከታ ስልት ከሌሎች የምልከታ ስልቶች ተመራጭ ነው (Dornyei፣ 2007)። ስለሆነም በዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ የመረጃ ግብዓቶች ከዕውቀቱ ባለቤቶች በቦታው በመገኘት ተሰብስበዋል። ይህ ሁኔታ ደግሞ የምርምር የመቼት እና አውድ ሁኔታን ይዞ ብቅ ይላል። በምርምር ሂደት ውስጥ የተለያዩ የመቼት ዓይነቶች አሉ። እነርሱም ተፈጥሯዊ መቼት፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት እና አርቲፊሻል መቼት ናቸው። ተፈጥሯዊ መቼት ሥርዓቱ በሚከወንበት ትክክለኛ ጊዜና ቦታ በመገኘት የሚሰበሰብ ሲሆን ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ደግሞ ተፈጥሯዊው ክዋኔው ባልተገኘበት አጋጣሚ ተፈጥሯዊውን አስመስሎ የሚሰራ መቼት ነው። አርቲፊሻል መቼት ግን ከሁለቱ ፍጹም የተለየ ሲሆን ክዋኔው በሌለበትና ክዋኔውን አስመስሎ መስራት በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ በቦታው ከተገኙ የተለያዩ ጠቋሚ ማስረጃዎች የሚሰበሰብበት የመቼት ዓይነት ነው። ከእነዚህ የመቼት ዓይነቶች ውስጥ ለዚህ ጥናት ተመራጭ ሆኖ የተገኘው ሁለተኛው ማለትም ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ነው።

ይህ ጥናትም የምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን በትክክል ጠልሰምን የሚጠለስሙ ሰዎችን በማግኘትና በማነጋገር፤ ቀድሞ የሰሯቸውን ማሳያ የጠልሰም ሥራዎች በፎቶ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በማስቀረት ተሰብስቧል። ከዚህ ቀደም በተለያዩ ሕመሞች ተጠቅተው የነበሩ ሰዎችን በማግኘትና

ሕመሙ ጥሎባቸው ያለፉ ጠባሳዎችንና የተሰጧቸውን ጠልሰማዊ መድሃኒቶች በመመልከት መረጃው ተሰብስቧል።

### 1.7.3. የሰነድ ማስረጃዎች

የሰነድ ማስረጃዎች ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆኑ ይህም በተለያዩ ስፍራዎች የተሰሩ የጠልሰም ውጤቶች ማለትም ከቤተመጻህፍት ከአርካይቭ ከልዩ ልዩ ባለሙያዎች እንዲሁም ከልዩ ልዩ ስፍራ የሚገኙ ማስረጃዎችን የሚመለከት ነው። ይህም የተለያዩ የጠልሰም ሥዕላትንና አስማቶችን አሳሳል እና አቀራረብ ለማጤን አስችሏል። ከዚህ ባለፈም ጥናቱ ማእቀፍ ስላደረጋቸው ፎክሎራዊ ንድፈ ሃሳቦች ምንነት ለማጤን የተለያዩ መጻህፍትና የድኅረ ገጽ መረጃዎች ጥቅም ላይ ውለዋል።

እንዲሁም በባህላዊ ዕውቀት ባለቤቶች ወይም በመረጃ ሰብሳቢዎች ወይም በባለሙያዎች ተጠብቀው ሲቆዩ የሚኖራቸውን ባህሪያዊ መገለጫ ማጤን ያስችላል። ይህም የልማዳዊ እውቀቱን ተስተላልፎ ለውጥና ቀጣይነት መገንዘብ ያስችላል።

### 1.7.4. መረጃ መሰነጃ መንገድ

ከመስክ መረጃ አቀባዮች ጋር በሚኖረው መስተጋብር መረጃ በተለያዩ መንገዶች ይሰበሰባል ይሰነዳል። ይህም በማስታወሻ ደብተር በመቅረጸ ድምጽ በፎቶግራፍ። በማስታወሻ የሚሰንዱ መረጃዎች የዕውቀቱን መረጃ አቀባዮች ለቃለ መጠይቁ የሚሰጡትን መረጃ ለመሰነድ የሚያገለግል ይሆናል። የመቅረጸ ድምጽ መረጃዎችን በመሰነድ ሂደት ውስጥ ጎን ለጎን አብሮ የሚሄድ የመረጃ መሰብሰቢያና መሰነጃ መንገድ ይሆናል። እንዲሁም በምልከታ ወቅት ያሉትንና በመረጃ አቀባዮች በሚሰጠው መረጃ በመንተራስ አስፈላጊ ገጽታዎችን በፎቶግራፍ ለጥናቱ መሰብሰብን ታሳቢ ይደረጋል።

### 1.7.5. የናሙና መረጣ ዘዴ

በፃታ ወረዳ ውስጥ ስምንት (8) ቀበሌዎች የሚገኙ ሲሆን ይህ ጥናትም በዳምትኩነ እና አርመር ቀበሌዎች ላይ ያተኮረ ነው። ከስምንቱ ቀበሌዎች መካከል እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያትም ይህ የጠልሰም እውቀት በስፋት የሚገኘውና ክዋኔው እየተተገበረ ያለው በእነዚህ ቀበሌዎች ብቻ በመሆኑ ነው። በሌሎቹ ቀበሌዎች በተወሰነ

መልኩ ያለ ቢሆንም የዳምትኩነ እና አርመር ቀበሌዎችን ያህል የሰፋና የተጠናከረ ባለመሆኑ የተደራጀ መረጃ ለማግኘት ሲባል እነዚህ ሁለት ቀበሌዎች ተመርጠዋል።

ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች በዓላማ ተኮር ዘዴ የተመረጡ ሲሆን ከላይ እንደተገለጸው ተተኳሪ ስፍራውም ሆነ መረጃ አቀባዮች የጥናቱን ርእሰ ጉዳይና የጥናቱን ዓላማ ተተኳሪ በማድረግ የተመረጡ ናቸው። ምክንቱም ዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ የጥናቱን ዓላማ መነሻ በማድረግ የሚደረግ የናሙና መረጣ በመሆኑ ከእነዚህ ሁለት ቀበሌዎች የተውጣጡ ጠልሳሚያንን በማግኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል።

### 1.8. የመስክ ተሞክሮ

የመስክ ተሞክሮ ለአንድ የጥናት ጽሁፍ ወሳኝ ነው። ምክንያቱም ተከታይ አጥኝ የቀደሙ ጥናቶቸን በሚያነብበት አጋጣሚ ከነበረው የመስክ ዕውቀት ተጨማሪ ግብአቶችን ይዞ እንዲዘጋጅና ሊገጥመው የሚችለውን ውጣ ውረድ በብልሀት እንዲያልፍ መንገድ ይጠቁማል። ለዚህም አላማ ሲባል የመስክ ልምዴን ከዚህ በታች አስፍሬአለሁ።

የመጀመሪያ ጉዞ ያደረኩት 2012 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ ሲሆን አካባቢው ከአዲስ አበባ 708 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ሁለት ቀን በጉዞ እንዳሳልፍ ምክንያት ሆነ። በገባሁ በማግስቱ ለጉዞ ከመነሳቴ በፊት የጥናት ትኩረት የሆነችውን ወረዳ በሚመለከት መረጃ ሰጪዎችንና የዕውቀቱን ባለቤቶች በስልክ የማግኘት ዕድል ስለነበረኝ በጉዞዬ ማግስት በቀጥታ መረጃ አቀባዮችን አገኘሁ። ከብዙ የሁኔታ አጋጣሚዎች እንዳስተዋልኩት አብዛኛው የኢትዮጵያ ገጠራማው ማህበረሰብ ለሰው የሚያዝን የከተማን ሰው ውጣ ውረድ የማይችል አድርጎ የማሰብ ሁኔታ ይስተዋላል። በተመሳሳይም ያገኘኋቸው የመረጃ አቀባዮቼ እጅግ በማዘንና በትህትና ተቀበሉኝ። ይህ ሁኔታ ለኔ በሚመች ስፍራ እነሱን ከመጥራት ይልቅ የእግር መንገዱንና ድካሙን በመቋቋም መስሎ ሳይሆን ሆኖ በማሳየት ለመረጃ አቀባዮቼ በጎ የሆነ አመለካከት በኔ ላይ እንዲኖራቸው ማድረጉን አይቻለሁ። የመጀመሪያ ቀን ትውውቅ በማድረግ እና ቤተሰባዊ ወግና የመጣሁበትን አላማ በመንገር ልባዊ ስምምነት ለማድረግ በቃሁ። በማግስቱ መረጃ የመሰብሰብ ሂደት በመጀመር ለተከታታይ አስር ቀናት ያህል በጥሩ መንፈስ ስራየን አከናወንኩ፤ ነገር ግን ለሚቀሩ ስራዎች እራሳችንን አዘጋጅተን የጉዞዬን ቀን ጨርሼ ተመለስኩ። ከዚያ በኋላ በሀገራችን የተከሰተው ኮሮና ቫይረስ በተከታይነት ደግሞ የሰሜኑ ጦርነት አካባቢውን የችግሩ ተጋላጭ አድርገውት በመቆየቱ በመሀል ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር መገናኘት እንዳልችልና ብዙ ጊዜ እንዲባክን ምክንያት ሆነ። ነገር ግን የጦርነቱ ሁኔታ በተወሰነ ሁኔታ መሻሻል ሲያሳይ ተመልሼ 708 ኪ.ሜ ርቀት በመጓዝ ሁለተኛ ዙር መረጃዬን ሰበሰብኩ። በመሀል በጦርነቱ ተቋርጦ የነበረው መረጃ የመሰብሰብ ሂደት በጎ ጎኑ የጐደሉትን እያንዳንዱን መረጃዎች ነጥብ በነጥብ ፈልፍዬ እንዳገኝና እይታዬን እንዳሰፋ አድርጎኛል። ይህ የሆነው ግን እራሴን ከጥናታዊ ጽሁፍ ሳለይ እረጅም ጊዜ በማሳለፌ ነበር።

የአካባቢውን ዳራ በተመለከተ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ክፍተት ገጥሞኝ ነበር። ምክንያቱም ለጥናት የተመረጠችው ፃታ ወረዳ  በቅርቡ የወረዳነት ደረጃ ያገኘች በመሆኗ የተደራጀ ተቋም አግኝቶ የሚመለከተውን መረጃ ለመቀበል አዳጋች ነበር። ነገር ግን የወረዳውን አስተዳዳሪ ፣ የግብርና ባለሞያ፣ የቱሪዝም ባለሞያና የአካባቢውን ነዋሪዎች በማነጋገር የመረጃ ክፍተቱን ለመሙላት ሞክሬአለሁ። እንዳጠቃላይ መረጃ አቀባዮቹ ቀናና ተባባሪ ነበሩ። ነገር ግን  እውቀቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ጠልሳሚዎችን እንደ "መተተኛ" የማየቱ ሁኔታ ለዕውቀቱ ባለቤቶች የሚኮሩበት ሳይሆን የሚያፍሩበት በመሆኑ በርግጠኝነት ሁሉንም መረጃዎች በተብራራና ድብቅ ባልሆነ መንገድ የመናገር ፍርሃቶች ነበሩ። ነገር ግን የእውቀቱን ስፋት እንዲሁም ጥበብና ቀደምት ዕውቀትነት በመሳሰሉት የማግባቢያ መንገዶችን በመጠቀም መረጃውን በተሟላ ሁኔታ ለማግኘት ችያለሁ። በሌላ ጐኑ እውቀቱን ለማግኘት ባደረጉት መውጣት መውረድ እንዲሁም ጥበቡን መናገር በራሱ ትክክል አይደለም በሚል የመደበቅ ሁኔታ ነበረ። ይህንንም ቢጠና ስላለው ትልቅ ጠቀሜታ እንዲሁም እነሱ በህይወት ሲያልፉ ቀሪው ትውልድ የአባቶቹን የአደራ ጥበብ የሚተላለፍበት አንድ መንገድ አድርገው እንዲያስቡ  በመንገር መረጃው የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ ችያለሁ።

## 1.9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ይህ የጠልሰም ዕውቀት መንፈሳዊ ጉዳዮችን የሚቃኝ በመሆኑ መረጃ ሰጪዎች አንዳንድ መረጃዎችን ግልጽ በመሆነ መንገድ ያለመስጠት ሁኔታዎች ተስተውለውባቸዋል። በዚህም ምክንያት የተወሰኑ የመረጃ እጥረቶች ያጋጠሙ ሲሆን በተዘዋዋሪ መረጃውን ለማግኘት የሚረዱ መንገዶችን በመጠቀም መረጃዎችን ለማግኘት ተሞክሯል። ከዚህ ባለፈም ከቃላዊ መጠይቁ በዘለለ  መረጃን ማግኛ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ ጽሁፋዊ ማስረጃዎችን መነሻ በማድረግ የጉደሉ መረጃዎችን ለማሟላት ጥረት ተደርጓል።

ከዚህ ባለፈም በዚህ ጥናት ላይ ዋናው ተግዳሮት የነበረው ዕውቀቱ በባህሪው ሚስጢራዊ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የማህበረሰቡ አመለካከት አሉታዊ አለመሆንና ስለ መድኃኒትነቱ ፈቃደኛ ሆኖ መረጃ ያለመስጠት ሁኔታ በተወሰነ ሁኔታ ተስተውሏል። ሆኖም መረጃ አቀባዮች እስካሁን ሲተገብሩት በመቆየታቸው ዕውቀቱን ከስፍራው በሚታወቁ ሰዎች ለማግኘት ጥረት ተደርጓል። ጥናቱ የመጠናቱን ዘርፈ ብዙ ጥቅም በመንገርና በማግባባት መረጃዎችን ለማግኘት ተሞክሯል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ይዛመዳሉ ተብለው የታሰቡ ሐሳቦች እና መረጃ መተንተኛ የሆኑ ንድፈ ሐሳባዊ ማህቀፎችን አስተሳስሮ የያዘ ክፍል ነው። ክለሳ ድርሳናት ዓቢይ ርዕስ በሥሩ ሶስት ንዑሳን ርዕሶችን ያቀፈ ነው። በመጀመርያው ንዑስ ርዕስ የጥናቱ ማዕከላዊ ሃሳብ የሆነው የጠልሰም እሳቤ ምንነት ለመገንዘብ የሚያስችሉ ጽንሰ ሃሳባዊ ጉዳዮች የተካተቱበት ሲሆን የጠልሰም ምንነትና ብያኔ የቀረበበት ክፍል ነው። በሁለተኛው ክፍልም ለጥናቱ መተንተኛ የሆኑ ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳዮች ምንነት ተብራርቷል። በሶስተኛው ንዑስ ክፍል የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የቀረበ ሲሆን ይህ የጥናት ቅኝትም ከእኔ ጥናታ ጋር ባላቸው ቅርበት ቅደም ተከተል (ከቅርቡ ወደሩቁ) ተቃኝተዋል።

### **2.1.** ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል በጠልሰም ዕውቀት ዙሪያ የሚነሱ ጽንሰ ሐሳቦች፤ የጉዳዩ ማዕከላዊ እሳቤዎች፣ በዕውቀቱ ዙሪያ ያሉ እይታዎችና መታገጊያዎች ተዳሰዋል። ስለሆነም ይህ ክፍል ጠልሰም ምንድነው?፤ እንዴትና መቼ ተጀመረ?፤ በጠልሰም ውስጥ የሚነሱ ዓቢይ እሳቤዎችስ ምን ምን ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን ይመልሳል።

### 2.1.1. የጠልሰም ምንነት

“ጠልሰም” የሚለው ቃል መነሻ አረብኛ ቋንቋ ሲሆን ትርጓሜውም “እጅግ ኃይለኛ ቁስ ወይም ነገር” ማለት ነው (Burtea፣ 2001፣94)። አንድም “ጠልሰም” ማለት “ክታብ ጠንቋዮች በጥቁር ቀለም ጥፈው ጠልስመው የሚያሲዙት። ክታብ፡ አስማቱ፡ ጠልሰም በያስማቱ ውስጥ የሚጣል ሥዕልና ሐረግ፡ ሰንጠረዥ ሙጭርጭር ጥፈት” ነው (ኪዳነወልድ፣ 1948፣502)። የእንግሊዘኛው መዝገበ ቃላት ደግሞ “Something worn in the hope that it will protect the wearer” በማለት ጠልሰም ማለት ያደረገውን (ጠልሰሙን ያሰረውን ሰው) ከአንዳች ነገር ይጠብቃል ወይም ይከላከላል ተብሎ የሚታመንበት ወይም ተስፋ የሚደረግበት ነገር መሆኑን ይገልጻል (https://dictionery.abyssinica.com/ጠልሰም, 2019)። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትን የሚፈታው መዝገበ ቃልም ጠልሰም “ሴቶች ለጌጥ በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉት የብር ወይም የወርቅ አሸንክታብ” መሆኑን ይገልጻል (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣1972፣251)።

ጠልሰም አብዛኛውን ጊዜ የተለያዩ ምስሎችና ስዕሎችን ብሎም ልዩ ልዩ ምስጢራዊና አስማታዊ ጽሑፎችን በአንድነት የያዘ መንፈሳዊ ጥቅል ወረቀት እንደሆነም ይነገራል። ከዚህም በተጨማሪ ጠልሰም ከተለያዩ ስዕላዊ መግለጫዎች ጋር በመቆራኘት ክፉ መናፍስትና ክፉ ዕድሎችን የሚያመጡ የተለያዩ በሽታዎች ለመፈወስ ይጠቅማል (Burtea፣ 2001፣ 95)። በርግጥ ሰዎች ጠልሰም የሚለውን ቃል “ክታብ” ከሚለው መጠርያ ጋር በማቀያየር ይጠቀሙበታል። ከዚህ በመነሳትም “በአንገት የሚታሰር ማጌጫ ሀብል ወይም ማተብ” የሚለውን አጠቃላይ አጠቃቀም ይገለገሉበታል።

ጠልሰም አንድም “ጠልሰም” አንድም ደግሞ “ስዕል” ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል። ስዕል የአማልክት ወይም ልዕለ ሰብ ታሪክና ገድልን የሚገልጽ የተጨባጩን ዓለም የሚያሳይ የጠልሰም ዓይነት ነው (Mercier፣ 1979፣ 24)። ስዕል በታሪክ የሚታወቁ ሁነቶችንና የሰዎችን ገድል የነገስታትን ታሪክ ይይዛል። ለዓብነት ያህል በኦርቶዶክስ አማኞች ዘንድ ከሚነገሩ ተረኮች ውስጥ የቅዱስ ጊዮርጊስ እና የአቡነ አረጋዊ ተረኮች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ተረኮች መነሻ በማድረግም ጊዮርጊስ ከዘንዶው ጋር የሚያደርገውን ፍልሚያ ብሎም አቡነ አረጋዊ ዘንዶን በመጠቀም የደብረ ዳሞ የተባለን ተራራ ሲወጡ የሚያሳዩ ስዕላት ይሳላሉ። እንዲህ ዓይነት የጠልሰም ስዕላት ምንም እንኳ የራሳቸው የሆነ ተምሳሌትነት ቢኖራቸውም በስፋት በጠልሰም ላይ ከአስማት ጋር ተስለው እንደምናገኛቸው ስዕላት ምስጢራዊ ኢ-ሊያም አስማታዊ ትርጓሜን አይዙም። በአንጻሩ ግን ጠልሰም ረቂቅ ትዕምርቶችን በማካተት የተለያዩ አስማታዊና መንፈሳዊ ጥበቦችን በማጣመር ይይዛል። ለዚህም የሰሎሞን ህቱም ምስጢራዊ ማህተም፣ ስምንት አንጻር ያለውን

የሰሎሞን ኮከብና መርበብተ ሰሎሞንን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል (Mercier፣ 1997፣ 49)። እንዲህ ዓይነት ምስጢራዊ ጠልሰሞች እንዲሁ ታይተው የሚፈከሩ ባለመሆናቸው ከሌሎች ስዕሎች ይለያሉ። አንድም የጠልሰምን ስዕል ልዩ የሚያደርገው ራሱን የቻለና ሰፊ ሐቲት የሚያስፈልገውን የሐረግ ጥበብ በውስጡ በመያዙ ነው። ከዚህ አንጻር ስለጠልሰም ሲታሰብ ሐረግን ማንሳት ያሻልና ስለ ሐረግ ጥበብ ጥቂት ላስፍር።

> "በኢትዮጵያ የሐረግ ስዕል መቼ እንደተጀመረ ባይታወቅም የረዥም ዓመታት ዕድሜ እንዳለው ይነገራል። በረጅም ዘመን የተሰሩ ቅርሶች፣ በቁፋሮ የተገኙት ሐውልቶችና ጽሑፎች፤ የኢትዮጵያ ነገስታት መከሊቶች ወይም ገንዘቦች፤ በስዕልና በሐረግ ስእል ያጌጡ በአክሱም ሀውልት ላይ የተሳሉ ሐረጎች፤ በላሊበላ ቤተመቅደሶች ውስጥ የተሳሉ ሐረጎች እና በጥንታዊ የእንጨትና የብር መስቀሎች ላይ የተሳሉ የሐረግ ስዕሎች የሐረግ ስእልን የረጅም ዓመታት እድሜ መኖር ያመለክታሉ" (ፍሥሐ ይሁን፣ V፣ 2001)።

ስለሆነም የሐረግ ስእል ከእድሜው ርዝማኔ ባለፈ የስእል ጥበቡ በተለያዩ የድንጋይ፣ የእንጨትና የብረት ቁሶች ላይ የተቆላለፈ የዛፍ ሐረግ መሰልና የተገመደ ገመድ ጉንጉን መሰል ወዘተ. እየተደረገ ይሳላል። በጠልሰም ስእሎች ውስጥም ይህ የሐረግ ጥበብ ተካቶ ይሳላል።

ከሁሉ በላይ በርካቶች የጠልሰምን ጥበብ የሚያገናኙት ከሰሎሞን ጋር ነው። ሰሎሞን ከአባቱ ዳዊት በኋላ የቤተመቅደሱን ግንባታን ሌሎች የአስተዳደር ጥበቦችን የተገለገለበት በጠልሰም ምስጢራዊ ኃይል ነው (Chernetsov S.፣ 2005፣ 89)። እነዚህም ከጠልሰም ዕውቀት በሚመነጩ ጥበቦች ተክኖ የከወናቸው ናቸው በማለት የሚያቀርቡ አሉ። ለዚህ ማሳያ አድርገው የሚያወሱት ማስረጃ የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ ነው። በሰሎሞን ቤተመቅደስ ግንባታ ጊዜ መልአኩ ሚካኤል የእግዚአብሔር ህቡዕ የሆኑ ስያሜዎች ያሉበት ቀለበት ሰጥቶታል በማለት ያነሳሉ። የጠቢቡ ሰሎሞን መጻህፍት ከሆኑት መካከል አንዱ በሆነው በመሓልየ መሓልየ ዘሰሎሞን ላይ "ባለ ብር ጉብጉብ የሆነ የወርቅ ጠልሰም ያድርጉልሽ" የሚል ቃል ተጽፎ ይገኛል (መሓልየ መሓልየ 1÷11)።

### 2.1.2. የጠልሰም አጀማመር

አሁን አሁን የጠልሰም ሥዕላት በዘመናዊ መንገድ እየተሳሉ በሥዕል አውደ ርዕዮች ላይ ሲቀርቡ ይስተዋላል። ሆኖም ሥዕላቱን ዘመንኛ የሚያሰኛቸው የሚሳሉበትና ለእይታ የሚቀርቡበት መንገድ እንጂ የሥዕላቱ እሳቤ መነሻ መንፈሳዊ ዕውቀቶች ናቸው። በዚህ ሳቢያ ጠልሰምን አንስቶ መንፈሳዊ እውቀትን መዘንጋት

ማደርያውን ትቶ የሚያድረውን እንደማንሳት ይቆጠራል። ስለሆነም የጠልሰም ዕውቀት እና ጅማሮ ሲነሳ ከእምነት ጋር የተያያዙ እሳቤዎች አብረው ይነሳሉ።

የጠልሰም ሥራ የተጀመረው የሰው ልጆች ከንግግር ባለፈ ሐሳባቸውን በጽሑፍ መግለጽ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቀማሉ፤"ፊደል የጻፈ እና ጠልሰም የቀረፀ የመጀመሪያው ሰው የካም አሥረኛው ትውልድ ሲሆን የእርሱ ልጅ ኢትኤል ነው" (ፍሥሐ ይሁን፤2001 vii)።

በተለይ በኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንድ ሺሕ አምስት መቶ ዓመት ዓለም አካባቢ ጀምሮ የቁም ጽሑፍ ሥራ እንደተጀመረ ፍሥሐ ይሁን (2001፣ viii) በመጽሐፋቸው ገልጸዋል። የቁም ጽሑፍ አስቀድሞ ይጻፍ የነበረው በአጥንት በጠፍጣፋ ድንጋይና በእንጨት እንደነበረም ተጠቅሷል፤ቀስ በቀስ ይህ እያደገ መጥቶ ኢትዮጵያውን ከእንሰሳት ቆዳ ብራና በማዘጋጀት ብዕር ቀርፀው ቀለም በጥብጠው የፍልስፍና የሃይማኖትና ማህበረሰባዊ መጻሕፍትን መጻፍ እየተለመደ መጥቷል።

ጠልሰም እንደ ፍልስጤም እና ሌሎች የዐረብ ሀገራት ባሉ በበርካታ ሃገራት ስልጣኔ ውስጥ ይገኛል። ጠልሰምን በአብዛኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከመዳሰሳችን በፊት የሃይማኖታዊ ጽሁፎች አጀማመርን መቃኘት ተገቢ ይሆናል። ምክንያቱም ስዕልና ጽሑፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትስስር አላቸው። ይህም የጽሁፍና የስዕልን ርባና እንዲሁም በኢትዮጵያ ያላቸውን የተቀባይነት ደረጃ ለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን የጠልሰምን ስፍራ በቀኖናውና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን እይታ እንድንገነዘብ ያስችለናል።

> Probably the most prolific area of Abyssinian literature is made up by the different types of "forbidden" writing, beginning with Biblical apocrypha and going on to spells and incantations. The main point of interest in this area is that the texts, which are no less bookish in character than other areas of writing in Ethiopic, at the same time reflect folk belief (Chernetsov. ፣ 2005፣189).

ከላይ የሰፈረው ጽሑፍ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፎች በመጽሐፍ ቅዱስ የተከለከሉ ናቸው ከሚባሉ አፃፃፎች እና ድግምቶች የተገነቡ መሆናቸውንና እነዚህ ክልክል የሆኑ አፃፃፎች በተመሳሳይ ሁኔታ የቡድኖችን እምነት የሚያንጸባርቁ ሆነው መገኘታቸውን ያትታል። ስለሆነም በኢትዮጵያ የጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ እሴቶች ተጣምረው መሄዳቸውን ከላይ ከሰፈረው ሃሳብ መገንዘብ ይቻላል።

ምናልባትም በርካታ የኢትዮጵያን የጽሑፎ ሥራዎች አንድም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረትነት ያላቸው አንድም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ኖራቸው ነገር ግን በሀይማኖቱ አስተምህሮ የተከለከሉ ሃሳቦች የተቀላቀሉባቸው ናቸው (አጽዕኖቱ የእኔ ነው)።

በኢትዮጵያ ክርስትና የተጀመረው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ የተለያዩ መዛግብት ያወሳሉ። Christianity emerged in Ethiopia in the mid-fourth century in the Aksumite Kingdom, endorsed by the King Ezana and the Syrian saint Fromentius (Henze 2000; Munro-Hay 2002; Tamrat 1993). ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የጽሑፍና አዋልድ መጻሕፍት በቤተክርስቲያኗ ጥቅም ላይ ይውላሉ። እነዚህ ዕውቀቶች ደግሞ ከክርስትና እምነት ጋር ተዛማጅነት አላቸው። በተቋማዊ ቀኖና በግለሰቦች ዕውቀት የሚኖረውን ቅዱስና እርኩስ፤ ተቀባይነትና ክልክል እሳቤዎች ይገኙበታል። አንዳንድ የግለሰብ እውቀቶች እንዲሁም የየአካባቢ ትምህርት ቤቶች በዕውቀቱ ስርጭትና ዕድገት ውስጥ ትልቅ ስፍራና ደረጃ ይሰጣቸዋል። የቅኔ፤ የድጓ፤ የቁም ንባብ፤ የተለያዩ የኢትዮጵያ የክርስትና ትምህርቶች በየአካባቢው በሚኖሩ መምህራን ደረጃም የሚታወቁበት ሂደት አለ። በዚህ የትምህርት ዕድገትና ስርጭት ውስጥ የሚኖረው የዕውቀት ሽግግርና ዕድገት ውስጥ የአንዱ ዕውቀት በሌላው መተቸት እንዲሁም የዕውቀቱ ተለዋዋጭነት በመኖሩ ሙሉ በሙሉ በሃይማኖቱ ቀኖና ውስጥ ተቀባይነት የለውም። በኢትዮጵያ የቤተክርስቲያን አሰራር ታሪክ ውስጥ የስዕል ስራ ሁለት ገፅታዎች አሉት። የመጀመርያው ህክምና ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አምልኮ ነው። በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ለአገልግሎት የሚሳሉ ስዕሎች ሲኖሩ ለህክምና ተብለው የሚሳሉ ሥዕሎች ደግሞ አብዝሀኛውን ጊዜ ከተቋሙ ውጪ በሆኑ ግለሰቦች ይተገበራል። በመሆኑም እውቀቱ በኢትዮጵያ በሁለት አቅጣጫ የሚታይ እንደሆነና የእምነቱ ቀኖና በሚፈቅደው መንገድ የሚሳሉና የቤተክርስቲያኗን ዕውቀት በማከል በግለሰቦች ግላዊ ፍላጎትና አስፈላጊነት ላይ መሰረት ያደረጉ ይገኙበታል ።

እንዲህ አይነቱ እውቀት ከቤተክርስቲያን ቀኖና አንጻር ያለውን አተያይ በተመለከተ Ménonville “In search of the Debtera: An intimate Narrative on Good and Evil in Ethiopia Today” በሚለው መጣጥፉ እንዲህ በማለት ያትታል።

> Nonetheless, the producers of healing and demonic images (otherwise known as talismans) are usually the ‘debtera’ who represent a ruptured social category and can be classified as either part of the orthodox clergy or independent healers, wise men, magicians, and even swindlers (Ménonville ፣2018፣105-144).

እንደ Ménonville ገለጻ በሌላ አጠራራቸው ጠልሰም ተብለው የሚታወቁ የፈውስ እና ድግምታዊ ሥዕሎችን የሚሰሩ ሰዎች "ደብተራ" እንደሚባሉ በመጥቀስ እነዚህ ሰዎች ከማህበረሰቡ የማይስማማ ቡድን አባል እና ገለልተኛ ተደርገው የሚታሰቡ፤ በአንድ በኩል አዋቂ፣ መድኃኒተኛ፣ አስማተኞች እና አጭበርባሪም ጭምር ተደርገው የሚታዩ የኦርቶዶክስ ካህናት እንደሆኑ ያትታል። ከዚህ ሃሳብ ማጤን እንደሚቻለው እነዚህ መድኃኒት ሰሪ ደብተራዎች አንድም ማህበረሰቡ በአሉታዊ እይታ የሚያያቸው አንድም ደግሞ አዋቂ ተደርገው የሚታሰቡ መሆናቸውን ማጤን ይቻላል። ደብተራዎች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ያሉ ማህበረሰቦች እነዚህን መድኃኒት ሰሪዎች በተለየ ዓይን (በፍራቻ) ቢመለከቷቸውም ለፈውስ ግን ይፈልጓቸዋል።

> The debtera, defined as 'the master of spells, the paragon of ingeniousness, ruse and eceitfulness, and, in the eyes of the more rigid priests, a fallen and impure being. These clerics have two faces, one of them bright and diurnal, lit by the light if the knowledge of God, the other obscure, casting evil spells in the dark of night' (Ménonville፣ 2018፣ 116)።

ደብተራ አንድም በዕውቀት የረቀቁ፣ በጥበብ የነጠቁ፣ ተደርገው ታሰባሉ። አንድም ደግሞ በቃላት የመርገም ስልጣን ያለው ተጠቃሽ አጭበርባሪ በኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮችና ቄሶች ዘንድ ውዳቂ የረከሱ ሰዎችም ተደርገው ይወሰዳሉ። ይህ አመለካከት በሁለት አግባባዊ እይታ የሚታይ ነው። የመጀመርያው በእውቀት የበራለትና በብርሃን የሚመሰል ሲሆን ሁለተኛው ጨለምተኛ በመሆን በምሽት የሚገለጽ ነው። የደብተራ ዕውቀት በሁለት ወገን መገልገሉ በዕውቀቱ ጉዳትም ጥቅምም ለማድረስ የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ማህበረሰቡ ስለሚያምን ነው።

ከላይ ስለጠልሰም ምንነት እና ጅማሬ ከሰፈሩት ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው ጠልሰም ጥልቅ ጉዳይ መሆኑን ነው። ጠልሰም ሲነሳ ወዲህ የመድኃኒትነት እሳቤ፤ ወዲህ የመንፈሳዊ ሃይል ጉዳይ፤ ወዲህ ደግሞ የስዕል እሳቤዎች ይነሳሉ። የዚህ ምርምር ዓቢይ ጉዳይ ደግሞ መድኃኒትነት ነው። የመድኃኒትነት ፅንሰ ሃሳብ ሲነሳ ደግሞ ገኖን ሆኖ የሚታየው የጠልሰም አስማታዊነት ሃይል ነው።

### 2.1.3. ቃላዊነትና ሃይል (አስማት)

በጠልሰም ዕውቀት ውስጥ ከሚነሱ እሳቤዎች መካከል ቃላዊነትና ሃይል ወይም አስማት ተጠቃሽ ነው። ቃል በእምነትና በመንፈሳዊ ትግበራዎች ትልቅ ስፍራ አለው። በክርስትና ሃይማኖት ዘንድ ቃል ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1÷1 ላይ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሄር ነበረ።" ይላል። ይህ አለም ሲሰራም በሃይማኖታዊ እሳቤው በቃል እንደተፈጠረ በመጽሀፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1÷3 "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች፡ አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ እግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር። እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃን ሆነ።" ይላል። ይህም ቃል በክርስትና እምነት ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ኃይለ ቃል እንደሆነ ይነገራል። እንደዚሁ ሁሉ የጠልሰም ህቡዕ ስሞችም ሃይል እንዳላቸውም ይታመናል። ይህ ዕውቀትና ኃይል በተመሳሳይ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደተወሰደ ማስረጃዎችን ይቀርባሉ።

እነዚህም የአምላክ ህቡዕ ስሞች፤ የመላዕክት ህቡዕ ስሞች፤ ለሰሎሞን የተሰጡ የአምላክ ህቡዕ ስሞች፤ እንዲሁም ሄኖክ በመጽሀፍ ቅዱስ የገለጻቸው ጥበቦችን እንመለከታለን።

የኢትዮጵያውያን የልዕለ ሰብ ተረኮች ውስጥ ስማቸው የሚነሳው አቡነ ተክለሐይማኖት ከጠልሰም ጋር የሚያያይዛቸው ታሪክ እንዳለ ከላይ የተጠቀሰው ጽሁፍ ያትታል። አቡነ ተክለ ሐይማኖት ከተለያዩ ነገሮች የሚከላከሉ ጸሎቶችን እና ጠልሰም ስዕሎችን የያዙ ጽሑፎችን ለንጉስ ይኩኖ አምላክ አዘጋጅተው እንደነበር Adrian እና Bogdan በመጣጥፋቸው "The first Ethiopian historical character to be mentioned in the legned having to do with talismans is the abuna Takla Hyamanot who, in the thirteenth century, is allieged to have compiled an anthology of protective prayers and talismans for the Emperor Yekuno Amlak" በማለት አስፍረዋል (Adrian P. and Bogdan B. ፣ 2012፣ 103)።

## 2.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ክፍል የጠልሰም እሳቤን ለማንጠሪያነት የሚውሉ ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳዮች ተዳሰዋል። እነዚህ ንድፈ ሐሳባዊ ጉዳዮች የጠልሰምን እውቀት፣ የመድሀኒትነት እሳቤ እና ፋይዳ ለማጤን የሚያስችሉ ሲሆኑ እነርሱም ተግባራዊ ወይም ጠቀሜታዊ (functionalism theory) እና ክዋኔ ተኮር (performance theory) ንድፈ ሐሳቦች ናቸው።

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን የጠልሰም ጥበብ ለመተንተን እነዚህ ንድፈ ሐሳባዊ ጉዳዮች ተመራጭ የሆኑት የጠልሰም የመድኃኒትነት ሥራ በርካታ ክዋኔያዊ ሂደቶችን የሚያልፍ ከመሆኑም ባሻገር የክዋኔ መሰረቱ ተግባር ነውና ጥበቡን ለማጥናት አመቺ ሆነው በመገኘታቸው ነው። ጠልሰም ለመድኃኒትነት በሚውልበት ወቅት የራሱ የሆነ የክዋኔ ሂደቶችን ያልፋል። በዚህ የክዋኔ ሂደት ህልውና ውስጥ አንድም ማህበረሰቡ፤ አንድም ደግሞ መድኃኒት ሰሪዎቹ የሚያገኟቸው ማህበራዊ፣ ስነ ልቡናዊ ብሎም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ጭምር ይኖራሉ። ይህ ሁኔታ በክዋኔ የተመላው ይህ ፎክሎራዊ ጥበብ ያለውን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያመለክታል። ጉዳዩን ከክዋኔ ተኮር እሳቤ አንጻር ብቻ እንኳ ብንቃኘው ከዋኝ እና በዚህ ክዋኔ ዙርያ የሚሽከረከሩና የክዋኔው አካል የሚሆኑ ማህበረሰቦች ይኖራሉ። ይህ ክዋኔ የሚካሔድበት ቦታ ይኖራል። ክዋኔውም የራሱ የሆነ ሂደት ብሎም ህግና ሥርዓትም ይኖረዋል። ለመድኃኒትነት የሚውል የጠልሰም ጥበብ እጅጉን ክዋኔያዊ ነው። ይህ ተከዋኝነቱም ከተግባር ወይም ከጠቀሜታ የራቀ አይደለም። ከመሰረቱ ስንነሳ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ በማህበረሰቡ ዘንድ ቅቡልነት አግኝቶ የሚከወነው አንዳች ማህበራዊ ዓላማን መነሻ በማድረግ ነው። ይህ ሁኔታ የፎክሎራዊ ጉዳዮችን ተከዋኝነት ከጠቀሜታዊነት ጋር የሚያስተሳስር ጉዳይ ነው። ስለሆነም የዚህ ምርምር ማስተንተኛ የሆኑት ክዋኔያዊ እና ተግባራዊ ንድፈ ሐሳቦችን ከዚህ በታች በተናጠል ለመቃኘት ተሞክሯል።

### **2.2.1.** ተግባራዊ ወይም ጠቀሜታዊ ንድፈ ሐሳብ

በፎክሎር ምርምሮች ውስጥ ማንኛውም ፎክሎራዊ ጉዳይ ለሚከውኑት ማህበረሰቦች ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል። ይህ ጠቀሜታም ከአንድ ጎን ብቻ የሚበየን አይደለም። አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ባህላዊ፣ ማህበራዊ አሊያም ስነ ልቡናዊ ጠቀሜታዎችን ይዞ የሚገኝበት ሁኔታ የተለመደ ነው። ይህን ጉዳይ (Green፣1997፣ 386) ጠቀሜታዊ ንድፈ ሐሳብ የማህበረሰቦችን ስነ ልቡና፣ በቡድኖች ውስጥ ያለ ማህበራዊ መዋቅርን እና በማህበራዊ ትስስር አማካይነት የሚፈጠርን ህሊናዊ ጋርዮሽ (conscience collective) ለመመርመር በማስቻሉ በማህበራዊ ሳይንስ ምርምሮች ውስጥ ሰፊ ድርሻ እንደሚሰጠው ያትታል። ይህ ማለት ግን ንድፈ ሐሳቡ ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች የራቀ ነዉ ማለት አይደለም። ሁሉም የትምህርት ዘርፎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ትኩረታቸዉ የሰዉ ልጅ አሊያም ማህበራዊ ትስስር ነዉ። ከዚህ አንጻር ንድፈ ሐሳቡ ቴክኖሎጂን ጨምሮ እንደ ስነ ሕይወት (biology)፣ ስነ ልቡና (psychology) እና ፍልስፍና (philosphy) ባሉ ትምህርቶች ዉስጥ ጭምር ትኩረት ይሰጠዋል።

እንደ Bronislaw Malinowski፣ Radcliffe Brown፣ Émile Durkheim እና Marcel Mauss ያሉ ምሁራንም ጠቀሜታዊ ንድፈ ሀሳብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በሚሰጡት ጠቀሜታ ላይ ማተኮሩን ያሳያሉ። አገላለጻቸው እና የሚያነሷቸው ነጥቦች አቀራረብ ይለያይ እንጂ የሁሉም ማጠንጠኛ ፎክሎር ለማህበረሰቡ

ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንደሚሰጥ ማሳየት ላይ ያተኩራል። ስለሆነም የዚህ ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳይ ዋና ዓላማ አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ለማህበረሰቡ ከሚኖረው ጥቅም ጋር እያይዞ መመልከት ላይ የተመሰረተ ነው።

Malinowski “The individual needs are satisfied by derived cultural and social institutions, whose functions are to satisfy those needs. In other words, every social institution has a need to satisfy, and so does every cultural item”. በማለት የእያንዳንዱ ሰው ግላዊ ፍላጎት እና እርካታ የባህላዊና ማህበራዊ ተቋማት ክፋይ መሆኑን እንደሚያስረዳ Bohannon and Glazer ይገልጻሉ (Bohannon and Glazer፣1973፣ 274)። ከዚህ ረገድ የ Malinowski የጠቀሜታዊ እሳቤ አብዝቶ በግለሰቦች ስነ ህይወታዊ እና ስነ ልቡናዊ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል። ይህን መሰረት በማድረግም የሰዎች ፍላጎት በሰባት ነጥቦች ላይ እንደሚመሰረት ያስረዳል። እነዚህ ሰባት ነጥቦች ምግብ፣ ደህንነት፣ ዝምድና፣ እንቅቃሴ፣ እድገት፣ መራባት እና የሰውነት ምቾት ናቸው (Green፣ 1997፣ 386)። Malinowski እነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች እርስ በእርስ የተሰናሰሉና አንዱ ከአንዱ እንደማይነጠል ይገልጻል። በህይወት ለመኖርና አቅምን ለመገንባት ምግብ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ባህልም እንደዚሁ ለሰው ልጆች አስፈላጊ ነገር መሆኑንም ያትታል። እነዚህ ግለሰባዊ ፍላጎቶች የሚጸኑትም ግለሰቦቹ በሚገኙበት ማህበራዊ መዋቅር ውስጥ ነው። ይህ ማለት በሌላ አነጋገር ማንኛውም ማህበራዊ ተቋም የግለሰቦችን ፍላጎት ለማሟላት እንደሚንቀሳቀስ ሁሉ በአንድ ተናጠላዊ ፎክሎራዊ ጉዳይ ውስጥ የሚከወኑ ባህሎችም ለባህሉ ባለቤቶች በግለሰብም ሆነ በጥቅል በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰጡት ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው።

ይህ የ Malinowski እሳቤ የተለያዩ ባህላዊ እምነቶችና እምነታዊ ስርዓቶቹን ተከትለው የሚመጡ ክዋኔዎች ለማህበረሰቡ ብሎም ለእያንዳንዱ ግለሰብ ስነ ህይወታዊ እና ስነ ልቡናዊ ጠቀሜታ እንደሚሰጡ ልብ ይሏል። እንደ ጠልሰም ያሉ ሀገር በቀል እውቀቶች አስከትለው የሚመጧቸው ስርዓቶች እና ክዋኔዎች ለማህበረሰቡ የሚኖራቸው ፋይዳ በቀላሉ ይህ ነው ተብሎ ሊነገር የሚችል አይደለም።

እንዲህ ዓይነት ፎክሎራዊ እዉቀቶች ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ ልቡናዊ ብሎም ሀገራዊ ጠቀሜታቸዉ ከፍተኛ ነዉ። እንደ William R. Bascom ገለጻ ፎክሎራዊ ሥርዓቶች ትምህርት ቀመስ ያልሆኑ ማህበረሰቦችን (nonliterate societies) ኢቀጥተኛ በሆነ መንገድ ከማስተማር ረገድ ጠቀሜታቸዉ የጎላ ነዉ (Sims and Stephens፣ 2005፣ 175)። እንደ ተረት፣ ምሳሌያዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገሮች፤ ሚቶች ብሎም እንቆቅልሾች ያሉ ቃላዊ ሥርዓቶች አጠቃላይ የተጥሮን ሁኔታ፤ የሰዎችን ስነ ልቡና፤ ብሎም ስለ ዓለም አፈጣጠር እና የሰዉ ልጆች አኗኗር በቀጥታም ሆነ በተለያዩ ወካይ ገጸባህርያት አማካይነት ያስተምራሉ።

ባህላዊ የሽንጎ እና የእርቅ ስርዓቶች፣ መድኃኒቶች፣ የሀዘን እና የሰርግ ብሎም የጨዋታ ሥርዓቶች ወዘተ. ማህበረሰቡን ከማቀራረብ፣ ከህመም ከመፈወስ፣ እያዝናኑ ህግና ሥርዓትን ከማስተማር ረገድ ሚናቸዉ ከፍተኛ ነዉ። ለዚህም ነዉ ኢቀጥተኛ የማስተማርያ መንገዶች መሆናቸውን Bascom የሚያነሳዉ። የ Malinowski የጠቀሜታዊ እሳቤ በግለሰቦች ላይ እንደሚያተኩር ሁሉ የ Bascom ትኩረት ደግሞ የፎክሎርን ጠቀሜታ ትምህርት ቀመስ ካልሆኑ ማህበረሰቦች አንጻር ወደማየት ያዘነብላል። ከዚህ አንጻር ቃላዊ የሆኑ ጉዳዮችን በመመርኮዝ ፎክሎር ተቀባይነት የሌላቸውን ባህሎች የሚያስወግድ፤ ባህልን መሰረት ያደረጉ ማንነቶችን የሚያስከብር እና ነባር ባህላዊ ልማዶችን የሚያጸና እንደሆነ በመጣጥፉ ያስረዳል (Bascom፣ 1954፣ 333-349)።

በማህበራዊ ሳይንሶች ውስጥ ጠቀሜታ ማህበራዊ ሥርዓትንና ልማድን ለመፍጠር የሚያስችል መሰረታዊ ጉዳይ ነው። (Green፣ 1997፣ 387)። ፎክሎርም እነዚህን ልማዶችና ሥርዓቶች የማጽናት ጠቀሜታ አለው። በማህበራዊ መዋቅር ሥርዓት ውስጥ የሚከወኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮችም ለግላዊ ማንነት መሰረት ናቸው።

ስለሆነም ፎክሎር የማህበረሰብን እንዲሁም የግለሰብ ማንነት ከመገንባት እና ባህልን፣ ልማድና ሥርዓትን ከማስጠበቅ አንጻር የሚወጣቸው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። ሆኖም እነዚህን ሐሳቦች የሚያስተናግደው ይህ የጠቀሜታዊነት እሳቤ እንደ ህጸፅ ወይም ጉድለት የሚነሱበት ሐሳቦችም አልጠፉም። የተግባራዊ እሳቤን ችግሮች ከፎክሎር አንጻር የሚቃኙት Sims እና Stephen ንድፈ ሐሳቡ ቡድኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ ተመሳሳይ ክዋኔን ብቻ እንደሚተገብሩ አድርጎ ማሰቡ አንድ ድክመት መሆኑን በማንሳት "ተግባራዊነት በራሱ ወግ አጥባቂ ነዉ" በማለት ይገልጹታል (Sims and Stephens፣ 2005፣ 176)። በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ የሚከወኑ ተግባራት ለዉጥ ሊካሄድባቸዉ ይችላል። ፎክሎር በባህሪዉ ለውጥን ያስተናግዳል። ስለዚህ ይህ ንድፈ ሐሳብ ተግባራት የማይቀየሩና ወጥ እንደሆኑ አድርጎ መመልከቱ ስህተት ነዉ የሚሉ ትችቶች ይነሱበታል። ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በውስጡ የሚነሱት እሳቤዎች ከክዋኔ ጋር የተያያዙ ናቸው። ስለሆነም ከዚህ በታች በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ከሚደረጉ ንድፈ ሐሳቦች ሌላኛው የሆነውን ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሐሳብ ምንነት እና በውስጡ የሚነሱ ሐሳቦችን ከዚህ በታች ላንሳ።

### 2.2.2. ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሐሳብ

ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሐሳብ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ከአውዳቸው ጋር በማዛነቅ የሚመረምር የንድፈ ሐሳብ ዓይነት ነው። “ክዋኔ ተሳትፎን፣ ስሜትን ማጉላት የሚጠይቅ እና ለምላሽ የሚጋብዝ ገላጭ ክንውን ወይም ተግባር ነው” (Sims and Stephens፣ 2005፣ 128)። ይህ ብያኔ በዚህ ንድፈ ሐሳብ መሰረትነት የሚቃኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የማህበረሰቡን ተሳትፎ በእጅጉ የሚፈልጉ መሆናቸውን ያመለክታል። ይህ አይነቱ ክዋኔም ከድምጸት ጀምሮ የአቀራረብ ሁኔታን ይመረምራል። ከዚህ አንጻር ንድፈ ሐሳቡ “ክዋኔ የሌለው ነገር ባዶ ነው” የሚል መነሻ አለው። በዚህ መነሻነትም በእያንዳንዳቸው ጉዳዮች (text) ውስጥ ያሉ ማህበረሰቦችን እንቅስቃሴ ያጠናል።

ይህ ንድፈ ሐሳብ በፎክሎር ጥናቶች ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል ሲጀምር በእንቅስቃሴ ወይም በአቅርቦት እና በስነዳ መካከል ያለውን ልዩነት አሊያም ክፍተት ግልጽ አድርጎ ማሳየት እንደቻለ “In its initial use in folklore scholarship, the term *performance* evoked the gap that exists between presentation and its documentation.” በማለት A.Green ያትታል (Green፣ 1997፣ 630)። ይህ እሳቤ ከመምጣቱ በፊት ፎክሎራዊ ጉዳዮች (በተለይም ቃላዊ ፎክሎሮች) ተሰብስበው ይሰነዱ ነበር እንጂ ጉዳዮቹ አስከትለዋቸው የሚመጡት ክዋኔዎች ትኩረት አይሰጣቸውም ነበር። ነገር ግን እንቅስቀሴዎች፣ የፊት ገጽታዎች እና ተግባራት የሚጠኑትን ጉዳዮች ምንነት ከማጉላትና ከማሳወቅ አንጻር ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑ እየታመነበት የመጣው ከዚህ ንድፈ ሀሳብ መመንጨት በኋላ ነው። ይህ ጽንሰ ሐሳብ እንደ አፈ-ታሪክ እና የጀግና ግጥሞች ባሉ ቃላዊ ጉዳዮች ላይ በመመስረት ክዋኔዎችን በመመርመሩ ቃላዊ ትርክቶች ከተግባር እና ተግባሩ ከተከወነበት አውድ ከተነጠሉ ህልውና እንደማይኖራቸው ማሳየት ጀመረ። ይህም ለፎክሎር ትምህርት ዘርፍ ጥናቶች አዲስ በር ከፈተ።

ከዚህ በተጨማሪም ክዋኔ ፎክሎር ከመሰብሰቡ በፊት በራሱ ወይም በተፈጥሮ ማህበራዊ አውድ ውስጥ የሚገኝ ክስተት መሆኑን Green Kenneth Goldstein ን በመጥቀስ ያብራራል (Green፣ 1997፣ 630)። ይህ ገለጻ ሁለት ጉዳዮችን እንድናጤን ያስችለናል። የመጀመርያው ይህ ንድፈ ሐሳብ ቃላዊ ፎክሎሮች በሚገባ መጠናት ከጀመሩ በኋላ ብቅ ይበል እንጂ ቀድሞ በጉዳዮቹ ውስጥ ክዋኔ አልነበረም ማለት እንዳልሆነና እንደዚህ ብሎ ማሰብም የተሳሳተ መሆኑን ያስረዳናል። ከዚህ ባሻገርም ማህበራዊ አውድ ለክዋኔ የጀርባ አጥንት መሆኑንም ያመለክታል። አንድ ክዋኔ ያለው ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲጠና ሊመረመሩ አሊያም በተዘዋዋሪ የክዋኔ መገለጫ ባህርያት የሆኑ ሁነቶች አሉ። ከእነዚህ መካከል አውድ እና ከዋኝ ይጠቀሳሉ።

> Performance is an expressive activity that requires participation, heightens our enjoyment of experience, and invites response. In order

> for a performance to "happen," a recognized setting must exist (we have to know a performance is taking place) and participants (performers and audience) must be present. The details of the setting and relationships between participants can be quite complex and fluid, but all participants understand that they are engaged in some kind of performance activity. (Sims and Stephens፣ 2005፣ 128-129)።

ከላይ የሰፈረው ሐሳብ ክዋኔ እና ክዋኔው የሚካሔድበት አውድ ብሎም ከዋኞች ያላቸውን ትስስር ያሳያል። ክዋኔ እንዲኖር ወይም እንዲከሰት የታወቀ መቼት ሊኖር ይገባል (ክዋኔ እየተካሔደ መሆኑን ልንገነዘብ ያስፈልጋል)። እንዲሁም ተሳታፊዎች (ከዋኞች እና ታዳሚዎች) የግድ ሊኖሩ ይገባል። በተሳታፊዎቹ እና በመቼቱ መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብ እና የማይጨበጥ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ሁሉም ከዋኞች አንዳች ክንውን ውስጥ እንደተሳተፉ ይረዳሉ። የቡደኑ አባላት እና ታዳሚዎች የአንድን ሰው ክዋኔ መረዳት እና መተርጎም ካልቻሉ የከዋኙ የሐሳብ አገላለጽ ስኬታማ አይደለም ማለት ነው ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የከዋኞች ጉዳይ አወዛጋቢ ሐሳቦች ይሰነዘሩበታል። በአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ውስጥ የሚሳተፉ ከዋኞች ሚናቸው ሊለያይ ይችላል። አንዳንዶች ከጉዳዩ ጋር ቀጥታ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ፤ አንዳንዶችም የተቀባይነት ሚና ሊኖራቸው ይችላል፤ አንዳንዶች ደግሞ ሚናቸው ከማጨብጨብ አሊያም ከመመልከት ያለፈ የታዳሚነት ተግባር ላይሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ ግን በክዋኔ ሂደት ውስጥ እነዚህ ዓይነት ከዋኞች ይኖሩ ዘንድ ግድ ነው። ይህ ካልሆነና ከዋኝ ከሌለ ክዋኔ የሚባል ጽንሰ ሐሳብም አይኖርም። ስለሆነም እነዚህን ሁሉ ጽንሰ ሐሳቦች የሚያቅፈው የክዋኔ ሂደት ሲጠና በርከት ያሉ ጥያቄያዊ ዓዞችን ይዞ ሊመጣ ይችላል። Finnegan፡-

> In what sense does it exist independently and what are its links with performance? How is the text of a particular story (to some extent known and shared—or is it?) related to its specific performances? What are the local concepts of this relationship—if any? Which if either is believed to have priority, and how far do such beliefs correspond to actual behaviour? (1977፣ 88)።

በማለት ክዋኔዎች እንዴት እና የት ይከወናሉ?፤ እንዴት ተዘጋጁ?፤ እንዴትስ ተደራጁ?፤ በስፍራው እነማን አሉ?፤ ምንስ ዓይነት ባህርይ ያሳያሉ?፤ ምንስ ይጠብቃሉ?፤ ከዋኞቹ አንድን ዘውግ እንዴት ይቀርባሉ?፤ ታዳሚውስ እንዴት ባለ ሁኔታ አጸፋዊ ምላሽን ይሰጣል?፤ ይህ ክዋኔ ከእለት ተእለት የኑሮ ፍሰትስ እንዴት ይለያል? የሚሉት ጥያቄዎች ለአንድ ክዋኔያዊ ምርምር የሚያገለግሉ ጥያቄዎች መሆናቸውን ታስረዳለች። እነዚህ ጥያቄዎች በሚገባ ምላሽ አገኙ ማለት ተመራማሪው የክወና ሒደቱን በሚገባ አጥንቷል ማለት ነው።

ክዋኔ ሀገራዊ ስሜትን እና በብሔር በመደብ አሊያም በጾታ የተሳሰረን ማህበራዊ ህብረተሰብ ለመፍጠር ከማስቻል አንጻር ሚናው ከፍተኛ ነው (Kapchan፣ 1995፣ 479)። በተለይ ክዋኔው ማህበረሰቦቹን በሚገባ ሊያቀራርብ እና ሊያዛምድ የሚችል ከሆነ ይህን ሚናውን በአግባቡ ይወጣል። በተለይም አንዳንድ ክዋኔዎች ጊዜንና ወቅትን ብሎም መቼትን ሳይጠብቁ በእለት ተእለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ የሚተገበሩ ስለሚሆኑ ክዋኔዎቹ ኑሯችን የሆናሉ። ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ክዋኔ ከድምጸት ብሎም ከፊት ገጽታ ሊጀምር ይችላል። ስለሆነም እነዚህን ሁነቶች የሚያካትቱ ክዋኔዎች እለት ተእለት በህይወታችን ውስጥ ሊደጋገሙ ይችላሉ። ለምሳሌ እንደ ተረት እና ምሳሌያዊ አነጋገር ያሉ የቃላዊ ፎክሎሮች ክዋኔ እጅግ ተለምዷዊና እለታዊ የሚሆኑበት አጋጣሚ ሰፊ ነው።

### 2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች እና መጣጥፎች ተዳሰዋል። ዳሰሳው የተቃኙት ጥናቶች እኔ ጥናት ጋር ባላቸው ቅርበት ቅደም ተከተል (ከቅርቡ ወደ ሩቁ) መሰረት ተዳሰዋል። የጠልሰም ጥበብ ጋር ባይገናኝም አጠቃላይ ጥበቡ በምን ደረጃ ላይ እንዳለና ምን ያህልስ በጥናቶች ተዳሷል የሚለውን ለመቃኘት ብሎም እውቀቱ በሀገራችን ከተሰጠው ትኩረት ጋር ለማነጻጸር ይጠቅም ዘንድ ጥናቶቹ ተዳሰዋል።

ከተዳሰሱት ጥናቶች መካከል “Ethiopian Abənnät Manuscripts Organizational Structure, Language Use and Orality” በሚል ርዕስ በ Gidena Mesfin Kebede የተካሄደው ጥናት አንዱ ነው። ይህ ጥናት እ.ኤ.አ በ 2017 በሀምቡርግ ዩኒቨርሲቲ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የቀረበ የዶክትሬት ማሟያ ጥናት ሲሆን ጥናቱ አጥኚው “አብነት” የሚል ስያሜ የሰጣቸውን የግዕዝ ሥነ ጽሑፎች መሰረት በማድረግ የተካሔደ ጥናት ነው። ጥናቱ የአስማትና የጥንቆላ ጽሁፎች ያላቸውን ቃላዊ መዋቅር፤ የቋንቋ አጠቃቀም እና ጥቅም ላይ ሲውሉ ያላቸውን ሁኔታ በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ጥናት የአስማቶችን መሠረታዊ አጠቃቀም፣ በሚታዩ አካላት (በጠልሰምና ባለ መነጽር ፊደላት አቀራረብ)፣ አስማቶቹ ሲጻፉ በሚኖራቸው ቀመር ላይ እና

በመሪ ግሶች ታግዘው ሲከወኑ በሚያስከትሉት የነባራዊ ሁኔታ ለውጥ ላይ ያተኮረ ምርምር አካሒዷል። በተጨማሪም የአስማት ወይም የጠልሰም አገልግሎት በኢትዮጵያ ያለውን ገጽታም አቅርቧል። ጥናቱ የንጽጽር መረጃ መተንተኛ ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን የብራና ጽሑፎቹን መዋቅር ተመሳስሎና ልዩነት መርምሯል።

ይህ የ Gidena Mesfin ጥናት ጥበበ ዳዊት ወይም የዳዊት መዝሙር በምስጢራዊነቱና በያዘው በርካታ ቃላት የጠልሰም ዕውቀትን በውስጡ አብዝቶ እንደያዘ ይገልጻል። በጥቅሉ Gidena ይህን ምርምር ለማካሔድ ንጽጽራዊ የትንታኔ ማስሔጃ ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን ንጽጽሩም በግዕዝ ሥነጽሑፎች እና በቃላዊ እውቀቶቹ መካከል ባለው ሁኔታ ላይ የተደረገ ነው። በዚህም ጥናቱ ቃላዊ እውቀቶቹ እጅግ ምሥጢራዊና ውስብስብ፤ ጽሑፎቹም “ተውላጥ” እና “አዛወር” የተሰኙ ምስጢራዊ የአጻጻፍ መንገድ እንዳላቸው በጥናቱ ማረጋገጥ ችሏል። ይህ የ Gidena የምርምር ጽሑፍ የጠልሰም ሥዕሎች ላይ ስለሰፈሩ ቃላዊ ኃሎች በማንሳትና በማተት ከእኔ ጽሑፍ ጋር የሚያዛምደው ነጥብ ቢኖርም የእኔ ምርምር አንድም ተተኳሪ የሆነ የጥናት አካላይ ሥፍራ በመምረጥ አንድም ደግሞ የጠልሰም ጥቡብ ቃላዊ ኃይል ሥግው የሚሆንበትን ክዋኔ በሥፋት በማየትና በጥናት አካሔድ ዘዴም ጭምር ይለያል። የ Gidena ምርምር ትኩረት ቋንቋ ላይ የእኔ ጥናት ትኩረት ደግሞ የጥበቡ አከዋወን እና ፋይዳ ላይ መሆኑ ደግሞ በጥናቶቹ መካከል ያለ ሰፊ ልዩነት ማሳያ ነው።

በዚህ ንዑስ ርእስ ስር ከተዳሰሱ ጽሁፎች መካከል ሌላኛዉ “In Search of the Debtera: An Intimate Narrative on Good and Evil in Ethiopia Today” በሚል ርዕስ በ Siena de Menovile በ 2018 የተሰራ መጣጥፍ ይገኛል። ይህ መጣጥፍ ስለደብተራ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ገጽታ የሚቃኝ ሲሆን በጠልሰም ስራ ውስጥ የዕውቀቱ ባለቤት የሆነው ደብተራ ላይ የተካሔደና የማህበረሰቡን አመለካከት ጭምር የሚያትት ጥናት ነው። ጥናቱ የደብተራነት ትምህርት ከአብያተክርስቲያናት ቢያገናኙትም በተናጠል በህክምናው ዘርፍ ብቻ ተሰማርተው የሚሰሩ ግለሰቦች እንዳሉና ደብተራዎች ከሚሰሯቸው ስራዎችም መካከል ጠልሰምና የተለያዩ ባህላዊ ህክምና ተጠቃሽ መሆናቸውን ያትታል። አጥኚው ከአዳማ አካባቢ በመነሳት ወደጎንደር ወዳሉት ደብተራዎች በማቅናት ያደረገው ጥናት በመግቢያው ላይ አቅርቧል።

“ሃይማኖትና ጥንቁልና በኢትዮጵያ” በሚል አቢይ ርዕስ “ደብተራና ዕውቀቱ” የሚል ርዕስን በማንሳት አቅርቧል። ጥናቱ ሃይማኖትና ጥንቁልና ሁለቱም ተመሳሳይ ገጽታ አላቸው ነገር ግን ልዩነቱ ሃይማኖት በግልጽ በማህበረሰቡ ተቀባይነት በማግኘት በግልጽ የሚከወን ሲሆን ጥንቁልና ግን በተገላቢጦሽ በድብቅ በግልሰቦች መከወኑ እንደሆነ ይገልጻል። የዕውቀቱ ረቂቅ ባህሪይ ግን ተመሳሳይ መሆኑንም አክሎ ያስረዳል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ ያተኮረው ይህ ጥናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን

በአንድ አምላክ ማመን ይገልጻል። የሀይማኖቱ አጀማመርና ሂደት ከቤተመንግስት ጋር ያለውን ትስስር ያብራራል።

የጠልሰም ጉዳይን መነሻ በማድረግ ከተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች መካከል በሶስተኛነት የቃኘሁት ደግሞ "A handbook of Ethiopian magic incantations and talisman art" በሚል ርዕስ በ Derrillo በ 2017 የተሰራውን ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ የኢትዮጵያ የጠልሰም ዕውቀትና ክታብ ክርስትና እምነት ተከታይ በሆኑት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተጠቃሽ ባህላዊ፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ ዕውቀት መሆኑ ስፍሯል። ከዚህጋር ተያይዞም ይህ ጥበብ ሰው ያልተረዳው ጥበብ ብዙም ያልተዳሰሰ ብሎም ያልተጠና የዕውቀት ዘርፍ መሆኑ ተገልጿል። ጥናቱ የኢትዮጵያ የጠልሰም ዕውቀትና ክታብን መነሻ በማድረግ የዳሰሳ ጥናት አድርጓል።

በዚህም የጠልሰምን አጠቃላይ መጠሪያውን መነሻ እና የጠልሰም ዕውቀት ተስተላልፎን እንዲሁም የጠልሰም አገልግሎትን ዘርዝሯል። የ Derrillo ጽሑፍ አጠቃላይ የኢትዮጵያን የጠልሰም ጥበብ (ምንነቱንና እውቀቱ ያለበትን ደረጃ) በወፍ በረር ቅኝት የዳሰሰ እንጂ የጠልሰምን ጥበብ በጥልቀት የቃኘ ጥናት አይደለም። ሆኖም ይህ ጽሁፍ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስሉት ብሎም የሚለዩት ነጥቦች አሉ። የእኔ ጥናት አንድም በአንድ አካባቢ ላይ በመወሰኑ አንድም ደግሞ ጠልሰምን ከመድኃኒትነት አገልግሎቱ አንጻር መቃኘት ላይ በማተኮሩ ከ Derrillo ምርምር ይለያል። ሆኖም የጠልሰምን ምንነት እና መነሻ ከማንሳት እና የተስተላልፎ ጉዳይን በመጠቆም ረገድ እንመሳሰላለን።

ሌላው ጥናታዊ ጽሑፍ ደግሞ "Ethiopian Magic Texts" በሚል ርዕስ በ Chernetsov (2005) የተሰራ ጥናት ሲሆን ጥናቱ በአጠቃላይ የኢትዮጵያውያን ጠልሰም ዕውቀት ላይ የተሰራ ምርምር ነው። ጥናቱ በጽሁፉ ውስጥ የተካተቱ ጠልሰሞችን መነሻ ዘመን በ 19 ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ መሆኑን ይጠቅሳል። በጠልሰም በተዘጋጁ ጥበቦች አማካይነት የክርስትና ሃይማኖት ውሃን ወደ ጸበል የመቀየር ኃይልና በጸበል መንፈስን የመዋጋት ሂደት እንደሚከወንበት ይገልጻል። እነዚህንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተወስደው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስያን ተቀባይነት ያገኙ መንፈሳዊ ዕውቀቶችንና ተቀባይነት ያላገኙትን ባህርያት ይገልጻል። በጠልሰም ስራ የመፈወስ ሂደት የሚድኑትንና በዕጽዋት የሚድኑ የመንፈስ በሽታዎችን በመለየት በተለይ እንደ የቡዳ መንፈስ፣ ዛር፣ ጋኔን፣ መጋኛ፣ ሾተላይና የመሳሰሉትን በጠልሰም የሚድኑ በሽታዎችን ተንትኗል። ለነዚህ በሽታዎች የሚሆነውን የጠልሰም አዘገጃጀት ሂደት፣ የቀለም አዘገጃጀት ሂደትንም ይገልጻል። ከዚህ ባሻገርም የጠልሰም አዘገጃጀት ምክንያት የጠልሰም አሰራር ምክንያትና የጠልሰም አጠቃቀምን ይገልጻል።

ይህ ጥናት በባህላዊ የጠልሰም አዘጋጆች መካከል የሚደረገውን የዕውቀት ሽግግርና ልውውጥ ገልጿል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በርካታ የጠልሰም የመባያ ጉዳዮች በልዩነት ተብራርተዋል። እነዚህም የጠባቂ መላእክት

የጠልሰም አሳሳል፤ የተለለያዩ የመስቀል ቅርጾችና ዓይነቶች፤ የአብያተ ክርስቲያናት አሳሳልና አገላለጽ፤ ክፉ መናፍስት ወይም በሽታዎችና መጥፎ ገዶች፤ የዘጠኙ ቅዱሳን፤ ባለስምንት ጫፍ የዳዊት ኮከብና ገጸ ሰብ፤ ተካተዋል። ከመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥም የተለያዩ ልዕለ ሰቦች ልክ እንደ ዳንኤል አናብስትን አፋቸውን እንዴት እንዳስዘጋና፤ የዳዊት ህቱም ኮከብና ምስጢራዊ ቃሎችና ገድሎቹ፤ ኢየሱስ ክርስቶስና የተአምራቱ ምስጢራት፤ የአራቱም አቅጣጫ መላዕክት፤ የሱስንዮስ ጸሎት ሃይሎችና የሰይጣን መታሰር ተብራርተዋል። ይህ ጥናት በተወሰነ መልኩ የመናፍስትና የበሽታ መፈወሻ ጠልሰሞችን በማንሳቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም የእኔ ጥናት በልዩነት የጻታ ወረዳን የጠልሰም የመድኃኒነት እውቀት የሚዳስስ መሆኑ በሁለቱ ጥናቶች መካከል ያለ ሰፊ ልዩነት ነው።

ፍካሬው እና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ የጠልሰምን ጥበብ በዓለም ላይ በበርካታ ሀገራት ማግኘት ተችሏል። ከዚህ አንጻር ምንም እንኳን የሀገራችንን የጠልሰም ጥበብ የሚመለከቱ ባይሆኑም የአጠናን ሂደትን ለመረዳት ያገለግላሉ በሚል እሳቤ ከዳሰስኳቸው ጥናቶች መካከል የ Witakowska ጥናት አንዱ ነው። ይህ ጥናት “illustrating charms: a syriac manuscript with magic drawings in the collection” በሚል ርዕስ በ UPPSALA ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ በ 2008 የተካሔደ ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። ይህ የምርምር ሥራ የሶርያ ጥንታዊ ጽሁፎችና ጠልሰሞች ላይ አተኩሯል። በእንግሊዝ ቤተመጻህፍት የሚገኙ የሶርያ ጠልሰሞችን በማብራራት ላይ ያተኮረው ጥናቱ “The Book of Guidance,” በሚል ርዕስ የተከማቸውን ጠልሰም በጥቅሉ የሚይዙት የጸሎት ወይም ኃይል ያላቸው ቃሎች፤ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች፤ ተከታታይና በአንድ ጊዜ የሚባሉ ቃሎች እና ልመናዎች እንደሆኑም አትቷል። እነዚህም ሰዎችን ከተለያዩ መጥፎ መንፈሶች ይታደጋሉ ተብሎ ይታመንባቸዋል። ይህ ጽሁፍ አስራ ስምንት ጠልሰሞችን በዋቢነት በመያዝ ለእያንንንዱ መግለጫና ማብራሪያ ይሰጣል። ይህም የሚጀምረው የቅዱስ ዮሐንስን የወንጌል ክፍሎችና አራቱ ወንጌላውያንን የያዘ የጠልሰም ስራን በማብራራት ይጀምራል። አራቱ ወንጌላውያንን በጠልሰማዊ ስራ ያቀረበ ሲሆን የወንጌል ክፍል ጥቅሶችን በአንድ በኩል በሚገኘው ክፍል አስፍሯል። በዚህ መልክ የአስራ ስምንት ጠልሰሞችን ትንተና ሰርቷል።

ከነዚህም ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ ትንተና የተካሔደበት የቅዱስ ጊዮርጊስ ጠልሰም ማብራሪያ ሲሆን በዚህም ውስጥ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰባቴ ሞቶ ሰባቴ የተነሳበትን ጽናትና የቅርጽ መቀየር ማለትም መፈጨት፣ መቃጠልና ሌሎችን መቋቋም የቻለበትን ሁኔታ በሁለተኛው ክፍል ላይ ያብራራል። በሶስተኛው ክፍል ደግሞ የቅዱስ ገብርኤል ጠልሰምን እንዲሁም መሪ ወይም ንጉስ በሰረገላ ላይ ሆኖ በሚታይበት ጊዜ የሚሰጠውን ግርማ ከሎሌዎቹ ጋር የያዘ ጠልሰም ማብራሪያ ይዟል። በአራተኛ ደረጃ የተለያዩ መሳሪያዎችንና ከነዚህ ጋር የሚገናኙ ቃሎችን ማብራሪያ ይይዛል። በዚህ መልክ ጥናቱ አስራ ስምንት ጠልሰሞችን ፍካሬ በስፋት አብራርቷል። በአጠቃላይ ጠልሰሞቹ የሰው፤ የተለያዩ እንስሳት (አንበሳ፣ ውሻ፣ እባብ እና ፈረስ) የመሳስሉትን

ይይዛል። ከዚህም በተጨማሪ የመገልገያ መሳሪያዎችንም ጭምር ይይዛሉ። ከዚህ ባለፈ ለፈውስና ህክምና የተሰሩ ጠልስሞች ደግሞ በንጉስ ወይም በመሪ ግርማና ስልጣንን የሚሰጥ፤ የሰሎሞን ማህተምና የተለያዩ ክፉ መንፈሶችን የሚከላከሉ ጠልሰሞችን ማብራሪያ ይዟል። ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የጠልሰም እሳቤን በማንሳቱና ሥዕላቱ ያላቸውን ኃይል እና ፍካሬ ያሰፈረበት መንገድ ከእኔ ጥናታዊ ጽሑፍ ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም የተጠኑት ጠልሰሞች አይነትና መገኛ መለያየት ብሎም የእኔ ምርምር አብዝቶ የጠልሰም የመድኃኒትነት እሳቤ ላይ ማተኮሩ በሁለቱ ሥራዎች መካከል ያለ ሰፊ ልዩነት ነው።

ሌላው የሚዳሰሰው ጥናት በ Adrian እና Bogdan ጥናት ሲሆን ጥናቱ “An Ethiopian Magical Manuscript at the University Library of Cluj, Romania (BCU, MS 6” በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ 2012 በቦስተን ዩኒቨርሲቲ የተሰራ ጥናት ነው። የዚህ ምርምር አዘጋጆች የሆኑት Adrian እና Bogdan “Cluj” ዩኒቨርሲቲ በርካታ የቀደምት ስልጣኔ መጻሕፍት ክምችት እንዳለው በመጥቀስ ከነዚህ ውስጥም አብዛኞቹ የኢትዮጵያ የጠልሰም ሥራዎች መሆናቸውን ይገልጻሉ። እነዚህ የጠልሰም ስራ ስብስቦች MS 681 as a “Coptic manuscript,” በሚል የካርድ ካታሎግ ቁጥር በቤተ መጻሕፍቱ እንደተሰደረ ይገልጻል። ይህ መጽሐፍ ዳጎስ ያለ የገጽ ብዛት አለው። ሆኖም መጠኑ ከተለመዱ የመጻህፍት መጠን የተለየ ቅርጽና ገጽ ብዛት መጠን እንዳለው ያስረዳል። ይህም በ (75 x 70 mm, text: 50 x 55 mm) መጠን ላይ ይገኛል። ይህም በባህላዊ የመጻህፍት ዓይነቶች አነስተኛው መጠን እንደሆነ ይታመናል። በስኩዌር መጠን የሚሰሩ መጻህፍቶችና ጠልሰሞች ከ 18 ኛው ክፍለዘመን በኋላ እየተመናመኑ መጥተዋል። ነገር ግን ከ 18 ኛው ክፍለዘመን በፊት በሰፊው የተለመዱ ነበሩ። ይህም የጠልሰሞቹ ስብስብ ከ 18 ኛው ክፍለዘመን በፊት የተሰሩ ውጤቶች መሆናቸውን መገንዘብ ያስችላል። የመጀመሪያው በፎቶግራፍ ከቀረቡት የጠልሰም ክፍሎች ውስጥ የተለመደውን የኢትዮጵያ በአምድ ከፍሎ የመጻህፍቱን ዕውቀት ያብራራል። በዚህም ሁለት ክፍል አምድ በአስራ ሰባት መስመር መሆኑን ይገልጻል።

ከዚህ ባሻገር የጠልሰም መጽሐፉን የሽፋን ክፍል ይገልጻል። ይህም የቀደመ በ 16 ኛውና 18 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መካከል ያለ ሽፋን እውቀት ነው። የድጉሱን የቆዳ ኮሮጆና ማንገቻውን ያቀርባል። በስተመጨረሻም የጠልሰም ክፍል የዳዊት ኮከብና የተለያዩ የጠልሰሙ ክፍል ጽሁፎችን በመግለጽ ያብራራል።

በ (Heidi Cutts, Lynne Harrison, Catherine Higgitt and Pippa Cruickshank) በ 2010 የኢትዮጵያ በጨርቅ ላይ የተሳለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሚያሳይ ስዕል በ 1893 ዓ.ም ለብሪቲሽ ሙዚየም ገቢ ተደርጎ ነበር። ይህንን ስዕልና በርካታ በብሪቲሽ ሙዚየም ውስጥ የሚገኙ በርካታ ቁጥር ያላቸውን በኤግዚቢሽን መልክ ለማቅረብ በርካታ ምሁራንን በበይነ ዲስፕሊናዊ አቀራረብ ለማሳየት ከእንግሊዝና ከኢትዮጵያ ለማሳተፍ ተችሎ ነበር። ይህም በተፈጥሮው ለብዙ አመታት እንዲቆይ፤ በስዕሉ ላይ

ያሉ ቀለሞችን ቃሎችንና ፊደሎችና እንዲሁም ምልክቶችን በተገቢው ተርጉሞ ለማቅረብ ታስቦ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በኤግዚብሽኑ ላይ የቀረቡት ስዕሎች በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተለመዱ ስዕሎች ናቸው። ይህም ከኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም አዲስ አበባ ከሚገኘው በሚበልጥ ቁጥር ስብስቦችን ከያዘው ብሪቲሽ ሙዚየም የሚገኙትን ኦርጂናል የጥንት ስዕሎችን ስብስብ ስራዎችን ብቻ ማቅረብ ነው። በስዕሉ ላይ የአቡነ ሰላማ ስዕል፤ የአፄ ቴዎድሮስን መቀባትና ንግስና ስርዓት ሂደቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች ቀርበዋል። ስዕሎቹ ገሚሶቹ በጦርነት የተወሰዱ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ በጅምር የቀሩ ናቸው። እነዚህ ስዕሎች ከጠልሰም የአሳሳል ጥበብ ጋር በሚዛመድ አቀራረብ ተሰርተዋል።

ከዚህ ባለፈ በዚህ ንዑስ ርእስ ስር የተዳሰሰው  ተዛማጅ ጥናት የ Nosnitsin, Denis ጥናት ነው።  ይህ ጥናት እ.ኤ.አ በ 2015  “Essays in Ethiopian Manuscript studies.” በሚል ርዕስ የተካሔደ ነው። ጥናቱ በትግራይ ክልል በሚገኙ አብያተክርስቲያናት ውስጥ በመዘዋወር የአቡነ ተክለሃይማኖትን የተለያዩ ስዕሎችን ባህሪይ፤ የተሰሩበትን ዘመን፤ የተሰሩበትን አካባቢ፤ የመጽሀፍቱን ዕድሜና መነሻ ስፍራ፤ ከተሰሩበት አንጻር ያለውን ባህላዊ ዳራ ለመቃኘት ይሞክራል። በአርሮ ተክለሃይማኖት በአዲግራት የሚገኝ ቤተክርስትያን በያዛቸው የቀደምት መጻህፍት ቁጥር ዋጋ ሊሰጣቸው የሚገቡ ታሪካዊ መጻህፍትን በውስጡ ይዟል። በመሆኑም ይህ ጽሁፍ የተለያዩ መጻሕፍቶችን በዘውግ በዘውጋቸው ከፋፍሎ ያቀርባል። በመሆኑም በመጀመሪያው ክፍል የዘውግ አንድ ክፍል ያደረገው የወንጌል ክፍሎች የያዙትን ነው። በ 15 ኛው ክፍለዘመን መጨረሻና በ 16 ኛው ክፍል መባቻ ያሉትን ያቀርባል። በሁለተኛው ክፍል ዘውግ ደግሞ ከ 17 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 18 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያሉትን አቅርቧል። በሶስተኛው ክፍልም ከ 19 ኛው መቶ ክፍሎ ዘመን እስከ 1831 ድረስ ያለውን ያቀርባል። በአራተኛው ክፍል ደግሞ የ 19 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስራዎችን አቅርቧል። በአምስተኛው ክፍል ደግሞ የመጀመሪያው 19 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ስዕሎችን አቅርቧል። በስድሰትኛው ክፍል ደግሞ ከ 1872 በኋላ ያሉትን ያካትታል። በስተመጨረሻም ማጠቃለያ ያቀርባል። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ስዕሎቹ የጋራ ባህሪይ እንዳላቸው በዚህም ስብስቦቹ በገቡበት የዘመን ቅደም ተከተል መክፈል እንደሚቻል ይገልጻል።

ይህ ሥራ መንፈሳዊ ሥዕል ላይ ከማተኮር ረገድ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም አንድም የጠልሰምን ጥበብ ብቻውን ነጥሎ ምስጢራዊ ሁነቶችን በመፈከር፤ አንድም በተለየ አካባቢ በማተኮር፤ አንድም ደግሞ የጠልሰምን የመድኃኒትነት አከዋወን ሂደት እና ፋይዳ ከመተንተን አንጻር የእኔ ጥናት ይለያል።

የጠልሰም ዕውቀት በእስልምናውም ዘንድም እንደሚገኝ ከሚያሳዩ ጥናቶች መካከል ደግሞ እ.ኤ.አ በ 2011 የተካሔደው የ L. D. Graham ጥናት ይጠቀሳል። ይህ ጥናት “In Islamic Talismans, Repeat-Letter Ciphers Representing the “Greatest Name” Relate to an Early Prototype of the

Seven Seals and may Link the Seals with the Pleiades" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ነው። ጽሁፉ በእስልምና ሃይማኖት እምነት ያለውን በጽሁፋዊ መልክ የሚገለጡ የፈጣሪ መጠሪያን በሰባት የተለያዩ ተከታታይ ስሞች ይገልጻሉ። በእስላማዊ አቀራረብ ያለውን የፈጣሪ መጠሪያን በራሱ ቅርጽና አቀራረብ በጠልሰሞች መጠቀሙ የተለየ ባህሪው ነው። እነዚህ ቅርጾችና መጠኖች የፈጣሪን መጠሪያ ታላቅነት የሚገልጹ ናቸው። በዚህ ጽሁፍ ከ 12 ኛው መቶ ክፍለዘመን ጀምሮ የተሰሩ ጠልሰሞች ዓይነት ተመሳሳይነት ያላቸው ጠልሰሞች በእስላምዊ ጠልሰም ዕውቀት ውስጥ የቀጠሉ እውቀቶችን ተመራማሪው ለመገንዘብ እንደቻለ ያረጋግጣል። እነዚህ የእስላምዊ ጠልሰም ግለወጥነት ያላቸው ጠልሰሞች በ 21 ኛው ክፍለዘመን ውስጥ በሚቀርቡ የጠልሰም ስራዎችም ውስጥ በጉልህ ተጽእኖዎቻቸው ቀጥሎ መታየቱን ይገልጽበታል። እነዚህ መግለጫዎች ደግሞ የፈጣሪ ወይም የልእለተፈጥሮ ስም ናቸው።

በጋራ ከሚኖራቸው ነጥብ የክርስትና ሃይማኖት ተዛምዶዎች መካከል የሰሎሞን ማህተም ተብሎ በጠልሰም ዐዋቂዎች የሚጠራው ምልክት ወይም የፈጣሪ መጠርያ ነው። ይህ ህቱም ትዕምርት በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በሰባቱ ህትማን ወይም ሰባቱ ምስጢራት በሚል ይቀርባሉ።

ይህ የጠልሰምን ዕውቀት በመካከለኛው ምስራቅ ያለውን የአብራማዊ እምነቶች[1] ተዛምዶን ማለትም የአይሁድ፤ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶችን ተዛምዶና ትስስር እንዲሁም የጠልሰም ዕውቀት መሰረታዊ መነሻ የጋራ መነሻ ነጥብ በመሆን መጠቀስ ይችላል። ይህ ጥናት ምሥጢራዊ ፍካሬን በሚሻው የጠልሰም ጥበብ ላይ ከማተኮር ረገድ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም የተጠኑበት ሀገርና ሥፍራ፣ ብሎም ሃይማኖታዊ እሳቤዎች መለያየት በጥናቶቹ መካከል ያለ ሰፊ ልዩነት ነው።

በእስልምናው ጠልሰም ዕውቀት ውስጥ ሁለተኛው የተቃኘ ተዛማጅ ጽሁፍ ደግሞ በጠልሰሞች ላይ ያተኮረ የኮንፈረንስ ውይይት የተካሄደበትን አጠቃሎ ወይም አብስትራክት ስብሶቦችን የያዘ እትም ነው። በዚህም በ Marcella Garcia probert and Hayat Ahlili ተጽፎ "Amulets and Telsmans in the Muslim world" በሚል ርዕስ በ 2016 በመጽሔት ታትሟል። በኮንፈረንሱ ስድስት የተለያዩ ውይይቶች የቀረቡ ሲሆን በነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች የቀረቡ የሁለቱን አጠቃሎዎች እንደሚከተለው ቃኝቻለሁ።

ፓናል አንድ፦ ይህን መወያያ ያቀረበው Ursula Bsees የተባለ አጥኚ ሲሆን ርዕሱም "Characteristics of amulets and how to work with them (with special regard to the Vienna Papyrus Collection)" ይሰኛል። ይህ የምርምር ሥራም የክታብንና የጠልሰምን ብያኔ ከመግለጽ የሚነሳ ሲሆን በዚህም

[1] የአብራ(ሃ)ማዊ እምነት መነሻው በአብራሃም ልጆች መሰረት ላይ ሲሆን በአካባቢም በመካከለኛው ምስራቅ ነው። ይህ የሰማዊ ስልጣኔ ክፍልን የሚይዘው የስም ልጆችን የዘር ሀረግ ተከትሎ የዛሬውን ገናና ሀይማኖቶች መሰረት የሆነ ነው። በመሆኑም በአካባቢያው መነሻ ተዛዶና በሃይማኖትና መንፈሳዊነት ረቂቅ እሳቤ ፍልስፍና ሰፊውን ዓለም በበላይነት ተቅባይነት አግኝቶ ላለፉት በርካታ ክፍለዘመኖችን ቆይቷል። (ፕሮፌሰር መስፊን ወልደማሪያምና ሪቻርድ ፓንክሬስትን ተመልከት)።

የአስማታዊ ኃይል ያላቸው ቃሎች ከከታቦች የሚለዩበትን መንገድ ለማሳየት ይሞክራል። በተጨማሪም የጠልሰም ልዩ ልዩ ይዘቶችን ባህሪዎችን፤ የጽሁፍና የቋንቋ አቀራረቦችን ያብራራል። በዚህም በህይወት ውስጥ ያላቸውን መቸት በመግለጽ በእስላማዊ የጠልሰም ዕውቀት ያለውን መገለጫ በቁርዓን ቃሎችና ከቁርዓን ቃሎች ውጪ በስዕላዊ አቀራረብ የሚገለጹበትን አቀራረብ ያብራራል። ለነዚህም ማስረጃ የሚሆኑ ከአውስትሪያ በተመጻህፍት ያገኘውን ጠልሰሞችን ማስረጃ ያቀርባል።

ፓናል ሁለት፡- ይህ ሁለተኛ መወያያ “Baha Jubeh the Tawfiq Canaan Collection of Palestinian Amulets” በሚል ርዕስ የቀረበበት አጠቃሎ ሲሆን በውስጡም የፍልስጤም ጠልሰምን ከእስልምና እምነት አቀራረብ አንጻር ይቃኛል። በመሆኑም ጠልሰም በበርካታ ሰዎች ዘንድ የሚሰጠውን አመለካከትና ኋላ ቀር እውቀት ነው የሚለውን በመግለጽ ይጀምራል። አቅራቢው የራሱን አመለካከት ምልኪ አለመሆናቸውን፤ ኋላ ቀር ቁሶች አለመሆናቸውንና በሰዎች ስነልቡና ላይ ለፈውስ ብቻ ከእምነት አንጻር የሚቀርቡ ቀላል የስነልቡና ማከሚያ ቁሶች ብቻ አይደሉም በማለት ይሞግታል። በመሆኑም የፍልስጤም የእስልምና እምነት የጠልሰም እውቀቶችን ስብስቦች በማቅረብ በእውቀት በመመርመር በርካታ የፍልስጤም ታሪክ፤ ጥበብ፤ ዕውቀትና ሙያዎችን እንዲሁም በርካታ ህቡዕ ምስጢራዊ የፍልስጤም እውነታዎችን ለመመርመር ለፈለገ አጋዥ ናቸው በማለት ያቀርባል።

# ምዕራፍ ሶስት

## አካባቢያዊ ዳራ

ይህ ምዕራፍ የምርምር ሥራው ትኩረት የሆነችው ፃታ ወረዳን የሚመለከቱ መረጃዎች የሰፈሩበት ነው። ስለሆነም በዚህ ምዕራፍ የፃታ ወረዳን አሰያየም ታሪክ፣ መልክዓምድራዊ አቀማመጥ፣ የኢኮኖሚ ሁናቴ፣ አካባቢያዊ ስያሜ እና የህዝብ አሰፋፈር፣ የማህበረሰቡን ቋንቋና ሀይማኖት እንዲሁም ታሪካዊ ስፍራዎች የሚመለከቱ መረጃዎች ቀርበዋል።

### 3.1 የፃታ ወረዳ አካባቢያዊ ስያሜ እና የህዝብ አሰፋፈር

የዚህ ጥናት ተተኳሪ ሥፍራ የሆነችው "ፃታ" ወረዳ በዋግ ኽምራ ብሔረሰብ ዞን ውስጥ ከሚገኙ 7 ወረዳዎች መካከል አንዷ ናት። ፃታ ወረዳ ከሰቆጣ ከተማ በስተሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ አርባ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ቦታ ስትሆን ስያሜዋን ያገኘችው በአካባቢው ከነበረ የማኅበረሰብ አስተዳዳሪ የሥራ መመሪያ ጋር በተገናኘ እንደሆነ ነዋሪዎቹ ያስረዳሉ። ይህም በአንድ ወቅት የነበረ የአካባቢው አስተዳዳሪ ሕዝቡን ሰብስቦ ለማወያየት ይፈልግና በአጠገቡ የነበረውን አንድ አርሶ አደር ግለሰብ ጠርቶ "ነገ በዚህ ቦታ ትልቅ የሕዝብ ስብሰባ ስለሚካሄድ ሂድና ለሕዝቡ ስብሰባ ተጠርታችኋል እያልክ ንገራቸው" አለው ይባላል። ግለሰቡም በየሰፈሩ እየዞረ ለነዋሪዎቹ መልዕክቱን ያደርሳል።

የአካባቢው ሕዝብም ስብሰባው ስለምን ጉዳይ እንደሆነ ስላልተገለጠ "ይህ መሪ ወይም የሕዝብ አስተዳዳሪ የጠራን ለምን ይሆን?" የሚለውን ጥያቄ እያብሰለሰሉ ሲጓዙ፣ ከመካከላቸው አንድ ሰው በአካባቢው ቋንቋ "አንቺን ደኘሽን ኣፃተ የኘ አቐውድ" አለ ይባላል። ትርጓሜውም "ይህ ዳኛ (መሪ) ለሥራ ሊልከን ነው የሚሆነው" ማለት ነው። "ኣፃተ" ማለት ልትልክ ወይም ትእዛዝ ልትሰጥ ማለት ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ቦታው "ኣፃተ" የሚለውን ሙሉ ትርጉም የሚሰጥ ቃል በመተው "ፃተ" በሚለው ጉርድ ቃልና ሙሉ ትርጉም በማይሰጠው መጠሪያ ይጠራ ጀመር። (አቶ በላይ ገ/ኪዳን፣ የጻታ ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ቢሮ ኃላፊ፣ ግንቦት 7 2013)።

## 3.2. የፃታ ወረዳ መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የኢኮኖሚ ሁኔታ

የፃታ ወረዳ በሰሜንና በምስራቅ አቅጣጫ የትግራይ ክልል የሚያዋስኑት ሲሆን ከባህር ወለል በላይ 1145 ሜትር ዝቅተኛና 3500 ሜትር ከፍተኛ ቦታ ላይ ይገኛል። ወረዳው 44974.16 ሄክታር ስፋት ያለው ሲሆን ከጠቅላላ ቆዳ ስፋቱ ሜዳማ 20.8%፣ ወጣ ገባ 38.35%፣ ተራራማ 30.38%፣ ሸለቆማ 10.47% ይሸፍናል። የአካባቢው የአየር ንብረት የቆላማ የወይና ደጋነትና የደጋነት ሁኔታ ያለው ሲሆን ይህም በአማካይ ሲቀመጥ ቆላማ 30%፣ ወይና ደጋ 70% እና ደጋ 10% ነው። የአካባቢው የዝናብ ስርጭት ዝቅተኛው 150 ሚ.ሜ ከፍተኛው ደግሞ 700 ሚ.ሜ ሲሆን የሙቀት መጠኑ ደግሞ ዝቅተኛው $15^{0}$C ከፍተኛው $42^{0}$C እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ (ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ሪፖረት፣2011)። በወረዳው ካለው ጠቅላላ የቆዳ ስፋት ውስጥ 8838.65 ሄክታር መሬት የሚታረስ ሲኖረው እንደ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ተልባ፣ ማሽላ፣ ሱፍ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ምስርና ሽንብራ ያሉ ሰብሎች ይመረታሉ።

## 3.3 የፃታ ወረዳ ማህበረሰብ ቋንቋና ሀይማኖት

በ 2013 ዓ.ም. በነበረው መረጃ መሰረት የፃታ ወረዳ ጠቅላላ ህዝብ ብዛት 52,934 ሲሆን ወንድ 23,432 (ሃያ ሁለት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ሁለት) ሴት 29,502 (ሃያ ዘጠን ሺህ አምስት መቶ ሁለት) ናቸው። ሁሉም ማለትም መቶ ፐርሰንት የኦርቶዶክስ ዕምነት አማኝ ናቸው (አቶ ብርሃን አማረ፣ የፃታ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ግንቦት 9/2013)። ።

በወረዳው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩ ሲሆን ከቋንቋ ስብጥር አኳያ ሲታይ አገውኛ፣ አማርኛና ትግርኛ ቋንቋዎች ይነገራሉ። አገውኛ 100%፣ አማርኛ 30%. ትግርኛ ደግሞ 30% ተናጋሪ ማኅበረሰብ ያሉበት አካባቢ ሲሆን ሦስቱንም ቋንቋዎች የሚናገሩ ሰዎችም ይገኙበታል (አቶ ብርሃን አማረ፣ የፃታ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ግንቦት 9/2013)።

## 3.4 የቱሪዝም ሀብቶች በፃታ

በፃታ በርካታ ታሪካዊ፣ መንፈሳዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶችና መስህቦች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ቅርሶች እና መስህቦች የማህበረሰቡን ሥነ ልቡና፣ አኗኗር እና ሥርዓት የሚያሳዩ ናቸው። ዋና ዋና የሚባሉት ቅርሶችና መስህቦችም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ሰፍረዋል።

### 3.4.1 ታሪካዊ መስህቦች

በፃታ ወረዳ በርካታ ታሪካዊ መስህቦች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ "የዋግሹም ቀየ ውሃ" እና "ዳምትኩኑ" ተየተባሉት ተጠቃሽ ናቸው። "የዋግሹም ቀየ ውሃ" በመባል የሚጠራው ቦታ ከሰቆጣ ከተማ በስተሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ 42 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከምትገኘውና "ፃተ" እየተባለች ከምትጠራው የገጠር ከተማ በስተ ምሥራቅ በኩል የሚገኝ ውሃማ ቦታ ነው።

ስያሜውን ያገኘው በዋግሹሞቹ ዘመን እንደሆነ ይነገራል። የተሰየመበት ምክንያት የአካባቢው ነዋሪዎች እንደገለጹት ቀደም ባለው ዘመን በዋግና አካባቢዋ ኃይለኛ ድርቅ ተከሥቶ ነበር። በዚህ ጊዜ በአካባቢው የሚገኙት ትላልቅ ወንዞች ፅራር (ጥራሬ)፣ ጅልወ (ዙሪያ)፣ ጊብየ (ንሣ በለው) እነዚህ ሁሉ ደርቀው የሚጠጣ ውሃ ጠፍቶ እንደነበር ነዋሪዎቹ ያስረዳሉ (አቶ ቢተው ብሩ፣ ግንቦት 6/2013)።

በዚህ ቦታ ያለው ውሃ ግን በጣም ኃይለኛ የውሃ ምንጭ ያለውና በዚህ ወቅት ደርቆ ነበር የተባለበት ታሪክ ያልተሰማበት ውሃ ነው። በመሆኑም በዚያ የድርቅ ዘመን በሰቆጣ ከተማ የሚጠጣ ውሃ ጠፍቶ የከተማውና የአካባቢው ሰው ሁሉ ወደዚህ ቦታ እየመጣና ውሃውን እየቀዳ በአህያና በበቅሎ እያጓጓዘ በወቅቱ የተከሠተው ድርቅ እስኪያልፍ ተጠቅመዋል ይላሉ (ከንድዬ ጫኔ፣ የአካባቢው ነዋሪ፣ ግንቦት 8/2013)።

በዚህ ቦታ ያለው የውሃ ምንጭ ተፈጥሮ ለአካባቢው የለገሰችው በየትኛውም ወቅት የማይደርቅ ቢሆንም፣ በ 1991 ዓ.ም MSF በሚባል የውጭ ድርጅት እርዳታ በዘመናዊ መልክ እንደተሠራ የአካባቢው ነዋሪዎች ያስረዳሉ። ይህ በጎ አድራጊ ድርጅት ከመንግሥትና ከዞኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ሥራውን ለመሥራት ሲጀምር ከአካባቢው ማኅበረሰብ የተወሰነው ክፍል "ከእግዜር የተሰጠን ተፈጥሯዊ ወንዛችን ሃይማኖቱ ምን እንደሆነ ባልታወቀ አካል አይነካም (አይሰራም)" በሚል ተቃውመው እንደነበር መገንዘብ ተችሏል (አቶ ጌታወይ ሽመይ፣ የጻታ ወረዳ ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ ግንቦት 5/2013)።

ነዋሪዎቹ እንደተናገሩት በዚህ ቦታ በየዓመቱ የአካባቢው ታቦታት ወርደው በዓለ ጥምቀትን የሚያከብሩበት፣ ከሃይማኖት ጋር በተቆራኘ ሁኔታ ለቦታው ልዩ ግምት የሚሰጠው በመሆኑ እንደሆነም ይነገራል (ከንድዬ ጫኔ፣ የአካባቢው ነዋሪ፣ ግንቦት 8/2013)።

በዚህ አጋጣሚ ውሃው በዘመናዊ መልክ እንዳይሠራ ኅብረተሰቡን ለአድማ አነሳስታችኋል በሚል ሰበብ በቀበሌው አስተዳደር ለተወሰነ ጊዜ የታሠሩ ሰዎችም እንደነበሩ ተገልጿል። ይሁን እንጂ ጉዳዩ የሚመለከታቸውና የአካባቢው ነዋሪዎች ደጋግመው በመወያየታቸው ከመግባባት ላይ ደርሰው፤ ውሃው በዘመናዊ መልክ ተሰርቶ፤ በአሁኑ ሰዓት ለአካባቢው ኅብረተሰብ የተሻለ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በአንድ ወቅት በዋግና አካባቢዋ ተከስቶ በነበረው የውሃ ድርቅ ምክንያት በዚህ ቦታ ያለው ውሃ ለሰው መጠጥ ከመሆኑ ባለፈ የዋግሹሞቹ ልብስም በበቅሎና በአህያ ተጭኖ እየመጣ በዚህ ቦታ ይታጠብ ነበርና በዚህ ምክንያት ሽማርወአቍ (የዋግሹሞች ቀየ ውሃ) ተባለ።

ለዚህ ታሪካዊ ቦታ የሚጠቀሰው የቅርብ ጊዜ ማስረጃ በ 2008 ዓ.ም በዋግና አካባቢዋ ተከሥቶ በነበረው ድርቅ ምክንያት ሰቆጣ ከተማ ውስጥ የመጠጥ ውሃ ጠፍቶ፣ ከከተማው ነዋሪዎች የተወሰኑ የሆቴል ነጋዴዎችና የመንግሥት ሠራተኞች ወደዚህ ቦታ እየሄዱ በቀን እስከ 70 ጀሪካን ውሃ ቀድተው ይወስዱ እንደነበር ነዋሪዎቹ ተናግረዋል (አቶ ብርሃን አማረ፣ የጻታ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ግንቦት 9/2013)።

ሌላኛው ታሪካዊ መስህብ ደግሞ "የዋግ ሹሞች ደም ህንጻ" እየተባለ የሚጠራው ግንብ ነው። ይህ ግንብ የሚገኘው "ፃግበጂ" በሚባለው ቦታ ውስጥ በ 029 ቀበሌ ነው። በዚች የገጠራማ ቦታ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ የቆመ ሦስት እጁ የፈረሰና አንዱ እጁ ያልፈረሰ ግንብ አለ። አሁንም ድረስ አካባቢው የሚጠራው "የዋግ ሹሞች ደም ህንጻ" እየተባለ ነው። ቦታው ስያሚውን ያገኘው የአካባቢው ተወላጅና በዋግሹምነት ማዕረግ ተሹሞ ፃግበጂን ሲያስተዳድር ከነበረው ዋግሹም ዳም (ደሞ) ጋር በተያያዘ ነው።

ዋግሹም ዳም ቤተመንግሥቱን በዋነኛነት ሰቆጣ ከተማ ላይ አድርጎ ወደ ፃግበጂ ሲሄድ የሚያርፍበትና የሕዝቡን አቤቱታ ሰምቶ ፍትሕ የሚሰጥበት ቅርንጫፍ ቤተመንግሥት ፃታ ላይ አሠርቶ ነበር።

ይህንም ቤት ያሠራው አፈሩን በእንስሳት ደም እየለወሰ በደም በተለወሰው ጭቃ ነው ይባላል። በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የግንብ ክፍል ፈርሶ አንድ አራተኛ የግንቡ ፍራሽ እንደቆመ ይገኛል። በቆመው ግንብ ላይ ቁልቋል በቅሎብታል። ይህንንም በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል። የአካባቢው ነዋሪዎች ቀደም ሲል ያለፈውን ዘመን የሚያስታውሱብትና እንደ ቅርስ የሚያዩት ስለሆነ የግንቡ ምልክት እንዲጠፋ እንደማይፈልጉ ይናገራሉ። በመሆኑም አካባቢው ዳምትኩነ 'የዳም ግንብ' እየተባለ ይጠራል (አቶ በላይ ገ/ሚካኤል፣ የጻታ ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ ግንቦት 7)።

### 3.4.2 መንፈሳዊ መስህቦች

በማይዳሰስ መንፈሳዊ መስህብነት ከሚመደቡ እና በፃታ ምድር ሊታዩ ከሚገባቸው በአላት መካከል የጥምቀት በአል ላይ የሚዘመረው የሰቆጣ አቋቋም ተብሎ የሚታወቀው ቀልብን የሚገዛ ያሬዳዊ ዜማ፣ በመስከረም 17 ቀን የሚከበረውና የክረምቱ ወቅት አልፎ የተዘራው አዝመራ በሚያሸትበት ወቅት የሚከበረው በአል የአዝመራ አመልካች ምሰሶ ስትወድቅ የሚታይበት ድንቅ የመስቀል በአል ተጠቃሽ ናቸው። ከዚህ ባለፈም በየአመቱ በግንቦት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ለተከታታይ ሶስት ቀናት የሚከበረው ግንቦተ-ማርያም የንፍሮ በአል በአካባው ሊታይ የሚገባውና አዝናኝ ሀይማታዊታዊና ማህበራዊ በአል ነው። የሚታዩና የሚዳሰሱ መንፈሳዊ ሐብቶች ከሚባሉት መካከል ደግሞ የተለያዩ ጥንታዊ ገዳማት ይገኙበታል። ከእነዚህም ውስጥ ሰላምጌ ማርያም እና ሲብ ተጠቃሽ ናቸው።

ሰላምጌ ማርያም ሌዊያውያን ካህናት ኢትዮጵያ ከተከሏቸው የኦሪት ቤተክርስቲያኖች አንዷ ስትሆን የዋግ ህዝብ የኦሪት ሀይማኖት ተከታይ እንደነበር የምታመላክት ዋነኛ ምስክር ነች። በሰቆጣ ወረዳ በጻግብጅ ንኡስ ወረዳ የምትገኘው ደብር በመጀመሪያ በዋሻ፣ በድንኳንና በመቀጠል ከኢየሩሳሌም መጣ በሚባልለት እንጨትና ድንጋይ ከክርስቶስ ልደት በፊት በተሰሩ ባለ 12 ክፍሎችና 12 በሮች መቅደስ የቅዳሴ አገልግሎት ትሰጣለች። በግራኝ መሀመድ ጦርነት ያልተቃጠለችና በባዜን ዘመነ መንግስት ከሚኒሊክ ጋር አብረው ከመጡት የእስራኤል በኩር ልጆች አንዱ በሆነው ሲራክ እንደተመሰረተች አባቶች ይናገራሉ (ቄስ እንዳለ አለልኝ፣ የቤተክርስቲያኗ አስተዳዳሪ፣ ግንቦት 12/2013)።

ከዚህ በተጨማሪም ደብሩ በዋግ ሹሞች የተበረከቱ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ባለቤት ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል ዋግ ሹም ክንፉ በስጦታ ያበረከቱት ትልቅ ደውል እና ዘተዉሃበ ዋክሽም ክንፉ የሚል ጽሁፍ የተቀረፀበት መስቀል፣ ጥንታዊ የብራና መጽሃፎችና አልባሳት እንዲሁም ሌሎች ጥንታዊ የቤተክርስቲያን መገልገያ እቃዎች ይገኙበታል።

ከሰላምጌ ማርያም ባሻገር በመንፈሳዊ መስህብነቱ የሚጠቀሰው ከሰቆጣ ከተማ በስተሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ በዜሮ ሃያ ዘጠኝ ቀበሌ ውስጥ በግምት ሠላሳ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ቦታ ነው። በአካባቢው ከፃግብጂ ጅልወ (ዙሪያ) ወደሚባለው ወንዝ ሲኬድ ወደ ወንዙ መውረጃ ገደላማ አካባቢ የማርያም ቤተክርስቲያን አለች። ይህች ቤተክርስቲያን ቀደም ሲል የአካባቢው ተወላጅ አባ ቀጸላ ጊዮርጊስ የመሰረቱት በጅልወ ዙሪያ ወንዝ ዳር ያለው ጥንታዊ የቅዱስ ማርቆስ ገዳም ቅፋፍ ወይም ቅርንጫፍ ስለሆነች የቀደመ ስሟ "ገዳም" ይባል እንደነበር የአካባቢው ነዋሪ ሽማግሌዎች ይናገራሉ። በአሁኑ ሰዓት ግን ገዳም ሳይሆን ሕጋውያን ቀሳውስትና ዲያቆናት የሚቀድሱባት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ናት።

ከፍ ሲል እንደተገለጸው አካባቢው በገዳምነት ስለነበር ገዳም እየተባለ በሚጠራበት ቀደም ባለው ጊዜ በገዳም ሥርዓት በአበምኔት ማለትም በመነኮሳት አባቶች ይተዳደር ነበር። ገዳሙን አንድ መነኩሴ እያስተዳደሩ

በነበሩበት ወቅት አንድ ጥንታዊ የብራና መጽሐፍ ከገዳሙ አውጥተው አሁን ቤተክርስቲያኑ ካለበት በስተደቡብ በኩል ያለ "አሬኩ" እየተባለ ከሚጠራው የቤተክርስቲያኑ አጸድ አቅራቢያ ላይ ሆነው መጽሐፉን ለግለሰቦች እንደሸጡ ይነገራል።

"አሬኩ" ማለት "ገበያ አለ" ማለት ሲሆን ከመጽሐፉ ሽያጭ ጋር ተያይዞ የተሰየመ ቦታ እንደሆነ ነዋሪዎቹ ያስረዳሉ። ይህ ጉዳይ ከመንግሥት ጆሮ ደረሰና በዘመኑ ዋግን ያስተዳድር የነበረው ዋግሹም መነኩሴውን አስጠርቶ አርባ ጅራፍ ገርፎ መልሶ ወደ ገዳሙ ላካቸው።

ከዚህ ክሥተት በፊት መነኩሴው ገዳሙን እያስተዳደሩ በነበሩበት ወቅት የአካባቢው ማኅበረሰብ በዓውደ ዓመት ፍሪዳ ሲጥሉ ወይም ሲያርዱ ሳንባውንና አንድ ማሠሮ ቅቤ እንደ ዐሥራት አድርገው ለመነኩሴው ይሰጧቸው ነበር ይባላል። ፍሪዳውን የሚያርዱትም በዚያው አካባቢ ባለ ትልቅ የሾላ ዛፍ ሥር ስለነበር ይህ ትልቅ ዛፍ ስሙ "በበ ዐሥራተይ" ይባላል። ትርጓሜውም "ዐሥራት የሚከፈልበት ሾላ" ማለት ነው። ዛፉ በአሁኑ ወቅት ገሚሱ ደርቆ ገሚሱ ደግሞ እርጥብ እንደሆነ ይገኛል።

የገዳሙ አስተዳዳሪ የነበሩት መነኩሴ በጥንታዊ የብራና መጽሐፍ ሽያጭ ምክንያት በመንግሥት ከተቀጡ በኋላ የአካባቢው ሕዝብ የተለመደውን የፍሪዳ ሣንባና አንድ ማሰሮ ቅቤ ዐሥራት ወይም ሰርከ ኅብስት ለመነኩሴው አንሰጥም አሉ።

በዚህ ምክንያት መነኩሴው ወደ ሰቆጣ በመሄድ "የተለመደው ግብር ሊቀርብኝ አይገባም" ሲሉ ለዋግሹሙ አቤቱታ አቀረቡ። የአካባቢው ሕዝብ ከወከላቸው ሰዎች ጋር ብዙ ጊዜ ከተሟገቱ በኋላ መነኩሴውን በተጠራጠሩት የመጽሐፍ ሽያጭ መንግሥት ተመጣጣኝ ቅጣት ስለቀጣቸው ከዚህ በፊት ይሰጣቸው የነበረው የፍሪዳ ሳንባና ማሰሮ ቅቤ እንደተለመደው ይሰጣቸው ዘንድ ተፈረደላቸው። በዚያ ሰዓት አንድ ተናጋሪ ሰው "ሲብስ እንቊጠ ጨቅን" 'ለሣንባ ተብሎ ይህን ያህል ሙግት' አለ ይባላል። በዚህ ምክንያት ቦታው "ሲብ" እየተባለ መጠራት ጀመረ። በአሁኑ ሰዓት ይህ ቦታ ከአማርኛ ተፅዕኖ የተነሳ ማለትም በወረዳው የመንግሥትም ሆነ የቤተክህነት ሴክተር መሥሪያ ቤቶች የሥራ ቋንቋ አማርኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ 'ሰቡብ' የሚል መጠሪያ እየተሰጠ ያለበት ሁኔታ አለ። ነገር ግን ይህ አባባል መጀመሪያ ቦታው ከተሰየመበት ምክንያት ጋር የተዛመደ ሳይሆን ያልነበረ ሌላ ትርጉም የሚያስከትል መሆኑን ነዋሪዎቹ ይናገራሉ (አቶ አስራቴ ብርሃኑ፣ የአካባቢው ታሪክ አዋቂ፣ ግንቦት 12/2013)።

### **3.4.3.** ማህበራዊ መስህብ

የህድሞ ቤት የሚባለው የፃታ ማህበረሰብ የጥንት ባህላዊ ቤት ሲሆን ለዚህ ቤት መስሪያነት የሚውለው ቁስም በአካባቢው ከሚገኙ ድንጋይ (ጠፍጣፋ ቀይና ነጭ)፣ አፈር፣ እንጨት፣ ሸንበቆ፣ ክትክታና ጥንጁት የሚገኝ ነው

። የህድሞ ቤት የመሰራቱ ምክንያት አንደኛ ‹‹በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ›› እንዲሉ አንድ ቤት በሚያሰራ መሬት ላይ ፎቅ እና ምድር ቤት በመስራት ታችኛውን ዕቃ ቤት ላይኛውን ለሰዎች መኖሪያ በማድረግ ይገለገላሉ። በተለይ ባለጸጋዎች አካባቢውን የሚያስታዳድሩ ሰዎች ከማንኛውም አደጋ ራስንና አካባቢን ለመጠበቅ ህድሞ ቤት በመስራት በላይኛው ቤት የተለያዩ መስኮቶችን በመጠቀም ይገለገላሉ። እንዲሁም የህድሞ ቤት በሙቀት ወራት ዕህል እንዳይነቅዝ ለማናፈሻነት ጭምር ያገለግላል።



*ሥዕል 3.1፦* ባህላዊ የህድሞ ቤት

### **3.4.4** ባህላዊ መስህቦች

ከባህላዊ መስህቦች መካከል የሻደይ ጨዋታ፣ የቢቾ በአል ጨዋታና፣ የዋርዳሆየ ጨዋታ፣ እንዲሁም የሚሻሚሾ እና ሆርኳንዛ ጨዋታዎች ተጠቃሾች ናቸው።

በዋግ የሻደይ ጨዋታ ከውስን የወንዶች ተሳትፎ በቀር ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ሴቶች ብቻ የሚጫወቱትና የሚያከብሩት በዓል ወይም ጨዋታ ነው። የሻደይ ጨዋታ ህጻናትን፣ ወጣቶችንና እናቶችን ያለልዩነት የሚያሳትፍ ደማቅ፣ውብና ሁሉን አቀፍ ባህላዊ ክብረበዓል ነው። በመሆኑም በዓሉ ሴቶች በጉጉት፣ በናፍቆት፣ በፍቅርና በልዩ ዝግጅት የሚጠብቁትና በሚኖሩበት ማህበራዊ ስርዓት ሚዛን አዕምሯዊ፣ መንፈሳዊ፣ አለማዊ፣ ማህበራዊ፣ ምጣኔህብታዊና ስነልቡናዊ እርካታ የሚያገኙበት ነው። ጨዋታው በብሔረሰቡ ዘመናትን

ያስቆጠረ የብሔረሰቡ መንፈሳዊና አለማዊ ፈጠራዎች የዳበሩበትና የጨዋታው አያሌ ክዋኔዎች የሚንጸባረቁበት ብሎም በየዘመናቱ ያለ ትውልድ የራሱን መልካም እሴቶች እያካተተ ያጎለበተው የመጫወትን ነፃነት ለሴቶች የሚያጎናጽፍ ባህላዊ የጨዋታ ስርዓት ነው።

በሻደይ ጨዋታ ሴቶች በአዳዲስ ባህላዊ አልባሳት፣ ጌጣጌጥ፣ መዋቢያዎች፣ የፀጉር ስሪት ወዘተ ከአዘቦት ቀናት በተለየ ሁናቴ ደምቀው የሚወጡበት በመሆኑ በየፈርጁ ገበያው ስለሚደራ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ሲጎላ፣ በየቤቱ /ከድሃ እስከ ሀብታም/ በየቤተክርስቲያኑ፣ በየአደባባዩና በየመንዱ ባህላዊ ስርዓትን ተከትሎና አክብሮ በእግዳ ተቀባይነት፣ በአክብሮት፣ በፍቅር፣በመተሳሰብና በቤተሰባዊ ስሜት የሚደረገው የጨዋታው ስርዓት በህዝቦች መካከል ሊኖር የሚገባውን ማህበራዊ የጨዋታውን ፋይዳ ያንፀባርቃል። በቤተክርስቲያን ከፆመ ፍልሰታ ጋር በተያያዘና በግጥሞቻቸው የሚገለጹት ይዘቶች ሀይማኖትን ስለሚገልጹ በወጣት ሴቶችና ወንዶች መካከል የሚኖረው ግንኙነት መልካም ትውውቅን ፈጥሮ ወደ ጋብቻ ሊያመራ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ብዙ በመሆናቸውና አያሌ ባህላዊ ገጽታዎች የሚንጻባረቁበት በመሆኑ ለቱሪዝም ልማት ምቹ መሰረተነቱ ሰፊ ስለሆነ ለህብረተሰቡ አእምሮዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሀይማኖታዊ ምጣኔ ሀብታዊ እድገትና ብልጽግና ከፍተኛ ሚና ሊጫወት የሚችል ባህላዊ ጨዋታ ነው።

ልጃገረዶቹ በእለተ ነሐሴ 16 ቀን እግራቸውንና እጃቸውን እንሶስላ ቀብተው፣ ጣዕምና ሽታ ባላቸው እፅዋትና ሽቶዎች በተለወሰ ቅቤ ፀጉራቸውን ቀብብተው፣ የተለያዩ ጌጣጌጦችን በጸጉራቸው አድርገው፣ ባህላዊ ነጫጭ /ጀበርባሬና ማግ/ አልባሳትን ለብሰውና ወገባቸውን በሻሽ ሽብ አድርገው፣ የብርና የወርቅ ጌጣጌጦቻቸውን በእጃቸው፣ በእግራቸውና በአንገታቸው አድርገው፣ ጥርሳቸውንና የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ተነቅሰው፣ አይናቸውን ተኩለው፣ በተለያዩ የስሬት አይነቶች ፀጉራቸውን ተስርተው፣ ሰቆጤና ፕላስቲክ ጫማዎቻቸውን አጥልቀው፣ መስከረም ሲጠባ ብቅ እንደምትል አደይ አበባ ተውበው፣ ደምቀውና አምረው፣ እንደበጋ ጨረቃ ደምቀው እንደሐምሌ ቅጠልና ሳር ለምልመውና ለአይን አዲስ ፣ድንቅና ብርቅ ሆነው ብቅ ሲሉ እንኳን ለእንግዳ ለሚያውቃቸውም አስደምምው ይማርካሉ። እጅግ ቆንጅተውና አምረው ከመቅረባቸው ምክንያት የሻደይ ልጃገረድን አይተህ አተግባ እየተባለ በህብረተሰቡ ይነገራል። መልክ የሌላቸው እንኳን በጣም አምረው ስለሚቀርቡ ከቆንጆቹ ለመለየት የሚከብድበት አጋጣሚ ይከሰታል። የልጃገረዶቹ ፈገግታ፣ መልክ፣ ፀጉር፣ ያጎጠጎጡ ጡቶች፣ የእርግብን አይን የሚያስንቁ አይኖች ወዘተ. በባህላዊ አጊጌጥና አለባበስ እንዲሁም ማስዋቢያ ዘዴዎች ደምቀው የሚቀርቡበት በዓል በመሆኑ ለዋግ ሴቶች ልዩ ትርጉም አለው። የሻደይ ጨዋታ ለዋግ ሴቶች የአንጥረኛው፣ የልብስ ሰፊውና ሸማኔው፣ የጠላፊው፣ የነቃሹ፣ የፀጉር ሰሪዋ፣ ወዘተ ችሎታ ጎልቶ የሚታይበትና በውድድር የሚታጅብ የገበያ እድሉም የሚሰፋበት መልካም አጋጣሚ ነው።

የሻደይ ጨዋታ በዓል አከባበር ስርዓት ቅደም ተከተልና በጨዋታው ወቅት የሚቀርቡት ዘፈኖች ግጥሞች በክፍል በክፍላቸው የሚከተሉትን ይመስላሉ። የሻደይ ጨዋታ የሚጀምረው ነሐሴ 16 በመንደሩ አማካይ ቦታ በመሰባሰብ፣ የመንገድ ጨዋታዎችን በመጨዋት፣ በቅርብ ቤተክርስትያን/ደብር/፣ ከመንገድ፣ ከግለሰብ ቤት በቅደም ተከተል በሚካሄዱ ስርዓቶችና በመጨረሻም ሁሉም ቡድኖች በተገኙበት በተመረጠ/በተለመደ/ አደባባይ በሚካሔድ የውድድር ስርዓት ባለው ዝግጅት በዓሉ ይጠናቀቃል።



*ሥዕል 3.2፡-* ሴቶች በሻደይ ጨዋታ ላይ

ሌላኛው ባህላዊ ጨዋታ ደግሞ በኢትዮጵያ አዲስ ዘመን ሲብት አብሮ የሚጀመር፤ በመስከረም የመጀመሪያ ቀን ማታ ተጀምሮ በመስከረም 16 ማታ የሚጠናቀቀው የ"ዋርዳሆየ" ጨዋታ ነው። ባህላዊ ጨዋታውን የሚጫወቱት ወንዶች ሲሆኑ የመጀመሪያውን ሳምንት በመጫወቻ ቦታው ላይ በሚደረጉ ጨዋታዎችና ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ሳምንት ደግሞ በየቤቱ ማታ እየተዞረ ለቤተክርስቲያን ገቢ የሚሰበሰብበት ስራአት አለው። በመጀመሪያው ሳምንት ‹‹ሆየ ሆየ›› እያለ አንድ ሰው ሲያወጣ ሌሎቹ ደግሞ እየተቀበሉት ምሽቱን ካደመቁ በኋላ ከጥቁር እና የማይፈረከስ ድንጋይ የተሰራ ‹‹አሽኮለል›› የሚል መጠሪያ የተሰጣት መጫዋጫ ድንጋይ ከእሳት እንድትገባ ተደርጎ ቀይ እስከሚሆን ይጠበቅና በሁለት ቡድን ተከፍለው ለሚወዳደሩ ወጣቶች በዳኛ አማካኝነት ትውረወራለች። ሁለቱ ቡድኖች የጋለችውን ድንጋይ በእጃቸው ተቃምተው መልሰው ለወረወረላቸው ዳኛ ማስረከብ የቻለ ነጥብ የሚቆጠርለት እና በመጨረሻም ከብዙ ነጥቦች በኋላ አሸናፊ የሚሆንበት አስደሳች ባህላዊ ጨዋታ ነው። በዚህ ጨዋታ ተሸናፊ ቡድን ሽፈቱን ተቀብሎ ለሚቀጥለው ጨዋታ ተዘጋጅቶ የሚመጣበት እንጅ መጣላትና ማኩረፍ የሚባል ነገር ነውር ሆኖ የሚታይበት ለዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ጨዋታ ነው። ይህንን ጨዋታ በወርሀ መስከረም የ 16 ቀናት ምሽት ታድሞ መመልከት ቀልብን ይገዛል።



*ሥዕል 3.3፡- ወንዶች የዋርዳሆየ ጨዋታ ሲጫወቱ*

## ምዕራፍ አራት

## የጠልሰም ባህላዊ ዕውቀትና መድኃኒትነት በፃታ ወረዳ

በዚህ ክፍል የጠልሰም መድኃኒትነት በፃታ በሚል ርእስ መነሻነት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችና የተስተዋሉ ጉዳዮች ይተነተናሉ። በዚህ መነሻነትም የጠልሰምን አሰራርና አዘገጃጀት፣ አስፈላጊ ግብዓቶች፣ አገልግሎት ብሎም የመድህኒትነት እሳቤ የሚመለከቱ መረጃዎች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

### **4.1** የጠልሰም ግብዓቶችና የሚገኙበት ሥርዓት

በምዕራፍ ሁለት ጠልሰም ምንድነው?፣ መቼ እና እንዴት ተጀመረ? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልሱ መረጃዎች ተተንትነዋል። በዚህ ክፍል ደግሞ በቀጥታ የጠልሰምን የመድሃኒትነት እሳቤ ከማብራራት በፊት ይህ ጥበባዊ መድሃኒት እንዴት እና ከምን ይዘጋጃል?፣ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችስ ምን ምን ናቸው የሚሉትን ለማንሳት ተሞክሯል።

ጠልሰምን ለመስራት በዋናነት አስፈላጊው ግብዓት ቆዳ ነው። ይህ ቆዳ የበግ፣ የፍየል አሊያም የሚዳቋ ቆዳ ነው። ይህ ቆዳ የበሬ አሊያም የሌላ እንስሳ እንዲሆን የማይፈለግበትን ምክንያት ቄስ ደሳለኝ እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> እኔ ቄስ ነኝ። ለጠልሰም መጠልሰሚያነት የሚውል ቆዳን ስመርጥም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ካለው እሳቤ ተነስቼ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በግ የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሰፍሯል። አብርሃም ልጁን ሊሰዋ በተዘጋጀ ጊዜ በይስህቅ ፈንታ ቤዛ ሆኖ የቀረበው በግ ነው። ስለሆነም በግ ቤዛ ነው። በሌላ መልኩም የፍየልም ሆነ የሚዳቋ ቆዳን እንዳስፈላጊነቱ እጠቀማለሁ ይህም ደግሞ እውቀቱን በቤተሰብ ሐረግ ያገኘሁት ስለሆነ ቀድሞውኑ ሲሰሩበት የነበረውን ልማድ መከተሌ መንፈሳቸው እንዳይጣላኝ፤ ለምሰራው ሥራም ከእነርሱ እንደተማርኩት መፍትሔ ሆኖ ሲገኝ ስላየሁ ይህንኑ እጠቀማሉ (ነሐሴ 27/2012፣ 3፡55)።

መድሃኒትነት ካላቸው እጽዋት የተቀመመ ጥቁርና ቀይ ቀለም እንዲሁም መድሃኒትነት ከሌላቸው እጽዋት የተዘጋጁ የተለያዩ ቀለማት ለጠልሰም ሥራ አስፈላጊ ግብዓቶች ናቸው። እንደ መፋቂያ መራመሚያ እና መዳመጫ ያሉ የብራና መሳሪያዎችም ዋነኞቹ አስፈላጊ ቁሳቁሶች ናቸው። የሸንበቆ ወይም የመቃ ብዕር እና በተለምዶ ባሕር ዐረብ እየተባለ የሚጠራው የጠልሰሙን ማህደር ወይም ሽፋን ለመስራት የሚያገለግል ቀይ ቆዳም ጠልሰምን ለማዘጋጀት የሚውል ግብዓት ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት እነዚህ ግብዓቶች ወደጠልሳሚዎች እጅ ከመግባታቸው በፊት የሚያልፉት ሥርዓት አለ። በተለይም ጠልሰም የሚያስጠለስሙ ሰዎች የሚጠለሰምበትን ቆዳ የሚያመጡበት ሥርዓት አለ። አስጠልሳሚዎች ከቤተሰባዊ ተዋረድ የመጣ የበግ ወይም የፍየል ቤዛ አላቸው። ቤዛ ማለት አንድ ሰው ሳይታመምም ሆነ ከታመመ በኋላ "በእኔ ላይ የሚመጣውን መናፍስታዊ በሽታ አርቅልኝ" ወይም "ማንኛውም በሽታ እንዳይዘኝ ቤዛ ሁነኝ" ብሎ በራሱ የሚያዘረው በግ ወይም ፍየል ነው። ይህን በግ ወይም ፍየል ከቀለሙ ጀምሮ የሚመረጥባቸው ሁለት አማራጮች አሉ። የመጀመርያው በማህበረሰቡ ዘንድ አዋቂ የሆኑና በተደጋጋሚ ለዚህ ተግባር ማህበረሰቡ የሚመርጣቸው ያላዩትን ሁሉ የሚረዱና የሚያውቁ፤ መናፍስትን ጭምር ያናግራሉ ተብለው የሚታሰቡ ሰዎች የሚመርጡት ሲሆን እነዚህ ሰዎች ቆዳውን ብቻ ሳይሆን ምን ዓይነት ጠልሳሚ መስራት እንዳለበት ጭምር "በደቡብ የሚገኝ፤ በምስራቅ የሚገኝ፣ ቀይ ሰው" ወዘተ. እያሉ ጭምር የሚመርጡ ሰዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ ራሳቸው ጠልሳሚዎች የሚመርጡት ነው። ዓዋቂ ገሰሰ ቢተው ዓዋቂዎች ስለሚመርጡበት ሁኔታ የሚከተለውን ተናግረዋል።

> የመጀመርያው "ከአያት ከቅማታችን ለእኛ ዘሮች ቤዛነት ሲሰራበት የመጣው ቀይ፣ ነጭ ወይም ጉብስማ ቀለም ያለው በግ ነው" ከሚለው ብሂል የመጣ ነው። በዚህ አኳኋን በሚደረገው መረጣ ጊዜ የሚያስጠለስመው አካል ራሱ መርጦ በግም ሆነ ፍየል አቅርቦ፤ ቡና ተፈልቶ፤ ቁጤማ ተጎዝጉዞ ከቤተሰቡ መካከል ከፍ ያለች እናት ወይም አባት አሊያም ከቤተሰብ ሀረግ ጋር ተያይዞ የመጣ የቤት አውሊያ አድሮባታል ተብላ የምትገመት እናት ወይም አባት በጉን ወይም ፍየሉን ያዞሩለታል። የተዘረው ቤዛ ታርዶ ቤተሰብ የሆነ አሊያም በጋብቻ የተዛመደ ሰው ብቻ ሥጋውን አብሮ ከቤተሰብ ጋር ይበላል። ሥጋውን የቤተሰብ አባል ከሆነ ሰው ውጪ እንዲበላው የማይፈለግበት ምክንያትም በዘር ሐረግ የመጣ የሚጠብቅና የሚለመን መንፈስ አለ ተብሎ ስለሚታመን ሥጋውን ከዚያ የዘር ሐረግ ውጪ የሆነ ሰው ቢበላው ይህ መንፈስ ከሌላ መንፈስ ጋር እንዳይጣላ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። የበጉን ደምም ሆነ የተበላውን አጥንት ውሻና ድመት እንዳይበላው ይደረጋል። ስለምን ውሻና ድመት እንዳይለክፈው ይፈለጋል? ከተባለም በተለምዶ ሥጋቸው የሚበሉ እንሰሳትን ቅዱስ፤ ሥጋቸው የማይበላ እንሰሳትን ደግሞ ርኩስ አድርጎ የመቁጠር ሁኔታ አለ። እናም ሕመምተኛው ቅዱስ የሆነውን እንሰሳ ሥጋ በልቶ የዚያን ቅሪት ሥጋው የማይበላ እንስሳ ከለከፈው መድሃኒቱ ይረክሳል ተብሎ ስለሚታመን ነው። (ነሐሴ 28/2012፣ 5፡30) ።

ከላይ በተገለጸው አኳኋን የሚደረገው የጠልሰም አሰጣጥ መንገድ የመጀመርያው መንገድ ሲሆን ይህ ሥርዓት ከተከወነ በኋላ ቆዳውን (አጎዛውን) ለጠልሳሚዎች በመስጠት ጠልሳሚዎቹ ፍቀው ብራና አድርገውና ጠልሰሙን ጠልስመው ይሰጣሉ። ጠልሰሙን ለመድሃኒትነት ከሚያስረው ሰው ቤት ቡና

ተፈልቶ፣ የማሽላ ቆሎ ተቆልቶ ፤ ቤተሰብ ተሰብስቦ “እውነተኛ መድሃኒት ይሁንልህ” እየተባለ ጠልሰሙ በአንገቱ ይታሰርለታል።

ሌላው ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ራሳቸው ጠልሳሚዎች የሚመርጡበት ነው። ጠልሳሚዎች ራሳቸው በሚናገሩት የበግ ወይም የፍየል ቀለም ምርጫ ወይም ደግሞ ጠልሳሚ ያልሆኑ የባህል አዋቂ ሰዎች በሚናገሩት መሰረት ቤዛው ለታማሚው ተነግሮት የተነገረውን ዓይነት ቀለም ያለው በግ ወይም ፍየል ከላይ በመጀመርያው መንገድ የቀረበውን ሥርዓት አካሂዶ ቆዳውን ለጠልሳሚዎች ይሰጣል። ስለሆነም የበግ ወይም ፍየል ቀለም አመራረጥ ሁኔታዎቹ ይለያዩ እንጂ ቀለሙ ከተመረጠ በኋላ ያለው ሥርዓት ክዋኔ ግን ተመሳሳይ ነው ።

ይህ በጠልሳሚዎች የሚደረግ የቆዳ መረጣ እንደየ ሕመሞቹ ዓይነት ሊወሰን ይችላል። ይህ የሚሆነው ሕመሞቹ ሥርዓት ክዋኔ የማያስፈልጋቸው ሲሆኑ ነው። ሥርዓት ክዋኔ የማያስፈልጋቸው ሕመሞች የሚባሉት የራስን መንፈስ እንዳይጣላ መለማመኛ  ያልሆኑና ሌላን መንፈስ ማራቂያና ማሸሻ የሆኑት ናቸው። እንዲሁም ከተለያዩ መናፍስት መከላከያ ለሆኑ በአንገት ለሚታሰሩ የጠልሰም ዓይነቶች በብዛት በራሳቸው በጠልሳሚያኑ የቆዳ መረጣው ይደረጋል። አልፎ አልፎም በተራረፉ ቁማጭ ቆዳዎች ጠልሰሙ ተጠልስሞ አስማቱ ተጽፎ ለሕመምተኛው የሚታሰርበት ሁኔታም አለ።

በሌላ መልኩም ጠልሰም በወረቀት ላይ ሊጠለሰም ይችላል። ይህ በወረቀት ላይ የሚጠለሰም ጠልሰም ከወረቀት ዓይነትና ቀለም መረጣ ጀምሮ ሥርዓታዊና ምክንያታዊ ሂደትን የሚከተል ነው። ጠልሳሚ አዕመረ በወረቀት ላይ ስለሚጠለስሙት ጠልሰም የሚከተለውን ብለዋል።

> ጠልሰም በወረቀት ጭምር አዘጋጃለሁ። ለዚህም መስመር የሌለው ወረቀት ይመረጣል። ምክንያቱም አቋራጭና አሳባሪ የሌለው በንጹህ መንገድ የመሄድ ምሳሌነትን በመውሰድና ቀድሞውንም የነበረ ልማድ ስለሆነ ነው። ብዙ ጊዜም የቀለም ምርጫ ይኖራል። ለምሳሌ በጥቁር ወረቀት የሚጠለሰም የጠልሰም ዓይነት ለእኩይ ሥራ የሚውል ነው። ምክንያቱም የጨለማ ንጉስ ዲያቢሎስ ስለሆነ ሥራውንም እሱ በተመሰለበት የጨለማ መንገድ ወረቀቱን በዚያው ቀለም ማድረጉ እሶህን በሾህ እንዲሉ በዚህ ሁኔታ መጠቀም የተለመደ ነው። (ነሐሴ 27/2012፣ 8፡22)

ከላይ በሰፈረው መልኩ የጠልሰሙን ቆዳ ዓዋቂዎች መርጠውና የሚጠለስመውንም ሰውጭምር አመልክተው እንደሚያሳዩ ሁሉ ለመጠልሰሚያ የሚሆነውን ቆዳ የሚመርጡበት ቀንም አለ። አዋቂ ሸግነው ኪዴ የጠልሰምን ቆዳ ለመምረጥ ስለሚመረጡ ቀናት የሚከተለውን ገልጸዋል።

> ለጠልሰም መጻፊያ የሚውለውን የቆዳ ዓይነት ለመምረጥ ተፈላጊ ቀናት አሉ። በታየኝ መሰረት በዚህ ቀን ቢደረግላት፤ ቤዛ ተደርጎ የተመረጠው የእንስሳ ዓይነት በዚህ ቀን ቢዞርላት ብዬ እመርጣለሁ። ጠልሰሙ የሚዘጋጅለት አካልም የትኛው ቀን ክፍሉ እንደሆነ ዓውደ ነገሥትን በመመልከት አሊያም ደግሞ እንዲሁ በማየት የዚያ ሰው ክፍል የሆነውን ቀን እመርጣለሁ (ሐምሌ 2/2012፣ 3፡20)።

ከላይ መረጃ ሰጪው እንደተናገሩት በዚህ በጻታ ወረዳ ከጠልሰም ሥራ ጋር በተገናኘ ዓዋቂ ተደርገው የተመረጡ ሰዎች የመጠልሰሚያ ቆዳን ከመምረጥና ቆዳው የሚመረጥበትንም ቀን ከመወሰን አንስቶ ጠልሳሚው ሰው ማን መሆን እንዳለበት ጭምር እንደሚጠቁሙ መመልከት ይቻላል። ራሳቸው ጠልሳሚዎች መምረጥ ከሚችሉበት አግባብ ውጪ በእነዚህ አዋቂ ሰዎች የተመረጠውን ቆዳም ሆነ ቀናት መቀየር አይቻልም። ከተቀየረ መድሃኒቱ አይሰምርም፤ አይሰራም። ምክንያቱም እነዚህ አዋቂዎች ቤዛውንም ሆነ ቆዳውም እንዲሁም ቀኑን የሚመርጡት ዓውደ ነገስትን ገልጠውና ኮከብ አንብበው ነውና የታማሚውን እጣ ክፍል የሚያውቁት እነሱ ናቸው ተብሎ ይታመናል።

ጠልሰም ከመሳያ ቆዳው ባለፈ የመጠልሰሚያ ማለትም አስማቱን መጻፊ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የመንፈስ ስዕላቱን መሳያ ቀለማት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ጠልሳሚያኑ እነዚህን ቀለማት ከተለያዩ ቀለም ካላቸው እጽዋት ያዘጋጃሉ። ነገር ግን ይህን ጽሑፍ ለመጻፍ ይህን ቀለም፤ ይህቺን መንፈስ ለመሳል ይሔኛውን ቀለም ልጠቀም የሚል ልማድና ምስጢራዊ ትስስር እንደሌላቸው ገልጸዋል። ዋናውና ተፈላጊው ነገር ቀለማቱ ሳይበላሹና ሳይለቁ ለረዥም ጊዜ ይቆያሉ ወይ የሚለው ጉዳይ ነው።

> ቀለም የምንጠቀመው ከእጽዋት በጥብጠን ነው። ዋናው ዬፈለገው ነገር ቀለሞቹ ብራናው ላይ ካረፉ በኋላ ሳይለቁ ለረዥም ጊዜ እንዲቆዩ ይፈለጋል። ከዚህ ባለፈ ግን ለዚህኛው ሥዕል እና ጸሎት ወይም አስማት ይህኛውን ቀለም ብቻ ነው መጠቀም ያለብኝ የሚል ነገር የለም። ዋናው የመንፈስ ስእሎች አስፈሪ ሆነው እንዲቀርቡ የሚያደርገው የትኛውን ቀለም ብጠቀም ነው የሚለውን ነው የምናስበው። እንዲያውም አሁን አሁን ዘመናዊ ቀለማትን ችምር እንጠቀማለን (ቄስ ደሳለኝ፣ ነሐሴ 27/2012፣ 4፡10)።

ከላይ ከሰፈረው ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው በጠልሰም ሥራ የቀለም መረጣ ውስጥ ቀለማቱን ከመናፍስቱ ባህርይ አሊያም ከመድኃኒትነት እሳቤው ጋር የሚያዛምደው ምስጢራዊ ትስስር የለም።

አሁን አሁን ከእጽዋት ቀለምን የመበጥበጥ ልማድም ከፋብሪካ ተመርተው በሚወጡ የቆርቆሮ ቀለማት የመተካቱን ሁኔታም ማጤን ይቻላል።

## 4.2 የጠልሰም ዓይነቶች

የፃታ ወረዳ የጠልሰም ዓይነቶች ሶስት ዓይነት ሲሆኑ እያንዳንዳቸው የጠልሰም ዓይነቶች የራሳቸው የሆነ የአጠላሳሰም ጥበብ አላቸው። ከብራናው ርዝማኔ አንስቶ እንደየ ህመሞቹ የሚሰጡት የጠልሰም መድኃኒት አይነቶች ይለያያሉ። ይህን በማስመልከት ጠልሳሚ መሪጌታ አፈወርቅ ስለጠልሰም ዓይነቶች የሚከተለውን መረጃ ተናግረዋል።

> በዋነኛነት ሦስት ዓይነት ጠልሰሞች አሉ፤ እነሱም የቁም ክታብ (በሰዎች ቁመት ልክ የሚዘጋጅ)፣ የወገብ ዙር ክታብ (በሰዎች በወገብ ዙር ልክ የሚዘጋጅ) እና የግንባር ክታብ (በሰዎች ግንባር ከጆሮ እስከ ጆሮ የሚደርስ) ናቸው። የቁም ክታብ ወይም በሰው ቁመት ልክ የሚሠራ ጠልሰም የሚዘጋጀው በአብዛኛው ለሾተላይ ወይም ወልደው ፅንስ ለሚወርድባቸው እናቶች ነው። በወገብ ዙሪያ ልክ የሚዘጋጀው ጠልሰም ደም ለሚፈሳቸው ሲሆን በግንባር ልክ የሚዘጋጀው የጠልሰም ዓይነት ደሞ ለዓይነጥላና ከዓይነ ጥላ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ሌሎች ሕመሞች ነው (ነሐሴ 27/2012፣ 5፡35)።

የቁም ክታብ ወይም በሰዎች ቁመት ልክ የሚዘጋጅ ጠልሰም ፅንስ ለሚወርድባቸው ወይም ልጅ ወልደው ማሳደግ ለማይችሉ እናቶች የሚዘጋጅ መሆኑ እንድምታው ምን ሊሆን ይችላል? በሚል መሠረት ሐሳብ ስንነሣ ቁም ክታብ ሙሉ ሰውን የሚወክል በሰዎቹ ቁመት ልክ ተለክቶ የሚዘጋጅ ጠልሰም እንደሆነ ይታሰባል። ከሌሎቹ ጠልሰሞች በበለጠ ርዝመት ስለሚኖረው በውስጡ ብዙ አስማቶችን ሥዕላዋ ቅርፆችን መያዝ የሚችል መሆኑ አያጠራጥርም ። ከዚህ አንጻር የጠልሳሚዎቹ እምነትና ሥነ አመክንዮ "ሙሉ አካል ያለው ሕፃን ተወልዶ እንዲያድግ የሚያስችል በሰው ቁመት ልክ የተዘጋጀ ጠልሰም ነው'' በሚል ሥነ ልቡናዊ አንድምታ እንዳለው ይገመታል።

በእናቶች ወገብ ልክ የሚዘጋጀው የጠልሰም ዓይነት ብዙ ጊዜ የሚዘጋጀው ደም ያለወቅቱ ለሚፈሳቸው እናቶች እንደሆነ ከፍ ሲል ስማቸው የተጠቀሰው ጠልሳሚዎች ጠቁመዋል፤ በዚህም ወገብ ጋራ የተያያዘ አመክንዮ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ማንሣቱ ተገቢ ነው። እናቶች ደም ሊፈሳቸው ሲል ወገባቸውን እንደሚያማቸው፣ እንደሚቆረጥማቸው የሚታወቅ እውነታ አለ፤ በተለይ ያለ ጊዜው የሚፈስ የወር አበባ ሕመም ነው ተብሎ በፃታ ማህበረሰብ የሚታመን እንደሆነ በቃለመጠይቅ የተገኘው ማስረጃም

የሚያመላክተው ይህንኑ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል። ስለሆነም በድንገት ወገብን በመቆረጣጠም ደም እንዲፈስ ለሚያደርግ ረቂቅ የመንፈስ ሕመም በወገብ ልክ የሚዘጋጅ ጠልሰም መፍትሔ ነው ከሚል ባህላዊና አካባቢያዊ ሥነ ልቡናዊ እምነት የተነሣ የሚዘጋጅ እንደሆነ ይታመናል።

በእናቶችና በእህቶች ግንባር ልክ የሚሠራው አጭር ጠልሰም በዋነኛነት ለዓይነ ጥላና ከዓይነ ጥላ ጋር ተያያዥነት ላላቸው መናፍስታዊ ሕመሞች የሚዘጋጅ ባህላዊ መድኃኒት እንደሆነ ከፍ ሲል በተሰጠው የጠልሳሚው ንግግር ተገልጿል። ለዓይነ ጥላ በግንባር ልክ መሠራቱ ዓይን ከግንባር ጋር የተያያዘ አካል መሆኑን መነሻ በማድረግ ነው። ዓይነ ጥላ የሚባለው መናፍስታዊ ሕመም በዓይን በኩል የሚገባ ወይም ከሰው የአካል ክፍሎች ሁሉ ዓይንን ታኮ የሚቆራኝ ሕመም እንደሆነ የሚገመት ነው። ህመሙም የሰዎችን ዕድል ፈንታን ጽዋ ተርታን ጭምር የሚያደናቅፍ እንደሆነም በማህበረሰቡ ይታመናል (መሪጌታ አፈወርቅ፣ ነሐሴ 27/2012፣ 5፡35)።

ከእነዚህ ሶስት የጠልሰም ዓይነቶች ባለፈ አልፎ አልፎ በአንገት የሚታሰር የጠልሰም ዓይነትም ይስተዋላል። ይህ የጠልሰም ዓይነት ራስን እንደ ቡዳ ካሉ መናፍስት ለመከላከል ተብለው ለሚዘጋጁ ጠልሰሞች የሚታሰር ነው። በቁርጥራጭ ቆዳዎች ስመ አምላክን አሊያም የመላእክትን ስሞች በመጻፍ አሊያም ሥዕላቱን በትንሹ በመሳል መናፍስቱን እንዲከላከልለት በተፈለገው ሰው አንገት ላይ ይታሰራል። ይህ የጠልሰም ዓይነት በብዛት ለህጻናት እና ወልደው ለተኙ አራስ እናቶች ይታሰራል። ህጻናት ቶሎ በሰው ዓይን ውስጥ የሚገቡ ስለሆኑ ከቡዳ መንፈስ ለመከላከል፤ አራስ እናቶችም በወሊድ ጊዜ ሰውነታቸው ይከፋፈታልና እኩይ መንፈስ እንዳይጣባቸው ብሎ በማሰብ ይህ በአንገት የሚታሰር መከላከያ እንደሚታሰርላቸው ጠልሳሚ አዕመረ ገልጸዋል (ሐምሌ 26/2012፣ 8፡40)።

### **4.3.** የጠልሰም ስዕል የመሳል ማዕከላዊ እሳቤ

የጠልሰም ስዕላት በተለያዩ መናፍስት አልፎ አልፎም በመላእክት እና በቅዱሳን ሥዕላት የታጀቡ ናቸው። ሥዕላት ባይካተቱባቸውና አስማት ብቻ ቢኖራቸውም ጠልሰምነታቸውን አይለቁም። ምክንያቱም ጠልሰም የሚያሰኛቸው በውስጣቸው የሚይዙት ኅቡእ ስሞችን የያዙ አስማት እና ኃይላቸው እንጂ ሥዕላቱ ብቻ አይደሉም። ቄስ ኪሮስ ስለ ጠልሰም ሥዕላት የሚከተለውን ሃሳብ ገልጸዋል።

> ጠልሰም ሳዘጋጅ ስዕላት እጠቀማለሁ ብዙ ጊዜ የምስለው የመላእክትን ስዕል ነው። ምክንያቱም ጠልሰሙ ለሚዘጋጅላቸው ሰዎች ጠባቂ መላእክትን አጋዥ አድርጌ ስለምወስድ ነው። ያስፈልጋቸዋል ብዬ ስለማምን። በሌላ መልኩ ደግሞ ራሴ አስቤ በአዕምሮዬ የበሽታውን

የመንፈስ ስዕል አካል አላብሼ በተለያየ መንገድ በሚያስፈራ መንገድ እስላለሁ። ይህ ማለት መላእክት ዝቅ ብሎ ደግሞ ዕኩዩ መናፍስት ይወከላል ብዬ ነው የማስበው። በብራናው ወይም በወረቀቱ እጠለስማለሁ። የቅዱሳኑን ስዕል መጀመርያ ማድረጌ ከታች ያለውን እኩይ መንፈስ ይረግጠዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው። መንፈሱን መሀል አድርጌ አስማቱን ላይና ታች መጻፍ ደግሞ ኃል ያለው አስማት መንፈሱን ያስረዋል ብዬ ስለማምን ነው (ነሐሴ 3/2012፣ 4፡23)።

ከላይ እንደተገለጸው የጠልሰምን ጥበብ ልዩ የሚደርገው የማይታዩና ረቂቅ የሆኑ እኩይ መናፍስትን ሳይቀር ሥግው አድርጎ የመሳልና የመገተብ ልማዱ ነው። ይህ ደግሞ አንድም መናፍስቱን በኃያላን አስማት ማሰር ይቻላል ሚለውን ዕምነት ለማስረጽ አንድም ደግሞ መናፍስቱን ያለመፍራትና ያለመደንገት ሥነ ልቡናዊ ግንባታን በሕመምተናው ላይ ለማምጣት ታልሞ ሚደረግ ተግባር ነው። ለአንድ ጠልሰም ሥዕል ግዴታ እንዳልሆነና የጠልሰም ዋናው ጉዳይ ጸሎቱና አስማቱ መሆኑን ደግሞ ቄስ ደሳለኝ ገልጸዋል።

> ብዙ ጊዜ ጠልሰም ሳዘጋጅ ሥዕላትን መጠቀም ግዴታ እንደሆነ አላስብም። ሆኖም ግን መናፍስቱን መሳል ካለመሳል የተሸለ ጥቅም ለሕመምተናው ስላለው መሳልን እመርጣለሁ። ምክንያቱም ታማሚው ሥዕሉን ሲያይ የተጣባው መንፈስ ሊታይ የሚችል መሆኑን ያስባል። ይህን ሲያስብ ደግሞ ሊሸነፍና ሊታሰር የሚችል መንፈስ መሆኑንም ጭምር ያስባል (ነሐሴ 3/2012፣ 4፡55)።

## 4.4. በሽታን የመለያ ዘዴ

ጠልሳሚያን የሕመምተኛውን የሕመም ዓይነት የመለየት ሥራን የሚሰሩት ለጠልሰም መስሪያነት የሚሆነው ቤዛ እንስሳ ታርዶና የሚፈጸመው ሥርዓት ተካሂዶ ቆዳው ከመላኩ በፊት ነው። አስቀድመው ሕመሙን ከለዩና ካወቁ በኋላ ኮከቡ ተነቦና እጣ ክፍሉ ተለይቶ ቤዛ እንዲቀርብለት ያደርጋሉ። በጠልሰም መድኃኒትነት የሚታከሙ የመናፍስት ሕመሞች በርካታ ናቸው። አንድ ሰው መናፍስት ተጣብተውት ሲመጣ ዛር፣ ቡዳ፣ አጋንንት፣ ስራይ አሊያም ሾተላይ መሆኑን እንደምን ባለ ሁኔታ ትለያላችሁ? ለሚለው ጥያቄ ቄስ ኪሮስ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

> ብዙ ጊዜ በማየት የምንለይበት ሁኔታ ነው ያለው። አስቀድሜ ምመለከተው የሕመምተኛውን የዓይን እውታር ነው። አንድ ጅማት ከሆነ ገና ሕመሙ ያልጠናበት ነው። ሶስት አራት እውታር ከሆነ ደግሞ ወይም ከአራት እስከ ሰባት ቀን ሀያ ጅማት ከደረሰ ሕመሙ ወር አልፏል ብለን የተጠናወተውን እኩይ መንፈስ ስም ለመስጠትና ዓይነቱን ለመለየት ይረዳናል። አልፎ አልፎም ዓውደ ነገስትን በመግለጥ የታመመው ሰው እና የእናቱ

ስም የእያንዳንዱን ቁጥር በመጻፍና በመግደፍ የምትቀረዋን ቁጥር በመያዝ እንዴት ያለ ተፈጥሮ እንዳለውና ምን ዓይነት መንፈስ ሊያዘው እንደሚችል ሊጣላውና ላይጥመው የሚችለውን መንፈስ ማወቅና ለይቼ ጠልሰሙን ለመጠልሰም ይረዳኛል (ሐምሌ 02/2012፣ 9፡30)

ዓውደ ነገስትን መግለጥ አሊያም እንዲሁ በመመልከት ሕመምን መለየት እንደሚቻል ከላይ የሰፈረው ሃሳብ ያስረዳል። የኣይ መስመር መሰል ጅማቶችን ቁጥርና ብዛት በማየት የሕመሙን የክብደትና የቅለት ደረጃ ጭምር ማጤን እንደሚቻላ ሃሳቡ ያስረዳል። ስለሁኔታው መረጌታ ደሳለኝና ጠልሳሚ አዕመረ ጸሐዬ የተናገሩትም ከላይ ከሰፈረው ሃሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው። በማየት ማወቅ ሲያዳግትና አንዳንድ ጊዜም ራሱን በታማሚው ውጫዊ አካል ላይ አንዳች ምልክት ትቶ የማያልፍ መንፈስ ሲገጥም የግድ ዓውደ ነገስትን ለመግለጥ ይገደዳሉ።

ይህ በሽታን የመለያ ዘዴ ለሁሉም የጠልሰም መድኃኒት ህመሞች የሚሰራ ነው። ማለትም አንድ ታማሚ ሾተላይም ሆነ አይነጥላ አሊያም ሌላ ከመንፈስ ጋር የተያያዘ ህመም ገጥሞት ቢመጣ ጠልሳሚያኑ ዓይኑን በማየት እንዲሁም ህመምተኛው የሚሰሙትን ሰሜቶች በመጠየቅ ይረዳሉ። ህመምተናው ስሜቱን በግልጽ መናገር የማይችልበት ሁኔታ ላይ ከሆነ አሊያም ዓይኑንም ጭምር በማየት ማወቅ ካልተቻለ አውደ ነገስትን ገልጦ ኮከብ በመቁጠር ይታወቃል። ስለሆነም ይህ ዓይነቱ ሕመምን የመለያ ዘዴ ለሁሉም ሕመሞች ይሰራል።

ጠልሳሚያን ልክ እንደ ጠልሰም አሰራር ጥበብ ሁሉ የሕመም መለያ ዘዴንም ጭምር ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ ልማድ ይማሩታል። ዓውደ ነገስት ተገልጦ እንደምን ባለ ሁኔታ የሕመምተኛውንና የእናት ስም አቀናጅቶ እጣ ክፍል ቁጥርን ማውጣት እንደሚቻልና ቁጥሩን መሰረት በማድረግ ኮከብን ቆጥሮ የሰውን ማንነት ማወቅ እንደሚቻልም ቃላዊና ተግባራዊ በሆነ መንገድ ለእነሱ እውቀቱን ካስተላለፉ መምህራን ይማራሉ። በዚህ ሙያ ላይ ረጅም ዓት በመቆየት ብዛትም አልፎ አልፎ ያራሳቸውን ልምድና ተሞክሮ በመጨመር የሕመም መለያ መንገዳቸውን እያዳበሩ እንደሚሄዱም ጠልሳሚያኑ ያስረዳሉ።

### 4.5. የጠልሰም መድሃኒትነት

ጠልሰም የተለያዩ አገልግሎቶች አሉት ከነዚህም ውስጥ መድሃኒትነት አንዱ ነው። በፃታ ማህበረሰብ ዘንድ በጠልሰም መድኃኒትነት አማካይነት የሚፈወሱ ህመሞች አብዛኞቹ ከማይታዩ መናፍስት ጋር የተያያዙ ህመሞች ናቸው። ለፈውስ የሚከወኑት ጸሎቶች ብሎም ክዋኔዎችም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። በጠልሰም መድሃኒትነት ይፈወሳሉ ወይም ይድናሉ ተብለው የሚታሰቡ በርካታ ህመሞች አሉ።

ከእነዚህም መካከል ሾተላይ፣ ዓይነ ጥላ (ሕጻናትን ገዳይ በሽታ)፣ ገርጋሪ፣ ዓይነ ወርቅ፣ ደም መፍሰስ፣ ማዕሰረ አጋንንት፣ መግረሬ ጸር፣ ዛር ማውገዣ፣ ዛር ማስታረቂያ፣ መፍትሔ ስራይ፣ መድፍነ ጸር እና መስጥመ አጋንንት ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ህመሞች ከላይ የጠልሰም ዓይነቶች ብለን ከዘረዘርናቸው ውስጥ አንዱን በመጠቀም የሚፈጸሙ ናቸው። ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ሕመሞች ተጠቅተው ሲመጡ ጠልሰም የሚጠለሰምላቸው አካላት ዕድሜያቸው ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ሰዎች ናቸው። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ እነዚህ ሰዎች የሚዋረሳቸውን መናፍስት ለመከላከልም፣ ለመለማመንም፣ ለማውገዝም ጭምር አመቺ ናቸው ተብሎ ይታሰባልና ጸሎቱና የፈውስ ሥርዓት ክዋኔው ይደረግላቸዋል። ስለሆነም የእያንዳንዳቸውን ህመሞች ሥርዓተ ክዋኔ፣ ጸሎት እና ማብራሪያ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል።

### **4.5.1.** ሾተላይ

ሾተላይ ህጻናትን ለሚገድል የመንፈስ ህመም የተሰጠ ስያሜ ነው። ለዚህ በሽታ የሚዘጋጅ ጠልሰም የራሱ የሆነ አዘገጃጀት እና መለያ ያለው ሲሆን በዚህ በሽታ የሚቃጠቃው መንፈስም "ውርዝልያ" ተብላ እንደምትጠር ጠልሳሚ መሪ ጌታ ደሳለኝ ገብረ ሚካኤል ያትታሉ። ስለ በሽታው ሁኔታና አጠለሳሰም ሁኔታም እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> *ጠልሰም ውርዝልያ ለምትባል እኩይ መንፈስ፤ ለሾተላይ ማለትም ሕፃናትን ለሚገድል መንፈስ መከላከያና መፍትሔ ነው። ሱስንዮስ የሚባል ሰው ልጁ በዚህች ውርዝልያ በተባለችው መንፈስ ልጁ ስለሞተበት "ውርዝልያ የምትባለውን ሕፃናት ገዳይ እንዳጠፋት ሥልጣን ሰጠኝ" ብሎ ወደ እግዚያብሔር ጽልዮ ከእግዚአብሔር ሥልጣን አገኘ። የሕፃናት ገዳይ መንፈስንም አስወገደ። (እንደምን ባለ ሁኔታ መንፈሷን እንዳስወገደ በሚታሰረው የጠልሰም ጸሎት ላይ በስፋት ሰፍሮ ይገኛል)። ነገር ግን ሱስንዮስ ከሞተ በኋላ የሕፃናት ገዳይ ሾተላይ እኩይ መንፈስ እንደገና ስላገረሸ አባቶች የሱስንዮስ ገድል በጠልሰም ጽፈን ለእናቶች ብናሥር መድኃኒት ይሆናል ብለው ሕፃናት ለሚሞትባቸው እናቶች እየጻፉ ማሠር ጀመሩ (መሪጌታ ደሳለኝ ኪሮስ፣ ነሀሴ 27/2012፣ 4፡30)።*

ይህ ለሾተላይ ሕመም መጽኃኒት የሚሆነው ጠልሰም የራሱ የሆነ ይዘት አለው። ይዘቱም ምን እንደሚመስል ጠልሳሚ መምህር አዕመረ ፀሓዩ እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> *ጸሎት በእንተ ሾተላይ ገድል ወስምዕ ዘቅዱስ ሱስንዮስ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘስሙ ሱስንዮስ ወአውሰበ አሐተ ብእሲተ ወወለደት ወልደ ተባዕተ ወእንስተ ወለቀዳማይ ወልዱ ቦአት*

ውርዝልያ ወቀተለቶ ወከልሐት እሙ ወበከየት ወሶበ ስምዐ ቅዱስ ሱስንዮስ ዘንተ ነገረ ወይቤላ ለብእሲቱ ምንት ያበክየኪ ኦ ብእሲቶ ወትቤሎ እስመ ውርዝልያ መጽአት ወቀተለቶ ለወልድየ ወሶበ ሰምዐ ቅዱስ ሱስንዮስ ዘንተ ነገረ ተጽዕነ ዲበ ፈረሱ ወነሥአኩናቶ በየማን ወፅአ ወሐረ ከመይቅትላ ለውርዝልያ ከመኢትቅትል ሕፃናት እለ ይጠብው ጥበ ወረከባ ለውርዝልያ ነቢራ ታሕተ አም እንዘ የሀውድዋ ብዙኃን አጋንንት ወመናፍስት ርኩሳን ወቦቤሃ ወረደ ቅዱስ ሱስንዮስ እምላዕለ ፈረሱ ወሜጠ ገጸመንገሰ ምሥራቅ ወሰፍሐ እደዊሁ ወሰገደ ኀበ እግዚአብሔር ወጸለየ እንዘይብል አምላከ ሰማያት ወምድር ሰማዕ ጽሎትየ ለእመ ቦአት ውርዝልያ አምታሕተ እደውየ እምቀተልክዋ ከመ ኢትቅትል ሕፃናት እለይጠብው ጥበ አንሰ አሐውር ወእከውን ሰማዕተ በስምከ ቅዱስ ወእዘ ይዴሊ ከመዝወይስእል ኀበ እግዚአብሔር መጽአቃል እምሰማይ ዘይብል ኦሱስንዮስ ተሰምዐ ጽሎትከ እምኀበ እግዚአብሔር ከመትንሥአ ለውርዝልያ ወትግበር ዘፈቀድከ ወሶበ ስምዐ ቅዱስ ሱስንዮስ ዘንተ ቃለ እምኀበ እግዚአብሔር ተፈሥሐ ጥቀ ወሰገደ ቅድመ እግዚአብሔር አምላኩ ተጽዕነ ዲበፈረሱ ካእከ ወሖረ ኀበ ውርዝልያ ከመይቅትላ፤ ይእቲስ ከልሐት ወበከየት እንዘትብል አንሰ ኢየሐውር ኀበ ተጸውዐ ስምከ ወኀበተገብረ ተዝካርከ እመሂ ቤት አውቤተ ክርስቲያን እመሂ ብእሲ ውብእሲት ዘጸረ መጽሐፈ ፀሎትከ ኢየሐውር ኀቤሁ በመዓልተ ወበሌሊት እመሂ በቀትር ወቅዱስ ስሰኮነ ሰማዕተ በስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ አአምላከ ቅዱስ ሱስንዮስ ዕቀብዐ ወድንና ለአመትከ እገሌ እምሕማመ ሾተላይ እስመ  አልቦ ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር።

## የጸሎቱ ትርጉም


የሾተላይ ጸሎት የቅዱስ ሱስንዮስ ገድልና ምስክርነት። ሱስንዮስ የሚባል አንድ ሰው ነበር እንዲት ሴት አገባ፣ ሴትና ወንድ ልጅም ወለደችለት፤ የመጀመሪያውን ልጅ ውርዝልያ ገብታ ገደለችው፤ እናቱ እየጨኸች አለቀሰች፤ ቅዱስ ሱስንዮስ ይኸን በሰማ ጊዜ "ሴትዮ ምን ያስለቅስሻል?" አላት፤ "ውርዝልያ መጥታ ልጄን ገደለችው" አለችው ቅዱስ ሱስንዮስ ይኸን ነገር በሰማ ጊዜ በፈረሱ ላይ ተቀምጦ ጦሩን በቀኝ እጁ ይዞ ጡት የሚጠቡ ሕፃናትን እንዳትገድል ውርዝልያን ይገድላት ዘንድ ወጥቶ ሔደ፤ ውርዝልያን በዛፍ ሥር ተቀምጣ ብዙ አጋንንት ርኩሳን መናፍስት ከበዋት አገኘ፤ ያን ጊዜ ቅዱስ ሱስንዮስ ከፈረሱ ላይ ወርዶ ፊቱን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ መልሶ እጆቹን ዘርግቶ ወደ እግዚአብሔር ሰገደ። የሰማይና የምድር አምላክ ጸሎቴን ሰማኝ እያለ ጸለየ። "ጡት የሚጠቡ ሕፃናትን እንዳትገድል ውርዝልያ በእጆቼ ላይ ብትገባ በገደልኳት ነበር" እያለ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። "እኔ ሔጄ በቅዱስ ስምህ ሰማዕት እኾናለሁ።" እያለ ጸለየ። እንደዚህ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ "ውርዝልያን


እንድትይዛትና የፈለግሽውን እንድታደርግ ጸሎትህ በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰምቷል።" የሚል ቃል ከወደሰማይ መጣ፤ ቅዱስ ሱስንዮስ ይኸን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ በሰማ ጊዜ እጅግ ደስ ብሎት በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት ሰገደ።

ዳግመኛ በፈረሱ ላይ ተቀምጦ ይገድላት ዘንድ ወደ ውርዝልያ ሔደ። እርሷ ግን "ስምህ ወደ ተጠራበት መታሰቢያህ ወደ ሚደረግበት ቤትም ቢኾን፣ ቤተክርስቲያንም ቢኾን የጸሎትህን መጽሐፍ ወደ ተሸከመ (ወደ አሠረ) ወንድም ቢኾን ሴትም ቢኾን በቀትር በቀን በሌሊትም ቢኾን ወደርሱ አልሔድም።" እያለች ጮኸች፤ አለቀሰች። ቅዱስ ሱስንዮስም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰማዕት ኾነ። የቅዱስ ስስንዮስ አምላክ ሆይ አገልጋይኽ ዕገሌን ከሾተላይ በሽታ አድናት ጡብቃት ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና (ጠልሳሚ አእመረ ፀሐዬ፣ ነሐሴ 28፣ 8፡20)።

ከላይ በግዕዝ ቋንቋ ተጽፎ በጠልሳሚው ወደ አማርኛ ቋንቋ የተተረጐመው አስማት ወይም ጸሎት ሲጤን ቅዱስ ሱስንዮስ ለልጁ ሞት ምክንያት የሆነችውን ውርዝልያን ለማጥፋት ወደ ፈጣሪው ወደ እግዚአብሔር እንደተማፀነ ያመለክታል። በሱስንዮስ ገድል የተሰተዋለው ጠልሰማዊ ጹሑፍ ይዘት ከክርስትና ሃይማኖት ጋር የተያያዘ መሰረትነት አለው።

ሾተላይ እየተባለ በዖታ ማህበረሰብ የሚታወቀው ሕፃናት ገዳይ ረቂቅ በሽታ በአንድ በኩል ሊታይና ሊዳሰስ የማይችል በሰዎች ሥነ-ልቦናዊ አመለካከት የሚታመን ህመም ነው። በአንድ በኩል ደግሞ ይህ ሕፃናት ገዳይ መንፈስ የተቀራኛት በዓይን ልትታይ የምትችል ውርዝልያ የምትባል ፍጡር እንደነበረች የሚያመላክት ነገር አለ። በጠልሰሙ ላይ የተጠቀሰውም ይህን ያስረግጣል። ሱስንዮስ ይህችን መንፈስ እንዳያት በገድሉ ሰፍሯል። ከዚህ በመነሳትም በጠልሰሙ ላይ የዚህች መንፈስ ወካይ የሆነ ሥዕል (መንፈሷ) ይሳላል።





ሥዕል **4.1**፦ በወረቀት የተሳለ የውርዝልያ ሥዕል

ሥዕል **4.2**፦ በብራና የተሳለ የውርዝልያ ሥዕል

ከላይ በሥዕል 1 እና 2 እንደሰፈረው ለሾተላይ ሕመምተኛዋ በሚሰጠው ጠልሰም ላይ የውርዝልያ ሥዕል ይሳላል። ይህ የሚሆነውም የሚታይና የሚጨበጥ ነገር አይፈራምና ሕመምተኛው እንዳይጨነቅና እንዳይፈራ መፈወሱንም እንዲያምን የማድረግ ሥነልቡናዊ ሚና አለው ተብሎ ያታመናል። ለዚህች መንፈስ የሚጠለሰመው ጠልሰም በወገብ የሚታሰር የጠልሰም ዓይነት ሲሆን ሕመሙ ባጠቃት ሴት ወገብ ላይ ከዚህ በታች በቀረበው የፎቶ ማስረጃ ላይ መመልከት በሚቻለው መልኩ ይታሰራል። ለሾተላይ የሚሆን መድኃኒት ሲሰራ ጠልሰሙ የሚጠለሰምበት ቆዳ የሚመረጠው ከላይ የጠልሰም ግብዓቶችና የሚሰጡበት ሥርዓት በሚለው ርዕስ ስር ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ነው። ቆዳው በአዋቂዎች ተመርጦ ቤዛው ታርዶና ሥጋው ተበልቶ ቆዳው ለጠልሳሚዎች ተሰጥቶ ቆዳው ለመጠልሰሚያነት እንዲሆን ተደርጎ ከተዘጋጀ በኋላ ከላይ የሰፈረው ጸሎት በጠልሰሙ ላይ ይጠለሰማል። ይህ የተጠለሰመው ጠልሰም ሾተላይ ሕመም በያዛት ሴት ላይ ይታሰራል። ሲታሰር ቄጤማ ተጎዝጉዞና ቡና ተፈልቶ ጸሎቱ እየተደገመ በታማሚዋ ጭንቅላት ላይ የተጠለሰመውን መድኃኒት 3 ጊዜ አሊያም 7 ጊዜ ጠልሳሚው ካዞረ በኋላ በወገቧ ላይ ይታሰራል።



ሥዕል **4.3፡-** የሾተላይ ጠልሰም በወገቧ የታሰረላት ሴት

በዚህ በሾተላይ ሕመም ተጠቅተው ጠልሰም ተጠልስሞላቸው ፈውስን ካገኙ መካከል ሰዎች ወ/ሮ አለሚቱ ጫኔ አንዷ ናት። ስለ ሕመሟ ምልክትና ስለተሰጣት መድሃኒት ብሎም ስላገኘችው ፈውስ የሚከተለውን ገልጻለች።

> “እኔ ስሜ አለሚቱ ጫኔ ይባላል። ዕድሜየ 31 ነው የፊታችን ሚያዚያ ሲመጣ ማለት ነው። ከባለተቤቴ ጋር ከተጋባን 5 አመት ከመንፈቅ ሁኖናል። ልጅ የመውለዱ ጉዳይ አስቸገሮኝ ነበር የኖረው። ጽንስ ከቋጠርኩማ 6 ወር ሳይሞላኝ ፅንሱ ጨነገፈ፣ወረደብኝ። ከማህጠኔ እንደው ቢጫ የመሰለ ፈሳሽ ይፈስኝ ነበር። ልብ ድካሙ፣ ለመተንፈስ መቸገር እና ሆድን ቅትት አርጎ ይነፋኝ ነበር። ከዚያማ ቤተሰቡም ጎረቤቱም ተደናገጠ። ኋላ እኛው ቀበሌ ግድም አንድ ደብተራ ነበሩ ለእሳቸው ስንነግራቸው ሁለመናየን አዩና ይሄማ ሾተላይ አደለ ብለው በቆዳ የተጠቀለለ መደሃኒት ወገቤ ላይ አሰሩልኝ። ከዚያ ልጅ እወልዳለሁ ብየ ደስተኛ ነበርኩ። እግዜር ይመስገን ነው እንጅ ተያ ቡሃላ ፅንሱ ረግቶ፣ሽል ሆኖ ልጅ ለመውለድ ቻልኩ” (ሐምሌ 3/2012፣ 4፡27)።

መረጃ ሰጪዋ እንደገለጸችው በወገቢ ላይ በታሰረላት ጠልሰም መድሃኒት አማካይነት ከሕመሚ ተፈውሳ ልጅ መውለድ እንደቻለች ገልጻለች። ይህ ጠልሰም መድኃኒት ለተወሰኑ ጊዜያት ድረስ በጥንቃቄ መታሰር ይኖርበታል። ፈውስነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ማውለቅ የሚቻል ቢሆንም በብዛት ግን መንፈሱ መለሳል ተብሎ ስለሚታሰብ በመቀነታቸው አሊያም በአንዳች መያሻ ውስጥ አድርገው ይይዙታል።

### **4.5.2** ለዓይነ ጥላ ወይም ለገርጋሪ መንፈስ

ለመድኃኒትነት ከሚኾኑ ጠልሰሞች አንዱ ለዓይነ ጥላ ወይም ለገርጋሪ መንፈስ መፍትሔነት የማዘጋጀው ጠልሰም ምን እንደሚመስል ጠልሳሚ መምህር አእመረ ፀሐዩና ጠልሳሚ መሪጌታ ደሳለኝ ገብረ ሚካኤል፣ ጠልሳሚ መሪጌታ አፈወርቅ ነጋሽና ጠልሳሚ ቄስ ኪሮስ አሰፋ የሚከተለውን ተናግረዋል።

> ዓይነ ጥላ ማለት ሰዎች በሕይወታቸው ስኬታማ እንዳይኾኑ በትዳር፣ በሥራ ዓለም፣ ገንዘብ በማግኘት ሰዎች ጋር ተግባብተው በመሥራት ወዘተርፈ ውጤታማ እንዳይኾኑ የሚያደርግ ይኸ እኩይ መንፈስ ነው፣ ዓይነ ጥላ በሰዎች ላይ እንዲህ በአጋጣሚ ሊቆራኝ ይችላል፤አልያም ከሌላው ሰው ወደ አንዱ ሰው በመሸጋገር ሁለንተናዊ እድልን ሊከለከል የሚችል ነው ተብሎ ይታመናል፤ ለዚህ እኩይ መንፈስ በዋናኛነት መፍትሔ ይኾናል ተብሎ በእኛ የሚታሰበው ጸሎተ ንድራ በመባል የሚታውቀውና በጠልሰም የሚዘጋጀው አስማት ነው (መሪ ጌታ ደሳለኝ ገብረ ሚካኤል፣ ነሐሴ 27-2012፣ 8፡45)።

#### ጸሎተ ንድራ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፀሎት በእንተ ሕማመ ዓይነ ጥላ ወዓይነ ወርቅ ወገርጋሪ ወዓይነናንሰ ጸሎተ  ንድራ ዘውእቱ ሕማመ ዓይነ ጥላ ዘነገሮሙ እግዚእነ ለሐዋርያቲሁ ንጹሐን ወእነዘ የሐውር እግዚእነ ውስተ ባሕረ ጥብርያደስ ወመጽኡ ምስቤሁ ዐሥርቱ ወክልኤቱ አርዳኢሁ ወርእዩ መልክአብእሲት ዐሪጊት እንዘትነብር ዲበ መንበር ወይእቲ መፍርህት ወመደንግፅት ጥቀ እስመይበርቃ አዕይንቲሃ ከመ መብረቅ ወአእዳዊሂኒ ወአእጋሪሃኒ ከመ ሠረገላ እሳት ወይፅአእምአፋሃ ነበልባል መጠነ ስድሳምእት በእመታ መልአክ።

ለእመ ርእየት ፈረሰ ዘይረውድ ታወድቆ ፍጡነ ምስለ ዘይ ሴዐኖ ወለእመ ርእየት ሐመረ ዘየሐውር ዲበ ባሕር ትገናጽሎ ፍጠነ ወለእመ ርእየት ላሕመ እንዘ ትትሐሰብ ፍጡነ ይነጽፍ ሐሊባ ወይከውን ደመ ወለእመር እየት ብእሴ ወብእሲተ ምስለው ሱዶሙ ፍጡነ ትፈልጦሙ

ወታህጐሎሙ ወይቤልዎ አርዳኢሁ ለእግዚእነ ምንትኑ ዛቲ ዓይነ እኪት ወግርምት ወይቤሎሙ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በሉ አትሪኮን፣ በትሪኮን፣ ቦርፎሪካን፣ ጰሪከን፣ ርፎሪካን፣ አተርጋዎን፣ አኸያ፣ ሽራኸያ፣ በራኸያ፣ ኤልሻዳይ፣ አዶናይ፣ አካዕ፣ ክስብኤል፣ ብርስባሔል፣ አልፋ፣ ወኦ፣ ቤጣ፣ የውጣ፣ ለሐራሹን፣ ሐራፌፌኩር፣ በጠጁን፣ ዘሐጁን፣ ዋሕ፣ ሕርዋሕቅ፣ ኤል፣ ያፌጥን፣ ተሰኢላ፣ ሳዶር፣ አላዶር፣ ዳናት፣ አዴራ፣ ሮዳስ፣ ጭሐርር፣ ሴቃ፣ ቤቃ፣ ጼቃ፣ ራፎን፣ ራኮን፣ ጨልዋጭቅ፣ ሐሩ፣ ራኤል፣ ጸባዓት በአሉ አስማት አውዕይዋ በእሳት ወዝርውዋ በነፋስ ምሥራቀ ወምዕራብ ሰሜነ ወደቡብ ከመይጥፋዕ ወይሰስል ሕማመ ዓይነ ጥላ ዓይነ ወርቅ ዓይነ ነገርጋሪ ወዓይነ ናሕስ እምላዕለ አመት ከዕገሌ።

## የጸሎቱ ትርጉም

አንድ አምላክ በኸነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የዓይነጥላ፣ የዓይነ ወርቅና የዓይነ ናስ በሽታ ጽሎት የንድረ ጽሎት ይኸውም ፖይነ ጥላ የተባለው ነው፤ ጌታችን ንጹሐን ለኾኑ ሐዋርያቶቹ የነገራቸው መድኃኒት። ጌታችን ወደ ጥብርያዶስ ባሕር ሲሔድ ዓሥራ ኹለቱ ደቀ መዛሙርት መጡ:: በወንበር ላይ ተቀምጦ የአሮጊት ሴት መልክ ተመለከቱ፤ እርሷም እጅግ በጣም አስፈሪና አስደንጋጭ ናት፤ ዓይኖቿ እንደ መብረቅ ያንጸባርቃሉና። እጆቿም እንደ እሳት ሠረገላ ናቸው፤ በመልአኩ ክንድ ስድስት መቶ ርዝመት ያህል ከአፏ የእሳት ነበልባል ይምቦገቦጋል፤ የሚሮጥ ፈረስ ካየች ከተጫነው ሰው ጋራ ፈጥና ትጥለዋለች። በባሕር ላይ የሚሔድ መርከብ ካየችም ፈጥና ትገለብጠዋለች። ላም እየታለበች ካየች ፈጥኖ ወተቷ ይደርቃል ደምም ይኾናል፤ ባልና ሚስቶችን ከልጆቻቸው ጋራ ካየች ፈጥና ትለያቸዋል ታጠፋቸዋለች፤ ደቀመዛሙርቱ ጌታችንን “ይህች ክፉ ዓይን ያላት የምታስፈራ ምንድን ናት?” አሉት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም “የሚከተለውን አስማት በሉ” አላቸው። በእነዚህ አስማት ኃይል በእሳት አቃጥሏት፤ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ በነፋስ በትኗት ፤ የዚህች ዓይነ መጥፎ ስም አጠራር ይጠሩ ዘንድ። እንደርሷም ዓይነት ዓይነ ገርጋሪና ዓይነ ጥላ ከአገልጋይህ ዕገሊት/እገሌ ይራቅ ይወገድ።

ከፍሲል በግዕዝና በአማርኛ ትርጉም የተገለጸውና እንዲሁ ሳይተረጐም የተጠቀሰው አስማት ዓይነ ጥላ ለሚባለው በሽታ መከላከያ እንደኾነ መገንዘብ ተችሏል፤ ቀደም ሲል በተዳሰሱት የጠልሰም ጽሑፎች እንደተጠቆመው ይኸም የዓይነ ጥላና የዓይነ ገርጋሪ መድኃኒት ምንጭ ሃይማኖታዊ ነው በሚባል ደረጃ

ለመናገር የማያስችል ኹኔታ ያለው ይመስላል ምክንያቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ከእርሱ ጋር ወደ ጥብርያዶስ ባሕር እየሔዱ እያለ በአፈጣጠሯ የተለየች፤ አስፈሪና ያየችውን ኹሉ ለአደጋ የምታጋልጥ የምትገረግር ልዕለ ተፈጥሯዊ መልክና ቅርፅ ያላት አሮጊት ሴት መሰል ነገር እንደተመለከቱ ያትታል። ይህች መጥፎ ፍጥረት ምንድን ናት መፍትሔውስ ምንድን ነው? ብለው ክርስቶስን እንደ ጠየቁትና እርሷ የምትሸነፍበትን አስማታዊ ኃይል እንደነገራቸው ይመለከታል። በሌላ በኩል ዐሥራ ኹለቱ ደቀ መዛሙርት ወይም ከደቀ መዛሙርቱ በከፊል በጥብርያዶስ ወንዝ አካባቢ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተነጋገሩት ስለዓሣ ማጥመድ እንደኾነ በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል።

> ወእምዝ ካዕበ አስተርአዮሙ እግዚእ እየሱስ ለአርዳኢሁ በብሔረ ጥብርያዶስ ወከመዝ አስተርአዮሙ እንዘ ሀለው ኅቡረ ስምዓን ጴጥሮስ ወቶማስ ዘይብልዎ ዲዲሞስ ወናትናኤ (ከዚህ በኋላ ጌታ ኢየሱስ በጥብርያዶስ አካባቢ ለደቀመዛሙርቱ ታያቸው፤ ስምዓን የተባለ ጴጥሮስ፣ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስና ናትናኤል በአንድነት እያሉ ታያቸው።

ይላል፣ በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ከመካከላቸው ተነሥቶ ዓሣ ለማጥመድ ወደ ባሕሩ እንደወረደ ሌሎቹም ደቀመዛሙርት አብረው ወደ ባሕሩ እንደ ወረዱ ያመለከታል። ነገር ግን ዓሣ ለማሥገር ብዙ ቢደክሙም ዓሣ መያዝ እንዳልቻሉም ያስረዳል፤ ከነጋ በኋላ ጌታ ኢየሱስ በሐይቁ አካባቢ ቆሞ ስለነበረ ዐውቀውት ወደ እርሱ ሲመለከቱ ልጆቼ የሚበላ ነገር አላችሁ አላቸው፤ እነርሱም ሌሊቱም ሙሉ ዓሣ ለማሥገር ደክመው አንድ ዓሣ እንኳን መያዝ እዳቃታቸው ነገሩት፤ የዓሣ ማጥመጃችሁን በመርከቡ በቀኝ በኩል አጥልቁ ካላቸው በኋላ ብዙ ዓሣ በማጥመጃው ውስጥ በመግባቱ ዓሣውን መሳብ እንዳቃታቸው ያትታል (ዮሐ 21፣1-8)።

ከዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አንጻር ከፍ ሲል የተገለጸው አስማት ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በጥብርያዶስ የነገራቸው የዓይነ ጥላ ሕመም መከላከያ የተባለው ምንጭ ሃይማኖታዊ (መጽሐፍ ቅዱሳዊ) ነው ብሎ ለመወለድ ያስቸግራል። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ በጥብርያዶስ ወንዝ የተነጋገሩት ዋና ምንጭ ውስጥ አስማታዊና ምትሐታዊ ጽሑፉ ስለማይገኝ ነው፤ ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይ በሐዲስ ኪዳን ሕማመ ሌጌዎን፤ሕማመ ነገርጋር ፤ጋኔን ወዘተ. የሚሉ ቃላት ይገኛሉ፤ እንደዚሁም ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ በዚህ ምድር እየተዘዋወረ ሲያስተምር የተለያየ የመናፍስት ርኩሳን ሕመም ያደረባቸው ሰዎችን በተአምራት ይፈውስ እንደነበረ ከብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል፣ ለምሳሌ ማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 5፣1 "በእንተ ሌጌዎን በማርቆስ ወንጌለ ምዕራፍ 9፣17 ላይ ደግሞ በእንተ ዘነገርጋር" የሚሉ አንቀጾች ይስተዋላሉ፤ እነዚህን መናፍስታዊ ሕመሞች ደቀመዛሙርቱ መፈወስ

ሲያቅታቸው ለምንድን ነው እኛ መፈወስ ያቃተን ብለው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥያቄ ያቀረቡባቸው አንቀጾች እንደሆኑ ይታወቃሉ።


ለእነዚህም ጥያቄዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የመለሰላቸው "ይህ ሌጌዎን ወይም ነገርጋር የሚባለው እኩይ መንፈስ የሚሸነፈው በጾምና በጸሎት ነው፤ እናንተ ማስለቀቅ ያልቻላችሁትም ፍጹም አማኞች ስላልሆናችሁ ነው" የሚል እንደሆነ ያስረዳል። ስለዚህ ቀደም ሲል ''ጽሎተ ንድራ'' በሚል የተገለጸውና በዚህ የተነገረው አይገናኝም ስለኾነም ከዚህ ዋና ምንጭ በመነሳት ጥንታዊያን ጠልሳሚዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከኢየሱስ ክርስቶስና ከደቀ መዛሙርቱ ንግግር በማስታከክ የደረሱት ፈጠራዊ ጽርሰን ነው ለማለት ያዳዳል። ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ያልተጻፈ ይኖር ይኾን? የሚል ጥያቄም የሚያስነሣ ነው፤ ምክንያቱም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21፣21 ላይ ያለውን እንመልከት።

> "ወዘንተ ገብረ እግዚእ እየሱስ ወቦ ባዕዳትኒ ብዙኃት ግብራት ዘገብረ እግዚእ እየሱስ ወሶበ ተጽሕፈ ኩሉ በበአሐዱ እመአያገመሮ ዓለም ጥቀ ለመጻሕፍቲሁ ዘተጽሕፈ"

(ይህን ጌታ ኢየሱስ አደረገ ጌታ ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎች ብዙ ሥራዎች አሉ ሁሉም እያንዳንዱ ቢጻፍ የተጻፋትን መጻሕፍት ዓለም ባልቻለም ነበር) (ዮሐ 21፣21)።

በዚህ የተጠቀመውን ስናጤን ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ወይም የሠራው ብዙ እንደኾነ፤ በጽሑፍ ያልሰፈረ በቃል እየተነገረ ከትውልድ ወደ ትውልድ የመጣ ሊኾን ይችላል የሚል ግምት እንዲኖር ያደረጋል፤ ጠልሳሚያን ከእነርሱ አስቀድመው ከነበሩት ሰዎች በተዋረድ የተቀበሉት ሊኾን ይችላል ወደሚል ድምዳሜ ይወሰዳል።

ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ "ይህን አስማት በሉ በዚህ አስማት ይህችን ለህመም ምክንያት የሆነችውን ዓይነ ጥላ በእሳት አቃጥሏት በነፋስም በትኗት አላቸው" የሚለው አስማት ሰፊ ዘት ያለው ነው። ለምሳሌ በጸሎቱ ውስጥ አኽያ፣ ሸራኽያ፣ ኤልሻዳይ፣ ጸባኦት፣ ሳዶር፣ አላዶር፣ ዳናት፣ አዴራ እና ሮዳስ ወዘተ. ይገኙበታል። እነዚህ አስማት የእብራይስጥ ቃላት ሲሆኑ ትርጉማቸውም የመገመርያና የመጨረሻ፣ አሸናፊ፣ ጌታ፣ ኃይል፣ ሁሉንቻይ ወዘተ. ሲሆን ምንጫቸውም የእብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለሆነም የጻታ ነዋሪዎች እነዚህ ስሞች ስመ አምላክ ወይም የአምላክ ስም በመሆናቸው በአስማቱ መለኮታዊ ኃይል ከሕመም መዳን ይቻላል፤ ይፈውሳሉም ብለው ያምናሉ።




*ሥዕል* **4.4፡-** በወረቀት የተጠለሰመ የንድራ ሥዕል

ከላይ የቀረበው ሥዕል የንድራ ሥዕል ሲሆን ለዓይነ ጥላና ለገርጋሪ እንዲሁም ለዓይነ ናስ እና ለዓይነ ወርቅ ሕመም መፍትሔነት የሚጻፈው ጠልሰማዊ ጽሑፍ ከሐይማኖታዊ ይዘት ንክኪ የለውም ብሎ ለመደምደም አያስደፍርም።

በዚህ ሕመም የተጠቃን ሰው ጠልሳሚያን በሚያውቁት ሕመሙን ከለዩ በኋላ በምዕራፉ መጀመርያ ባለው ርዕስ ስር በተገለጸው መንገድ ቤዛ የሚሆነው እንስሳ ቆዳ ተመርጦ ቆዳው ለጠልሰምነት ይዘጋጃል። ከዚህ በኋላ ጠልሳሚው ወደ ሕመምተኛው ቤት ይሔዳል። የቁብ ዶሮ እንቁላል ይዘጋጃል፣ ፍጹም ቁጥሮች ናቸው ተብለው ይታሰባሉና ሶስት ወይም ሰባት ዛጎል ይዘጋጃል እንዲሁም ሎሚ ይዘጋጃል። የዶሮው እንቁላል ተከፍሎ እስኳሉ እንዲፈስ ይደረጋል። ከዚህ በኋላም ዛጎሉን አሳርሮ በመቁላት እንዲፈጭ ይደረጋል። ይህ ከሆነ በኋላም የዛጎሉ ዱቄትና የሎሚው ውሃ ከእንቁላሉ ቅርፊት ውስጥ ይጨመራል፤ ወዲያውም በሕመምተኛው እናት ላይ ይቀመጣል። ከዚህ በኋላም ከላይ “ጸሎተ ንድራ” ተብሎ የሰፈረውን ጸሎት ጠልሳሚው 3 ጊዜ ይደግማል። የተቀላቀለው ሎሚ፣ ዛጎልና እንቁላልም ሕመምተኛው ጭንቅላት ላይ እንዳለ እየፈላ ይፈሳል። ይህ መሆኑም አይነጥላው እንዲህ እየፈላ ወጣ የሚል እንድምታ በማህበረሰቦቹ ዘንድ ይሰጠዋል።

ለአይነ ጥላ ወይም ለገርጋሪ የሚውለውን ጥሰማዊ መድሐኒት የተጠቀሙና ከዚህ ችግር ጋር ለብዙ ዐመታት የቆዩ የሁለት ሰዎች ተሞክሮ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል።

"እኔ አቶ አድማሴ ወልዱ እባላለሁ። በጻታ ወረዳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ ስሆን ሚስት ካገባሁበት ጊዜ ጀምሮ መግባባት የለነ፤ የምዘራው ቡቃያ ለፍሬ ሳይበቃ ሜዳ ላይ ይረግፋል። ምን ይሄ ብቻ ፍየሎች እና በጎች ነበሩኝ፤ ለመሸጥ ወደ ገበያ እሄድና ሌሎቹ ሽጠው ሲመለሱ የኔዎቹን ገዥዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሰበብ አድርገው ሳይገዙኝ ገርገሮብኝ ያውቃል። ስጨነቅ ጊዜነ በአካባቢያችን የሚኖሩ አዛውንት አማከርኳቸው እናም ጠልሰም ወደ ሚሰሩ ሰዎች ብሄድ መልካም እነደሆነ በነገሩኝ መሰረት በመሄዴ መፍትሄ አገኘሁ። መጀመሪያ በተለይ ጭንቅላቴ ላይ መድሃኒቱን ሲደረግልኝ ከላየ ላይ አንዳች ነገር ተነቅሎ እንደሄደ ሁሉ ሲቀለኝ ተሰማኝ ከዚያ በኋላ ሁሉም ነገር ተስተካክሎልኝ እየኖርሁ ነው።"

ስሜ ወ/ሮ ወርቅነሽ ንጉሴ ይባላል። የምኖረው በጻታ ወረዳ ነው። እድሜየ 50 ነው። ያጋጠመኝ ችግር ሰዎችን እኔን እንደሚጎዱኝ በማሰብ መራቅ፡ ከጎረቤት፣ ከዘመድ አዝማዶቸ ጋር አለመቀራረብ በተጨማሪም በቀበሌ ገበሬ ማህበሩ ስር ታቅፌ እንድሰራ ብመረጥም ፍርሀትና የሰውን ዓይን እንኳማየት ያስፈራኛል፣ ስጋት እና ጭንቀት እየተጠፈሩብኝ አስቸገረኝ። ስራውን እንኳ ለመስራት የምችል ብሆን። ወንድሜ የሚያውቃቸው ሰው ፈልገው መድሃኒት ካሰሩልኝ ጊዜ ጀምሮ ጥሩ መፍትሄ እየሁበት።"

እነዚህ ሁለት ሰዎች ገርጋሪ ሆኖ መሰናክል ሲፈጥርባቸው ከጉዟቸውና ከመንገዳቸው ሲያሰናክላቸው ከነበረው መንፈስ የተፈወሱበትን መንገድ ከላይ በቀረበው መሰረት ገልጸዋል። ከገለጻቸው መረዳት እንደሚቻለውም የጠልሰም መድኃኒት ፈውስ የሚጀምረው ከሚታሰርበት ሰዓት ጀምሮ አንዳች ሥነ ልቡናዊ ለውጥን እንደሚያስከትል ነው።

### **4.5.3** ለደመ ከቴር

በጻታ ወረዳ ካሉ ጠልሰማዊ መድሃኒቶች መካከል ለደመ ከቴር የሚጠለሰም ጠልሰማዊ መድኃኒት አንዱ ነው። ይህ መድኃኒት ያለ ጊዜው የወር አበባ ለሚፈሳቸውና ከወለዱ በኋላ በከፍተኛ ሁኔታ ደም ለሚፈሳቸው እናቶችና እህቶች የሚጠለሰም ጠልሰም ነው። በጻታ ማህበረሰብ ዘንድ ለዚህ ሕመም

መድኃኒት እንደሆኑ የሚታመንባቸው ጸሎቶች ሁለት ናቸው። ስለሆነም በብራናው ላይ ከዚህ በታች ከሰፈሩት ጸሎቶች መካከል አንዱ ሊጻፍ ይችላል።

1. መሊስ፣ መሊስ፣ መላሊስ፣ አፍሊስ ጸሎተ ደም በእሉ አስማት ይቁም ደም እምውሕዘት በከመ ቆመ ዝናም በቃለ ኤልያስ ነቢይ ወኢዘንመ እስከ ሠለስቱ ዓመት፣ ጋዴን፣ ጋዴን፣ ጋዴን ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅሬሁ ከማሁ ይግባእ ደም ድኅሬሁ ወይጽናዕ ውስተ ማሕጸና ለዓመትከ እገሊት (መሪጌታ አፈወርቅ ነጋሽ፣ ነሐሴ 25/2012፣ 5፡45)።
2. ጸሎት በእንተ ደም ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ህያው ወወልደ ማርያም ሥግው ዘፈወስኮ ለመጻጉዕ ዘሰላስ ወሰመንተ ክረምተ ሐመ በቃልከ ወኣሕውከ ብዙኃነ ድውያነ ሐንካሳነ ወጽቡሐነ በጽንፈ ሐይቀ ባሕረ ገሊላ ወፈድፋደሰ ከመፈወስከ እም ውሕዘተ ደማ ለብእሲት እንተ ደም ይውሕዛ አመ ገሠሠት ጽንፈ ልብስከ ከማሁ አድኅና እምሕማመ ደም ለአመትከ እገሊት።

## የጸሎታቱ ትርጉም

1. የደም ጸሎት መሊስ፣ መሊስ፣ መላሊስ፣ አፍሊስ በእነዚህ አስማት ደም ከመፍሰስ ይቁም። በነቢዩ በኤልያስ ቃል ለሶስት ዓመታት ዝናብ ላይዘንብ እንደቆመ ደም ይቁም። ጋዴን፣ ጋዴን፣ ጋዴን የዮርዳኖስም ውሐ ወደኋላው ተመለሰ እንደዚሁ ሁሉ ደም ወደኋላ ተመልሶ በእገሊት ማህጸን ውስጥ በጽንስ ወይም በእርግና ይጽና።
2. ስለ ደም ሕመም የሚጸለይ ጸሎት የህያው የእግዚአብሔር አብ ልጅ፤ ሥጋ የለበስክ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሰላሳ ስምንት ዓመት የታመመውን መጻጉዕን በቃልህ የፈወስክ፤ ብዙ ድውያንን አንካሶችን፣ ልምሾዎችን በገሊላ ባሕር አካባቢ የፈወስክ፤ ይልቁንም የልብስሕን ጫፍ በዳሰሰች ጊዜ ደም ይፈሳት የነበረችውን ሴት ከደሟ መፍሰስ እንደፈወስካት አገልጋይህን እገሊትን ከደም መፍሰስ ሕመም አድናት። (ማቴ 15÷29፣ ማር 5÷25፣ ዮሐ 5÷5) (አዕመረ ጸሐዩ፣ ነሐሴ 28፣ 6፡33)።

ከላይ የተገለጹት ሁለት ጸሎቶች በሁለት ጠልሳሚያን ምንጭነት የተገኙ ናቸው። በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ጸሎት ይዘት አስማታዊ ነው። በጽሁፉ መጀመርያ ላይ በነቢዩ ኤልያስ መንፈሳዊ ጸሎት ሰማ ለዘር ጠል ለመከር ዝናብ የተከለከለበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ይጠቅሳል። “ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖሰ ለመጠመቅ በሔደበት ጊዜ የዮርዳኖስ ወንዝ ወደኋላ ተመለሰች” የሚለው የዳዊት መዝሙር 113÷5 ላይ የሚገኝ ቃልም ታክሎብታል።

መሊስ መሊስ መላሊስ የሚሉት አስማት መሰል ግዕዝ ቃላት ፍካሬ መመለስን፣ ማቆምን የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም በግዕዝ ቋንቋ "መሊስ መሊሶት" ማለት መነለስ፣ መገደብ ወይም ማቆም ማለት ነው (ኪዳነወልድ፣ 1948፣ 597)። ከዚህ አንጻር ቡብራነው ላይ የሚጠለሰመው ይህ አስማት መድኃኒትነቱ የሚፈሰውን ደም ይመልሳል ተብሎ ይታመናል።

ይህ የደመ ከቲር ጸሎት በህክምና ከሚሰጡ ዓለማዊ መድኃኒቶች እንደሚለይ ይታመናል። በዓለማዊ መድኃኒት ባለሙያው ታማሚውን የሚመራው ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ነው። በዚህ ህክምና የመድኃኒቱ ተመራማሪና አምራች አለ፤ በቲዎሪ በተማረው ትምህርት መሰረት እየተመራ "ለዚህ ሕመም መድኃኒቱ ይህ ነው" ብሎ ለታማሚው መድኃኒት የሚያዝ ባለሙያ አለው። በጠልሰም ለታማሚዎች የሚሰጠው የደመ ከቲርም ሆነ የሌላው ህመም መድኃኒት ግን በእምነትና በባህል የሚደረግ ነው። ለመድኃኒትነት በሚሰጠው አስማታዊ ወይም ጸሎታዊ ክታብ ምክንያት የሚያድን ሌላ መለኮታዊ ኃይል ወይም ፈጣሪ ያድናል ተብሎ ይታመናል። ይህ እምነት በጠልሳሚዎቹም ሆነ በሚያስጠለስሙት አካላት መካከል በመኖሩ ሰዎች ከህመማቸው ይድናሉ።

ሰዎች በዚህ ነገር ከሕመሜ እፈወሳለሁ የሚል እምነት በውስጣቸው ማሳደራቸው ከሚሰጠው መድኃኒት በበለጠ ፈዋሽ መሆኑን የሳይንስ ሰዎችም ያምናሉ። በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጅ መድኃኒትም ከሥነ ልቡና ጋራ የተያያዘ በመሆኑ ነገሩ ተመሳስሎ ሰዎች ከህመማቸው የሚድኑት በዚህ ነገር እድናለሁ የሚል እምነት በውስጣቸው በመኖሩ ነው። በአንጻሩ የሥነ-ልቡና ጉዳይ ለፈውስ ብቻ ሳይሆን ለችግር ለመጋለጥም የሚያስችል ኃይል አለው። ፈዋሹ መድኃኒት "መርዝ ነው" ተብሎ በባለሙያዎች ቢነገር ሰዎች በውስጣቸው አስቀድመው መርዝ እንደሆነ ካመኑበት በተፈጥሮ መርዝ ያልሆነው ነገር የመርዝነት ያህል ጉዳት ሊስከትልባቸው ይችላል። ስለዚህ መፈወስም ሆነ አለመፈወስ ለህመምተኞች ከሚሰተው ቁሳዊ ነገር ባሻገር ውስጣዊ እምነት ወሳኝነት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። በዚህ በደመ ከቲር ህመም ተይዛ ከወር አበባ ዑደት ውጭ የሆነ እና ከመጠን ያለፈ ደም መፍሰስ ያጋጠማት እናት ህመሙ እንዴት እንደሆነ እና እንዴት በጠልሰም መድኃኒት እንደዳነች በቃለ መጠይቅ የሰጠችው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

> እኔ ስሜ ብልጫለሽ ተስፋዬ ይባላል። ሲያመኝ የነበረው ህመሜ በወር ከሚመጣው ደሜ ውጭ ባላሰብሁት ወቅት ዝም ብሎ ደም ይዞኝ ይሄዳል፤ ልጅ በምወልድበት ጊዜም ደም ይፈሰኛል በብዛት፤ ወገቤን ይቆረጣጥመኛል፤ የሰውነቴን ጠረንም በመጥፎ ይቀይርብኛል። ባለመድሃኒቱ እጽዋትን ቀጥቅጠው ምን እንደሆነ እኔ አላውቀውም በብልቴ ያዝኩት፤ በቁመቴ እና በወገቤ ልክ የሚሆን ጠልሰም እንድይዝ አረጉኝ። መድሃኒቱን ካረጉልኝ በኋላ ግን ደም በየወሩ ያለጊዜው አይመጣም፤ በጊዜው ሲመጣም አይበዛም፤ ወገቤንም አያመኝም አሁን ተመስገን ብያለሁ (ነሐሴ

7/2012፣ 6፡44)።

ከላይ ታካሚዋ በገለጸችው መሰረት የደመ ከቲር ማከሚያ የሆነው ጠልሰም ከላይ በጸሎቱ የሰፈሩት ኅቡእ ስሞች ታትመውበት በታማሚዋ ቁመት ልክ የሚሆን ብራና ላይ ተጠለስሞ ከተጠቀለለ በኋላ ልክ እንደ ሾተላይ ጠልሰም ሁሉ በወገቧ ይታሰርላታል። በቁመት ልክመሆኑም አንዳንድ ጊዜ ተደራራቢ ወይም የተለያየ ሕመም መናፍስት በአንድ ላይ ሲጣቡ እንዚህን በአንድ ለመጠቅለል ጸሎቱ ሰፋ ብሎና ብራናው ረዘም ብሎ በቁመት ልክ ሊሰራ ይችላል።

### **4.5.4.** ለመግረሬ ጸር ወይም መድፍነ ጸር

መግረሬ ጸር ማለት ጠላትን ለማንበርከክ፣ ለማሸነፍ እና ለማጥቃት በጠልሰማዊ አስማት ለማፍዘዝና ለማደንዘዝ የሚሆን ጥበብ ነው። ጠላት ሲባል እኩይ መንፈስን አሊያም ጠላት የሆኑ ሰዎች የሚልኩት መንፈስ ነው። ስለ መግረሬ ጸር ጠልሳሚ ቄስ ኪሮስ የሚከተለውን ብለዋል።


> የመግረሬ ጸር ጠልሰም በሁለት መንገድ ይዘጋጃል። አንደኛው በወረቀትም ሆነ በብራና ተጽፎ የጠላቶች ሥም ተጽፎበት የሚያዝ ወይም የሚታሰር ነው። ሁለተኛው ደግሞ ጠልሰሙ በወረቀት ተጽፎ የጠላቶች ሥም ገብቶበት ክንድ ከስንዝር ጉድጓድ ተቆፍሮ የጠልሰሙ ጽሑፍ ወደታች ተዘቅዝቆ ጉድጓድ ውስጥ ከገባ በኋላ አዲስ የመቃብር አፈር በወረቀቱ ላይ ተበትኖ፤ በላዩ ላይ ሶስት ቀንም ሆነ ሰባት ቀናት ዓይነ ምድር ተወጥቶበት፤ ጥቁር ሴት ዶሮ አንገቷን ቆርጦ ከጉድጓዱ አስገብቶ የተቆፈረውን አፈር በግራ እጅ መልሶ በግራ እግር ረግጦ “ጠላቶቼን እንደዚህ ድፈናቸው፣ ቅበራቸው” ብሎ ድንጋይ ጭኖ በመተው የሚከናወን ነው (ሐምሌ 27/2012፣ 8፡33)።

ለመግረሬ ወይም ለመድፍነ ጸር በሚዘጋጅ ጠልሰም ላይ የሚተለሰም ጸሎትና ትርጉም ከዚህ በታች የሚከተለው ነው።

ጸሎተ መግረሬ ጸር


ግፍዖሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ ጽብኦሙ እግዚኦ ለእለ ይጽብኡኒ ንሣእ ወልታ ወኩናተ ወተንሥአ ውስተ ረዲኦትየ ምላኅ ሴፈከ ወግዕቶሙ ለእለ ሮዱኒ በላ ለነፍስየ አነ ውእቱ ረዳኢኪ ለይትኀፈሩ ወይትኀሰሩ ኩሎሙእለ የኀሥሥዋ ለነፍስየ ለይግብኡ ድኅሬሆሙ ዌትኀፈሩ እለ መከሩ እኩ ላዕሌየ ለይኩኑ ከመ ጸበል ዘቅድመ ገጸ ነፋስ ወመልአከ እግዚአብሔር ለይሣቅዮሙ ለትኩን ፍኖቶሙ

*ዳኅጸ ወጽልመተ ወመልአከ እግዚአብሔር ለይሰድዶሙ እስመ በከንቱ ኀብኡ ሊተ መሥገርተ ያጥፍኡኒ ወበከንቱ አመንዘዝዋ ለነፍስየ ለትምጽኦሙ መስገርት እንተ ኢያእመሩ ወተአኀዞሙ መሥገርት እንተ ኀብኡ ወይደቁ ውስተ ይእቲ መሥገርት*



*ሥዕል* **4.5፦** *ለመግረሬ ጸር የሚሆን ጠልሰም ላይ የሚጠለሰም ሥዕል ማሳያ*

ይህ ከላይ የቀረበው ጠልሰም ለመግረሬ ጸር የሚጠለሰም ሲሆን። በጠልሰሙ ላይ የሚስተዋሉት ፊደላት አደራደርም ሆነ ትርጉም በውል እንደማይታወቅ ከትውልድ በተለምዶ ሲተላለፍ የመጣ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ጠቁመዋል። ሆኖም ግን ብዙ ዓይነት የመግረሬ ጸር ጠልሰም አሳሳል የሚገኙ ሲሆን በሥዕል 5 ላይ የሰፈረው አንዱ ሲሆን ለዚሁ ሕመም በተመሳሳይ መልኩ ከዚህ በታች የቀረበው ጠልሰምም በቆዳ አሊያ እንደሚከተለው በወረቀት ላይ ሊጠለሰም ይችላል።



*ሥዕል* **4.6፡-** *ለመድፍነ ጸር ወይም ለመግረሬ ጸር የሚሳል ጠልሰም*

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሥዕል 6 የሰፈረው ማሳያ ለመግረሬ ጸር ወይም ለመድፍነ ጸር ከሚሳሉ ጠልሰሞች መካከል አንዱ ነው። ከሥዕሉ ማስተዋል እንደሚቻለው ተገንዘው የተቀበሩ ሬሳዎች የሚመስሉ ሥዕላትን በመሳል ለመግረሬ ጸር የሆነው ጸሎት በግዕዝ ዙርያውን በክብ ይጻፋል። የተገነዙ ሬሳ መሰል ሥዕላቱ "ጠላት"ን የሚያመለክቱ ወይም የሚወክሉ ናቸው። ጠላት ማለት አንድም ወደኛ ክፉ መናፍስት ይልኩብናል ብለን የምናስባቸው ሰዎች አንድም ደግሞ እኩይ መናፍስት ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም ይህን ወካይና ተምሳሌታዊ ሥዕል በማስፈር ጸሎቱ ዙርያውን ይሰፍራል። ጸሎቱ ዙርያውን መስፈሩ ደግሞ "ጠላቶቼን እንደዚህ እጠርልኝ፤ እንደዚህ እሰርልኝ፤ እንደዚህም ከልልልኝ" የሚል አንድምታዊ ፍቺ አለው።

### **4.5.5.** ለዛር መለመኛ፣ ማውገዣ እና ማስታረቂያ

በአርባ አራቱ በሰማንያ ስምንቱ በሰሪው ባሰሪው በጃም አውሊያ በአንበሶ በአልባሶ በአማሙዝ ይሁንባችሁ። እግዚኦ የናንተ ያለህ እለምናችኋለሁ። በውድም አላጣችሁ፤ በግድም አላመጣችሁ፤ እናንተን ባላቀው እኛን ባደቀቀው በሞራ በጮማ እንቃችኋለሁ። በደም አጠልቃችኋለሁ። እግዚኦ የናንተ ያለህ። እግዚኦ የናንተ ያለህ። ደንቆሮስ ምን ሰምቶ፤ እውር ምን አይቶ ዛር ለምልክት ነጋይ ለክት ሳይሳም በተስኪያን ሳይለን ዛር የለም ምልክት አሳዩን በጋላው በአማራው በሻንቅላው በእስላሙ በዐረቡ በክርስቲያኑ በሴት ወይዛዝሩ በወንድ መኮንኑ እግዚኦ የናንተ ያላችሁ። ከሎሚ ጥላ ከወይን ዘለላ ያውላችሁ። ግራ ቀኝ በረኞች መጀን ሽሕ አንበሶ የአውሊያው ምሰሶ ወርቄ አባ ሙራስ የአውሊያው ባልደራስ በቆጤ በጣሹ ወሚን አባላፋ ግራኝ በረኛው በፊት ወዳሚ በኋላ ወራሪ ሰባሪ አሰባሪ መገን ሰይፉ ጨንገር የእሳቱ ማገር ተገረገራው ከበጀራው ታረቂ አስታርቁልኝ

ተለመኑ አላምኑን መጀን አጤ ኢያሱ እሜቴ ዲራ ቁርቢት እራሔሎ ሎ ወርቅ አዳኝ ባሕር አዳይ ግምጃ ሉሊት ዘውዲቱ በረሰናችሁ መጀን ሁለተኛ አባቶች ከጫማችሁ ነኝ፤ እባካችሁ አለሞቹ ለምለሞቹ ወለሎቹ እማትታዩ እማትለዩ በናትም ባባትም በወትም የመጣችሁ ነጭ በላ፣ ቀይ በላ፣ ጥቁር በላ፣ አንበስማ በላ፣ ጅብማ በላ፣ ሰባት መልክ በላ ለምልክት እምብዛም አንታክት በዚህ አስይዛችኋለሁ ዋድ አይፈርስም ሰማይ አይታረስም የሰው ሥጋ ቢበሉት እርም ነው። ቢጠብሱት ይሸታል በቆቆር ዕጣን በጭብጥ ቡና ያልማረ ወልይ ወልይ ሊባል አይችልም በአገሌ ላይ ያላችሁ (ጠልሰሚ አዕመረ ጸሐዩ፣ ነሐሴ 28/2012፣ 9:12)።

ከላይ የተጻፈው የዛር ህምም መውገዣ ሲሆን ይኸውም በአማርኛ ቋንቋ የተቀናበረ ነው። የጽሑፉ ይዘት የተለያዩ የቤት ጣጣ በመባል የሚታወቁ  የዛር ስሞችን እያነሳ በሥነ ቃላዊ ወይም ግጥማዊ ንግግር ዛሮችን የሚያወድስ ሲሆን ይህ ሥነቃላዊ ማውገዣ በጽሑፍ ከጠልሳሚዎች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሲሆን ዛሮች ከፈጣሪ በታች እንደሆኑ የሚያሳዩ አገላለጾችን የያዘ ነው። በጽሑፉ ዛሮችን "ሁለተኛ አባቶች ይላቸዋል። ይህ ማለት መጀመሪያ አባት ወይም ፈጣሪ መኖሩን የሚያመለክት ነው።

በዛር ማውገዣው ውስጥ "ሳይሳም ቤተስኪያን ሳይለመን ዛር የለም ምልክት" የሚል ማውገዣም እንመለከታለን። ይህም ሰዎች በሀይማኖታው ሥርዓት ብቻ ጸንተው የሚኖሩ ሳይሆኑ ከቤተሰብ እና ከአካባቢ ጋራ የተያያዘ ባህላዊ ዕምነትና ሥርዓት ጭምር ያላቸው መሆኑን ያስረዳል። በዚህ መሰረት በሀይማኖታዊ ሥርዓት ቤተስኪያን ሳሚዎች የሆኑ ሰዎች በባህላዊ እምነት ዛር አክባሪዎች እንደሆኑ ጭምር ያመለክታል። ይህ ሁኔታ በሀይማኖት አክራሪ ሰዎች ዘንድ "የባዕድ አምልኮ" በሚል ሊፈረጅ ይችላል። በሌላ አንጻር ሲታይ ደግሞ ሰዎች ሀይማኖታዊ ከመሆናቸው አስቀድሞ በአካባቢያዊ ወይም በሀገር በቀል እምነት ይኖሩ እንደነበር ሲታይ ደግሞ ከተለያዩ ሀይማኖት መፈጠር በፊት እያንዳንዱ ማህበረሰብ የሚያምነውና የሚከተለው የቤት ጣጣ ያለው እንደነበር መገመት ይቻላል።

ለዛር መለመኛ፣ ማውገዣ እንዲሁም ማስታረቂያ የሚሆን ጠልሰም ተጠልስሞ የሚደረግለት ሰው መድሃኒቱ ሲደረግለት ዕጣን እና የተለያዩ መልካም መዓዛ ያላቸው ሽቱዎች ይቀርባሉ፤ ጉዝጓዝ ይጎዘጎዛል። ቀጥሎም ጠልሳሚው ሰውም ሆነ ሕመምተኛው ንጹሕ ልብስ ለብሰው ጠልሰሙ ላይ የሰፈረውን አስማት ጠልሳሚው ይደግምና ሕመምተኛው ዕጣኑን እንዲታጠን ይደረጋል።

ከዛር ጋር የተያያዘ ሕመም ገጥሟት የነበረች ሴት ስለ ህመሙ እና ስለተደረገላ ሃገረሰባዊ ህክምና የተናገረችው እንደሚከተለው ቀርቧል።

እኔ ስሜ አዳኑ ቸኮለ ይባላል። ከቤተሰቤ የተወረሰ ዛር አለብኝ። ህመሙ ሆዴን ይቆርጠኛል፣ ራሴን

ይፈልጠኛል፣ ወገቤን ይቆረጥመኛል፣ ያሰፋሽገኛል፣ ወይ ዛር ሆኖ አይወርድ አያጎራ፣ ያስለቅሰኛል፣ እንደ አይምሮ ጭንቀት አይነት ያረገኛል። ከዚያ ምንድነው ሲባል ዛሩ መርጋት አለበት እንድረጋ ደግሞ ዛሩ መለመን አለበት ተብሎ ቡና ተፈልቶ፣ቆሎ ተቆልቶ፣ብዙ ነገር ተደርጎ ዳቦ፣ቂጣ ተጋግሮ፣ ጠላ ተጠምቆ፣ ደጋሚው ይመጣል፣ ጠልሰም ይጠለስማል፣ ከዚያ በኋላ የእጣኑ ጢስ ሲሸተኝ፣ ሲፈልጠኝ ሲቆረጥመኝ የነበረው ነገር ይተወኛል። ከ 7-14 ቀን እታጠናለሁ። ከዚያ በኋላ በየወቅቱ እየመጣ አይደቁሰኝም፣ ሊሊቱንም አይረብሸኝም። አንዳንዴማ የሚፈልገውን ልብስ ካለበስኩ ወይም ሌላ ነገር የሚፈልገው ካላደረኩ ዛፍ ወይም ገደል ላይ ይሰቅለኛል ወይም ፍም እሳት ያስጨብጠኛል ግን ዛሩ ራሱ ይጠብቀኛል አያቃጥለኝም። ለጉዳትም አያበቃኝም። ምን ይቅረብልህ ይሕን በል ይባላል። እኔ ላይ ያደረው ዛር እኔን ፈረሴ ነው የሚለኝ፣ ከዚያ ፈረሴ ጫማ የላትም ተራቁታለች፣ ልብስ የላትም ይላል። አብርውኝ ያሉት ደሞ ይቅር በለን ጌታየ እንድህ ሆነን እኮ ነው ያልከውን እናደርጋለን ይባላል። ይረጋጋል። እኔም እመለሳለሁ ወደ ጤናየ ከዚያ ደህና እሆናለሁ።

ከላይ ሰፈረው የመረጃ ሰጪ ሀሳብ የዛር መንፈስ የተጣባትን ሴት በመለማመን እንዴት ሕመሙን ማርገብ እንደሚቻል አመላካች ነው። ለዚህም ነው ዛር መለመኛ የተባለው። አልፎ አልፎ መንፈሱ ተለማምነውት የማይተውና የማይለቅ ከሆነ ወደውግዘት ይኬዳል። ከላይ መረጃ ሰጪዋ በገለጸችው አኳኋን የቀረበው ሥርዓት ክዋኔ ተደርጎ “ይህን እንዳታደርግባት ይህን እንዳትፈጽምባት ተብሎ” መንፈሱ ይወገዛል።

### **4.5.6.** ለማዕሰረ አጋንንት


ጸሎት በእንተ ማእሰረ አጋንንት ወመናፍስት ርኩሳን በዘረበቦሙ ሰሎሞን ወመርበብተ ጥበብ ሎፍሐም፣ ሎፍሐም፣ ሎፍሐም፣ ኢዩኤል፣ ኢዩኤል፣ ኢዩኤል፣ ኢዮርሳዊ፣ ኢዮርሳዊ፣ ኢዮርሳዊ፣ አብታሪ፣ አብታሪ፣ አብታሪ፣ ማርማሬ፣ ማርማሬ፣ ማርማሬ፣ አማርማጸዳ፣ አማርማጸዳ፣ አማርማጸዳ እንዘ እብል አአትብ ገጽየ ተማህጸንኩ በሎፍሐም ስምከ አነ አመትከ እገሌ ቀሐሹን አቅማሐሹን፤ ቀሐሹን አቅማሐሹን፣ ቀሐሹን አቅማሐሹንዘነበረት ውስተ ጎልቀቱ ለሰሎሞን ወዘከመዝ ጽህፈቱ ሐፒሮስ ቊስቋራ ወይቤ ሰሎሞን ገበርክዎሙ ብሂልየ አልፋዊ፣ ታቦራዊ፣ ሚሎሳዊ፣ ኬንያዊ ወቦእኩ እንተ ቀላይ ምስለ ጸዋጋን አጋንንት እንዘ ሥጋ እለብስ ሞእክዎሙ እኤዝዞሙ ወእቀንዮሙ በከመ ተመነይኩ። ወከማሁ አሰልጥነኒ ላእለ አጋንንት ጸዋጋን ወመናፍስት ርኩሳን ሊተ ለአመትከ እገሊት ለገብርከ እገሌ (አዕመረ ጸሐዩ፣ ነሐሴ 27/2012፣ 8፡55)።

ከላይ የተገለጸው አስማት አጋንንት በሰዎች ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንዳያደርሱ የሚታሰሩበት መለኮታዊ ኃይል አለው ተብሎ የሚታመን የጠልሰማዊ መድኃኒት ነው። የአስማቱ መረታዊ ምንጭ ጠቢቡ ሰሎሞን እንደሆነ የአስማቱ ይዘት ያስረዳል።

ጠቢቡ ሰሎሞን የንጉሥ ዳዊት ልጅ የሆነና በአስራ ሁለት አመቱ የነገሠ፤ ረሃብና ችግር ምን እንደሆነ የማያውቅ ንጉስ እንደነበረ ይነገርለታል። ከዕለታት በአንዱ ቀንም  አንድ የራበው ሰው ከደጁ ቆሞ የእግዚአብሔርን ሥም ጠራበት። ሰሎሞንም ከአተገቡ ነበሩተረነረ ሰዎች “ምን ሆኖ ነው?” አላቸው። እነርሱም “እርቦት እየለመነ ነው” አሉት። እርሱም “ረሃብ ምንድን ነው?” አላቸው። በዚህ ጊዜ ፈጣሪ ተቆትቶ ሰሎሞን ረሃብን የሚያይበትን መንገድ ለመፍጠር “ሐሩራኤል ጭርዋቅ” የሚል ስመ እግዚአብሔር የተጻፈባትን ግርማ ሞገስ ሆና ሰሎሞንን አስፈሪ ምታደርገውን ቀለበት በሰይጣን እጅ እንድትገባ አደረገ። ሰሎሞንም አንበሳ መደብ ሲወጣ (ግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሞ) ይህችን ቀለበት ከዙፋኑ ላይ ያስቀምጣል። በዚህ ጊዜ ሰይጣን ቀለበቱን አንስቶ በእጁ አጠለቀና ሰሎሞንን መስሎ፤ እንደርሱ ተጎናጽፎና መልኩን ቀይሮ በሰሎሞን ዙፋን ላይ ተቀመጠ። ሰሎሞንም ከአንበሳ መደብ ተመልሶ ሲመጣ ግርማ ሞገሱ ስለተገፈፈ የንጉሱ አገልጋዮች “የማን ነው ደግሞ ባዘኔ ከንጉሱ ዙፋን ለመቀመጥ የሚሞክር?” ብለው አባረሩት።

ሰሎሞንም ከቤተ መንግስት ወጥቶ በከተማው እየተዘዋወረ ቁራሽ ቢለምን እግዚአብሔር የከተማዋን ሰዎች ልብ አጽንቶ ሰሎሞንን አንድም የሚዘከረው ሰው አጣ። ከአንድ ሳምንት በኋላም ረሃቡ እጅግ ቢተናበት ወደ ባሕር ዳር ሂዶ ዓሣ አስጋሪዎችን ቢለምናቸው አንዲት የጠወለገች ዓሣ ወረወሩለት። ሰሎሞንም የዓሣውን ሆድ ሲቀድ በሆዱ ውስጥ የጣት ቀለበቱን አገኘ። የንጉስነት ግርማና ሞገሱም ተመለሰ። በዚህ ጊዜ በአካባቢው የነበሩት ዓሣ አስጋሪዎችና ሌሎችም ሰዎች “ንጉሥን ከዚህ ሥፍራ ማን አመጣቸው” ብለው ከበቡት። ሰሎሞንም ዳግም ወደ ቤተመንግስቱ ተመልሶ ከላይ በሰፈረውን አስማት ወይም መርቡብተ ሰሎሞን በመድገም በእርሱ ዙፋን ላይ የነበረውን ሰይጣን አሰረው። መሬት ቆፍሮ ሰይጣንን ከእነሕይወቱ ቀብሮታል (አክሊሉ ሰሎሞን፣ የቅዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጓሜ)።

ይህን መሰረት በማድረግ የጻታ አካባቢ ጠልሳሚዎች መርቡብተ ሰሎሞንን በጠልም መልክ በማዘጋጀት ሰዎች ከአጋንንት እስራት የሚድኑበትን መድኃኒት ይጠለስማሉ። መርቡብተ ሰሎሞን የሚለውን የአጋንንት ማሰሪያ አስማት በጠልሰም ከመጠልሰም ባሻገር በብርና በወርቅ ቀለበት ላይ ይህን አስማት “ሐሩራኤል ጭርዋቅ” ብሎ ድጋሙን በቀለበት ላይ ይቀርጻሉ። በዚህም ሰዎች ከአጋንንት እራት ይጠበቃሉ ተብሎ ይታመናል።



ሥዕል **4.7፦** በወረቀት የተሳለ የማዕሰረ አጋንንት ጠልሰም

ከላይ የተጠለሰመው ጠልሰም የሰሎሞን ምና ሌሎች ሶስት ኅቡእ አስማት የተጻፈበት ነው። የጻታ ጠልሳሚያን እንደሚሉት ከላይ በሰፈረው ሰንጠረዥ መሰል ጠልሰም መልክ የሚዘጋጅ መድኃኒት አጋንንት እንዲሰጡ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳሉ። የሰሎሞን ስም በራሱ በስተሳልም፣ መስተዋድድ የሚል ፍካሬ አለውና ኃይልን የሚያጎናጽፍ መሆኑንም ይናገራሉ። ይህን አጋንንትን የማስጠም መለኮታዊ ኃይል የሚከውኑትም አስማቱ ናቸው ተብሎ ያታመናል። ከላይ በጠልሰሙ ሥዕል ላይ ማስተዋል እንደሚቻለው ስሞቹ ወደጎንም ሆነ በተዋረድ ሲነበቡ ተመሳሳይ ንበት አላቸው ይህ የሚሆነውም በእነዚህ በአራቱም መዓዘን ተመሳሳይ በሆኑት ሃያል ስሞች አጥርነት መንፈሱን ማጠር ይቻላል የሚል ዕምነት አለ።


ይህ ለመስጥመ አጋንንት የሚሆን ጠልሰም ቆዳው በአዋቂዎች አውደ ነገስት ገልጠውና ኮከብ ቆጥረውን ከሕመምተኛው ዕጣ ክፍል ጋር በተዛመደ መልኩ ቆዳውን መርጠውና ቀለሙንም ጠቁመው ካበቁ የማሽላ ቆሎ እና ቡና ተዘጋጅቶ፤ ኑግ ተወቅጦ፤ ኩብ  ኩብ ተደርጎ በትንሽ በትንሹ ቂጣ ይጋገራል። ይህ የሚሆነውም መናፍስቱ ይቋደሳሉና ለሁሉም እንዲዳረስ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ይህ ከሆነ በኋላም ቅቤ ይቀርባል፣ ከከርቤና ከአደስ የሚገኝ መልካም መዓዛ ያለው ቁኒ ተብሎ የሚጠራም ሽቱ ይቀርብና ከቅቤው ጋር ይለወሳል። ከቤተሰቡ ትልቅ ተብሎ ሚታሰብ ሰው ተመርጦ በቁኒ የተለወሰውን ቅቤ በሕመምተኛው አናት ላይ ያስቀምጣል። "እንዲህ አድርግለት፤ መልካም አድርግለት" እያሉ በወጉብ የሚዞረውን አሊያም በግንባር የሚዘጋጀውን ጠልሰም ያስሩለታል። በጠልሰሙን የጠለሰመው ሰውም ጠልሰሙ ላይ የሰፈሩትን አስማት "ሎፍሐም፣ ነሐፍሎም፣ ንምሎስ" እያለ እየጠራ ሕመምተኛውን በውሃ ያጠምቃል። አንድ አጋንንት ያደረበት ታማሚ ስለ ህመሙ እና ስለተደረገለት ህክምና እንደሚከተለው ገልጿል።

እኔ ስሜ ገብሩ አስራት ይባላል። ህመሙ ጋኔኑ ካደረብኝ በኋላ የሚያረገኝ ራሴን ያስተኛል፣ ሌሊት ያቃዠኛል፣ ብቻዬን ያስወራኛል፣ ሁለመናየ የኔ አይመስለኝም ህቅሌን አላውቅም የምጠይቀው እና የማወራው አይገናኝም። አልፎ አልፎ ልብሴንም ያሥጥለኛል። እኔ ይህ ሁሉ ሲሆን በብዛት አላስታውስም። ወደ ቀልቤ ስመለስ የቀየው ሰው ነው የሚነግረኝ እንጂ። በኋላ ወደ ደብተራ ወሰዱኝ እና አጋንንቱን የሚያስር ድጋም እየተደገመ ከቤቴ ለ 7 ቀን ያጠምቁኛል። ይሄን ካደረጉ በኋላ ሲደገምልኝ የነበረውን ጠልሰም በዓለም ስሜ እና ክርስትና ስሜ አስገብቶ ሰጡኝ። ያን ይዤው እንቀሳቀሳለሁ፣ ስተኛም ይዤው እተኛለሁ። ከዚያ በኋላማ ምስጋና ለሱ ዳንኩኝ (ነሐሴ 9/2012፣ 3፡ 50)።

ማእሰረ አጋንንት አቅል አስቶና ጨርቅ አስጥሎ ለሚያሰቃይ እኩይ መንፈስ የሚሰት መድኃኒት መሆኑንና የመሽታውን ምልክቶች ከላይ ከሰፈረው ከመረጃ ሰጪው ንግግር መረዳት ይቻላል።

#### 4.5.7 ለመፍትሔ ስራይ

ጸሎት በእንተ ህማመ ባርያ ወሌጌዎን ጸር ወጸላእት ወሥራይ ቢስሚላሂ እራኅማኒ እራሂም አልሆይ ይቢቱ ወልቁሚቱ ቢስሚላሂ እራኅማኒ ራሂም አዚዙ ወልኢዙ አውዑድ ቢላሂ ሚን እረሾ ያጡኒ አላጢፋ አላጢፋ አላጢፋ አላሁ ላኢላሂ ኢላሁ አለመሊኩ አልሐቁ አልሙ ቢሉ ወለሃውላ ወለቅወታ ኢላቢላሂ አልአልዩል አዚሚ አድኅነኒ እም ሕማመ ዛር ወበሽታ ወጋኔን ወባርያ ወሌጌዎን ወእም ኩሎሙ መናፍስት ርኩሳን ወሰብእ መሰርያን እቀበኒ ለአመትከ እገሌ/እገሊት (መሪጌታ ደሳለኝ ኪሮስ፣ ነሀሴ 27/2012፣ 5፡15)።



ሥዕል **4.8፡-** በወረቀት የተሳለ የመፍትሔ ሥራይ ጠልሰም

ከላይ የተጻፈው ዐረባዊ አስማትና የተለያዩ ቅርጾችን አካቶ የያዘው ጠልሰም በሚዳቋ ብራና በቀይ ቀለም ተጽፎ ለመፍትሔ ሥራይ፣ ለዛር በሽታ፣ ለቡዳ መንፈስ መድኃኒትነት ጭምር የሚውል ነው። ልራይና ለተለያየ የዛርና የቡዳ መንፈስ መድኃኒትነት የሚሆን አስማት ይዘት ሲጤን ዐረብኛና ግዕዝ የተቀላቀለበት ነው። የዐረብኛው ቃላትም ሆኑ የግዕዙ ቃላት ኃል የሚገለጥባቸው የፈጣሪ ኅቡዕ ስሞች ናቸው ተብሎ ይታመናል። በተለምዶ የዐረብኛ አስማትን ከእስልምና ሃይማኖት፤ የግዕዝ ቃላትን ደግሞ ከኦርቶዶክስ ዕምነት ጋር የማያያዝ ሁኔታ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ዘንድ ይንጸባረቃል። ነገር ግን ቃላቱ ቋንቋዊ ፍካሬ እንጂ ሃይማኖታዊ አንድምታ ያላቸው ናቸው ለማለት አያስደፍርም፤ ምክንያቱም በየትኛውም ቋንቋ ማንኛውም ሃይማኖት ሊነገር ይችላል። ስለሆነም በጠልሰም እና በአስማት ዓለም "ይህ ዐረብኛ ቃል ነው ይህ ደግሞ የግዕዝ ቃል ነው" የሚል ድንበር ሳይኖር በጠልሰማዊ ጥበብ የተቀራኘ ተግባር እንደሚሰራ ያመላክታል። ያ ማለት ቢስሚላሂ ማለትም ሆነ በስመአብ ማለት አንድ ዓይነት ፍካሬ አለው እንደማለት ነው። በቋንቋነት የተለያዩ በትርጉምና በመድኃኒትነት አንድ የሆኑ አስማት ለመፍትሔ ሥራይና ለተለያዩ የዛር መንፈስ በሽታዎች መድኃኒትነት እንደሚጠለሰሙ ያስረዳል።

ከአስማቱ ቀጥሎ የተጠለሰመው ሰንጠረዣዊ ጠልሰም ውስጥ የተለያዩ የግዕዝ ፊደላት፤ የሶሎሞን አርማና ትርጉማቸው ይህ ነው ለማለት የሚያዳግቱ ሰያፍ ጭረቶች ይስተዋላሉ። እነዚህም ከሶሎሞን ጥበብ ጋራ የተያያዘ መድኃኒትነት  እንዳላቸው በአካባቢው ነዋሪዎችና በጠልሳሚያኑ ዘንድ ታመናል። በአሁኑ ሰዓት በእስራኤላውያን ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያለው ኮከብ መሰል ዓርማ በብዙ የኢትዮጵያውያን የጥበብ ውጤቶች ላይ ተቀርጾ ይስተዋላል። ለምሳሌ በቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፤ በተለይም በቤተ ማርያም

ውስጣዊ ክፍል ላይ ይገኛል። የጻታ ወረዳ ጠልሳሚዎች በጠልሰማቸው በሀረግ መልክ እንደሚቀርጹት ተስተውሏል። የዚያ መሰረታዊ አንድምታም ከሰሎሞን እና ከጥበቡ ጋር በተሰናሰለ መልኩ ትርጉም የሚሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

ለመፍትሔ ሥራይ፤ ለዛር በሽታና ለቡዳ መንፈስ መድኃኒትነት የሚዘጋጀው ይህ ጠልሰም በሚዳቋ ቆዳ የሚዘጋጅ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያትም በውዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጓሜ "ወኩሉ ፍጥረት ተፈስሐ በምጽአትከ" (በአንተ መምጣት ፍጥረት ሁሉ ደስ አለው) ከሚለው ገጸ ንባብ እንደተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ሲወለድ "ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም፤ ዮም ተወልደ መድኃኔዓለም" (የዓለም ሁሉ ቤዛ ዛሬ ተወለደ፤ የዓለም መድሃኒት ዛሬ ተወለደ) እያለች ሚዳቋይቱ ስትደሰትና ስትዘል አንድ ባሕታዊ ተመልክቷል።

ከሌሎቹ እንስሳት በተለየ ሚዳቋ የዓለሙ መድሃኒት ተወለደ በማለቷ ሥጋዋም ሆነ ቆዳዋ ለመፍትሔና ለመድኃኒት ይሆናል ተብሎ ይታመናል። አንድም ሚዳቋ ከአጥፊ አውሬ ለማምለጥ ከበጎችና ከፍየሎች ይልቅ የመሮጥ አቅም እንዳላት ሁሉ በሚዳቋ ብራና የተጻፈው መፍትሔ ከበሽታዎች ለመዳን ያስችላል ተብሎ ይታመናል። ሆኖም ግን ይህ ሁነት የገቢር ጣጣ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። ገቢር ማለት የባህላዊ መድኃኒቶች አሰራር ከአቀባዮች ወደ ተቀባዮች የሚተላለፉት በሁለት መንገድ መሆኑ ይታወቃል። አንደኛው በጽሑፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቃል ነው። በጽሑፍም ሆነ በቃል ከአበው ወደ ትውልድ ሲተላለፍ "ይህን እንደዚህ፣ በዚህ፣ ለዚህ፣ በዚህ መልኩ ወዘተ. አድርግ ከሚል ትዑፊታዊ አከዋወን ጋር የተያያዘ ነው። ስለሆነም እንዳስፈላጊነቱ ከሚዳቋ ውጭ በሆነ እንስሳ ቆዳና በተራረፉ ቆዳዎችም ጭምር የሚጠለስሙ ጠልሳሚያን እንዳሉ መረዳት ተችሏል። ይህ ከሆነ በኋላም ቡና ተፈልቶና ቁጤማ ተጎዝጉዞ መድሃኒቱን በታማሚው ወይም በታማሚዋ ላይ ሰባት ጊዜ በማዞር ይታሰራል።

ከዚህ በታች ሰዎች መድኃኒት አሰርተውበት የታመመው ሰው እና የተደረገለት የመፍትሄ ሥራይ ህክምና እና ውጤት እደሚከተለው ተገልጿል።

> እኔ ስሜ አበባው ተበው ይባላል። እኔ ታምሜ የነበረው ጓደኛ ውሎብኝ ነው። ከምበላው ምግብ ጋር መድሃኒት ለውሰው ሰጡኝ። በዚያ ምህኒያት ሆዴን በጠና ያመኝ ነበር፣ ሆዴን በብዛት ይነፋኛል። ወደ ባለመዳኒት ወሰዱኝ እኔ አላቀውም ምን እንደሆነ ግን ለ 7 ቀን በውሃ ላይ ተደግሞልኝ ተጠመኩ ጠልሰም እንድይዝም ተሰጠኝ ቀንም ሌትም ወደ ላይ ወደ ታች እያለ ሆዴን የነፋኝ ጓጉንቸር፣እና ሃሞት የመሰል ነገር ወጣልኝ። ከዚያ ተነፈስኩ (ነሐሴ 11/2012፣ 3፡ 22)።

## 4.6. የፃታ ወረዳ ጠልሰም ከሌሎች አካባቢዎች የሚለይበት መልክ

የፃታ አካባቢ የጠልሰም አሰራር ከሌሎች የሚለይበት መልክ አንደኛ ጠልሰም የሚሰራበት የእንስሳት ቀለም ከቤተሰባዊ፣ ባህላዊ ዕምነታዊና አመለካከት ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው። ሰሜን ጎንደር ውስጥ እንደ በለሳ፤ ደቡብ ጎንደር ውስጥም እንደ እስቴ ወረዳ አንዳ ቤት፤ ትግራይ ክልል በተንቤን አካባቢ እንዲሁም እንደ ላሊበላ ባሉ አካባቢዎች የጠልሰም ስራ የሚካሔድ ቢሆንም በፃታ አካባቢ እንዳለው አይነት የቆዳ መረጣ ሥርዓተ ክዋኔ በሌሎቹ አካባቢዎች እንደሌለ በሌሎች አካባቢዎች ይህን የጠልሰም ጥበብ አሰራር ያስተዋሉ የፃታ ጠልሳሚዎች ይገልጻሉ።

> እኔ በስራ አጋጣሚ ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ትግራይ እና ላሊበላ ወደሚባሉ አካባቢዎች ሄጃለሁ። ነገር ግን በነዚያ አካባቢዎች የሚተለስሙ ሰዎች ለቆዳ መረጣ የሚያካሂዱት ሥርዓት የለም። በተገኘው ቆዳ ራሳቸው ባገኙት ወይም መድሃኒት የሚያሰራው ሰው ይዞ በመጣው ይሰራሉ። አንዱ አምጥቶ በተረፈው ቆዳም ለሌላው ሊሰሩ ይችላሉ። ደግሞ በግንባር የሚታሰረው የተልሰም ዓይነትም በሌሎች አካባቢዎች የለም (አዕመረ ጸሐዩ፣ ሐምሌ 27፣ 4:50)።

ሰዎች ጠልሰሙን ሲያሰሩ በሥጋ ከሚወለድ ጠልሳሚ የሚያሰሩ ሰዎች መኖራቸው፤ የጠልሰሙ ቅርጽ እና ውስጣዊ ሀረግ ቀደም ሲል በዋግ ምድር ከነበሩ “የእጭበል ዘር” ከሚባሉ የብራና ጽሑፍትና ጠልሳሚዎች ሥራ ጋር የተያያዘ መሆኑ ከሌሎቹ አካባቢዎች የጠልሰም አሰራር የተለየ ነው። ከዚህ ባለፈም ከሥጋ ዘመድ ጠልሳሚ ውጪ ጠልሰም የሚያሰሩ ሰዎች “የእጭበል ዘር ነው?” ብለው በመጠየቅ የሚያስጠለስሙ ሰዎች መኖራቸውም ሌላ ልዩነት ነው።

የእጭበል ዘር የሚባሉት ዝርያዎች አሁንም በዋግ ምድር አልፈው አልፈው እንዳሉና ትንንሽ ክታቦችን የሚስከትቡ አንድ ሰዎች “የእጭበል ዘር እነማን ናቸው” ብለው በመጠየቅ አሁንም ድረስ የሚያስከትቡ

እንዳሉ ጠልሳሚ አፅመረ ጸሐዩ ጠቁመዋል (ነሐሴ 28/2012፣ 5:25)። በግንባር የሚታሰረው የጠልሰም አይነትም በሌሎች አካባቢዎች ያልተለመደና በፃታ ብቻ የሚገኝ መሆኑም ተገልጿል።

## **4.7** የማህበረሰቡ አመለካከት

የጠልሰም ዕውቀት ያደገና የዳበረ ሀገር በቀል ዕውቀት አይደለም። ጠልሳሚያኑ ለበርካታ አመታት በዚህ ተግባር ላይ የከረሙና ጥበቡንም ለተተኪዎች ለማስተላለፍ የታተሩ ቢሆንም የሚጠበቅበትን ያህል ያላደገ ጥበብ ነው። አሁን አሁን በተለያዩ የስዕል አውደርዕዮች ላይ ጠልሰማዊ ስዕሎች ብቅ ብቅ እያሉ፤ ጠልሰም ሰዓሊያንም የመገናኛ ብዙኃን ትኩረት እየሆኑ መጥተዋል። ሆኖም ጠልሰምን ከመድኃኒትነት አንጻር የመጠቀምና ዕውቀቱን የማሳደግ ሁኔታ አሁንም ድረስ የዳበረ አይደለም። ለዚህም በርካታ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል። ለዚህ ጥበብ አለማደግ በዋናነት ከሚነሱ ምክንያቶች ውስት ደግሞ ይህ ዕውቀት በሚከወንበት አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች አሉታዊ አመለካከት ዋነኛው ነው።

የጠልሰም መድኃኒቶች በሚሰሩባቸው እንደ ፃታ ባሉ አካባቢዎች ላይ ጠልሰምን እና ጠልሳሚያንን የሚመለከቱ አሉታዊ አመለካከቶች ይስተዋላሉ። ይህን ጥበብ የሚከውኑት ሰዎች የሚፈውሷቸው ሕመሞች አብዛኞቹ ከመናፍስት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው የአካባቢው ማህበረሰብ ጠልሳሚያንን ድግምት ደጋሚ መንፈስ አናጋሪ አድርጎ ይስላቸዋል። በዚህ ወደነዚህ ጠልሳሚያን ቀርበው መድኃኒቱን ከልብ ሽተውና አምነው የሚያስጠለስሙ ሰዎች በርካታ ቢሆኑም በዚሁ ልክ ደግሞ የሚሸሹና የሚፈሩም በርካቶች ናቸው። ለዚህ ሁኔታ ደግሞ የአንዳንድ ጠልሳሚያን ዕውቀቱን በአግባቡ ያለመጠቀም ሁኔታ መኖር በምክንያትነት ይጠቀሳል።

ይህ እውቀት ተጠብቆ በአግባቡ ተይዞና በተገቢው መንገድ ተተግብሮ ከቆየ የሀገር ሃብት መሆኑ እሙን ነው። ሆኖም ይህን ዕውቀት ለእኩይ ተግባር የሚጠቀሙ ጠልሳሚያንም እንዳሉ ከጠልሳሚያን መረዳት ተችሏል (አፅመረ ጸሐዩ፣ ነሐሴ 29/2012፤ መሪጌታ አፈወርቅ፣ ነሐሴ 28/2012)። አንዳንድ ጠልሳሚያን የአንድን ሰው ሃብት ከአንዱ ወደሌላው የማዞርና ይህን መሰል አሉታዊ ተግባርን የመፈጸም ሁኔታ ሰለሚኖራቸው ማህበረሰቡ ሁሉንም ጠልሳሚያን በአንድ ዓይን በመመልከት በአንድ ይፈርጃቸዋል። በምልከታዬ ካስተዋልኩት ረገድም በዚህ ምክንያት ጠልሰም የሚጠለስሙትን ሰዎች ማህበረሰቡ አልፎ አልፎ ሲሸሻቸውና ሲርቃቸው ይስተዋላል።

## **4.8.** የጠልሰም ዕውቀት ተስተላልፎ በፃታ ወረዳ

በፃታ የሚገኙ ጠልሳሚያን ጠልሰማዊ ጥበብን የወረሱበት አኳኋን ተቀራራቢነት ያለው ነው። ይህ ዕውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው አንድም በጽሑፍ አልፎ አልፎም በቃል ነው። ሰፋ ያለ ክዋኔያዊ ሂደትን ከሚጠይቀው የሾተላይ ሕመም አንስቶ ከቆዳ መረጣ ውጪ ጥልቅ ክዋኔያዊ ሥርዓትን እስከማይሹት ሕመሞች ድረስ ያሉ ጠልሰማዊ ጉዳዮች ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፉ የመጡበት ሁኔታ ጽሑፋዊውን እና ቃላዊውን በማጣመር ነው። አብዛኞቹ መምህራን እነሱን ያስተምሩ ከነበሩ መምህራን ዕውቀቱን ኢመደበኛ በሆነ መንገድ እንደወረሱትም ይናገራሉ።

> ይህን ሥራ ከጀመርኩ 15 ዓመት ሆኖኛል። መምህር አስተራይ የሚባሉ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ነበሩ። እኔ ደግሞ የአብነት ተማሪ ሆኜ ከሳቸው እግር ስር ቁጭ ብዬ እማር ነበር። ጠልሰም ሲሰሩ አይ ስለነበር “ይህ ምንድነው” እያልኩ ስጠይቃቸው ለእርሳቸው ታዛዥ ስለነበርኩ በከፊል በከፊል እየነገሩኝና እየተረዳሁ በተለይም የቁም ጽሑፍን በብርቱ እየሰራሁ መጣሁ። ከዚያ በኋላም በቤተሰቤ ክፉ መንፈስ ገብቶ እህቴን ስላመማት የመማር ፍላጎቴ ጨመረና መማር ቀጠልኩ (መምህር ኪሮስ፣ ነሐሴ 27/2012፣ 2፡40)።

ከላይ የሰፈረው መምህር ኪሮስ የጠልሰምን እውቀት የወረሱበት መንገድ ነው ልክ እንደርሳቸው ሁሉ መምህር አዕመረ ጸሐዩ እና መሪጌታ ደሳለኝ ገ/ሚካኤልም የጠልሰምን እውቀት የተማሩበትን መንገድ እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> እኔ የጠልሰምን ሙያ ተማርኩት በተለያየ ወቅትና ጊዜ ነው። የያሬዳዊ ትምህርት ለመማር ከቦታ ቦታ ስዞር ነው። ዞዝ አምባ የሚባል ትልቅ ደብር ያስተምሩ የነበሩ እስመለዓለም የሚባሉ አንጋፋ መምህር ነበሩ። ከእርሳቸው ጋር ከ 4 ዓመት በላይ በመቆየቴ የሚሰሩትን በማየት የተወሰነ ካወኩ በኋላ ሌሎች የቤተክርስቲያን ዕውቀቶችን ፍለጋ ወደ ሌላ ቦታ ሔድኩ። ተመልሼም እንደገና ወደ በለሳ ተመለስኩ። መምህሬም በዕድሜና በሁኔታ ከፍ ማለቴን ሲያስተውሉ ሌሎች ምሥጢራዊ ሆኑ የጠልሰም አስማቶችን አስተማሩኝ። በተለይ ድብቅ የሆኑ የተልሰም አስማቶጭ የሚዙት በቃል ስለሆኑእነዚያን ሁሉ በቃል አስተማሩኝ (አዕመረ ጸሐዩ፣ ነሀሴ 28/2012፣ 5፡23)።
>
> የጠልሰም ሙያን መስራት የጀመርኩት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ነው። ያስተማሩኝ መምህር ገ/ሥላሴ የተባሉ የቤተክርስቲያን አገልጋይነበሩ። የተማርኩት እኔ ጎጃም አዴት ወረዳ ቅኔ ለመማር ወደስፍራው በሔድኩበት አጋጣሚ ነው። ሁሉም ተማሪ እኩል

አይሆንምና እኔን ይቀርቡኝና ይወዱኝ ነበር። ለጠልሰም የሚሆን ብራና ሲፍቁና ሲያዘጋጁ ያዙኝና አግዛቸው ነበር። ከልጅነቴ ጀምሮም አስተማሩኝ። በተለይ ብቻዬን ስሆን እንጀራ ይሆነኝ ዘንድ አስማቱን እየቀዳሁ እንድጽፍ ያደርጉ ነበር። በዚህም አሁን ላለሁበት ደረጃ አበቁኝ እንጀራዬንም ሰጡኝ ማለት ነው (መሪጌታ ደሳለኝ፣ ሐምሌ 26/2012፣ 9፡55)።

ከላይ ከሰፈሩት የጠልሳሚያን ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው የጠልሰም ዕውቀት ተስተላልፎ መደበኛ ሳይሆን ኢመደበኛ መሆኑን ነው። መምህራን ለሚቀርቧቸውና አመኔታ ለሚጥሉባቸው ደቀ መዛሙርታቸው ኢመደበኛ በሆነ መንገድ አንድም በቃል አንድም በጽሑፍ ያስተላልፋሉ። በተለይም በብዛት እኩይ የሆኑ የጠልሰም ሥራ አይነቶች ተስተላልፎ ቃላዊ መሆኑንና ይህ እውቀት የሚተላለፍለት ደቀ መዝሙርም አስተዋይና ዕውቀቱን ለእኩይ ተግባር የማይጠቀምበት እንደሆነ የታመነበት መሆኑን ከሃሳቡ መረዳት ያቻላል። አሁን አሁን ግን ይህን እየሻሩና ዕውቀቱን ለእኩይ እየተጠቀሙ በሰዎች ላይ መንፈሳዊና አእምሯዊ ጉዳትን ጭምር የሚስከትሉ ጠልሳሚያን እንዳሉም መረጃ ሰጪዎቹ ጠቁመዋል። ምናልባትም የተልሰም ጥበብ መደበኛ በሆነ መንገድ ወንበር ተዘርግቶለትና ቀለም ተበጥብጦለት የሚሰጥ እውቀት ያልሆነውም በዚህ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ሆኖም ግን እኩይ የሆነውን ወደጎን ትቶ ሰናዩን ብቻ በማጉላት ጥበቡን ማሳደግና ማልጎልበት እንደሚገባ ማወቅ ያሻል።

## ምዕራፍ አምስት

### ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "የጠልሰም ባህላዊ ዕውቀትና መድኃኒትነት በጻታ ወረዳ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዓቢይ ዓላማም በጻታ ወረዳ የሚገኙ ጠልሰማዊ ሆኑ መድኃኒቶችን አሠራር እና ክዋኔ መመርመር ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካትም ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውለዋል። በእነዚህ መረጃ መሰብሰቢያዎች አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎችም በይዘት ተከፋፍለውና ተተንትነው ቀርበዋል። ከዚህ ረገድም የሚከተለው የማጠቃለያ ሃሳብ ላይ ተደርሷል።

የጥናቱ ተተኳሪ በሆነችው ፃታ ወረዳ ውስጥ ያሉ ማህበረሰቦች እንደ ሾተላይ፣ ዓይነ ጥላ (ሕጻናትን ገዳይ በሽታ)፣ ገርጋሪ፣ ዓይነ ወርቅ፣ ደም መፍሰስ፣ ማዕሰረ አጋንንት፣ መግረሬ ጸር፣ ዛር ማውገዣ፣ ዛር ማስታረቂያ፣ መፍትሔ ስራይ፣ መድፍነ ጸር እና መስጥመ አጋንንት ላሉ ከመንፈስ ጋር የተያያዙ ሕመሞች የሚሰጡ ጠልሰማዊ መድኃኒቶችን እንደሚጠቀሙ ማስተዋል ተችሏል። አንድ ታማሚ ሲመጣ ከላይ ከሰፈሩት ውስጥ በየትኛው ሕመም እንደተጠቃ ለመለየትም የተለያዩ መንገዶችን የሚጠቀሙ ሲሆን እንዲሁ በዓይ አይቶ መለየትና ዓውደ ነገስትን ገልጦ በማየት እጣ ክፍልን ለይቶ የሚደረግ ንባብም ዋነኛው ሕመም መለያ ዘዴ መሆኑን ከጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል።

ለእነዚህ ከላይ ለሰፈሩት ሕመሞች የሚውሉ መድኃኒትነት ያላቸውና መድኃኒትነት የሌላቸው እጽዋትን እንዳስፈላጊነታቸው ቀምሞ ቀለማትን በማዘጋጀትና የበግና የፍየል ብሎም የሚዳቋ ቆዳንም ጭምር በመጠቀም ብራና በማዘጋጀት ጠልሰማትን መስራት እንደሚቻል ጥናቱ አመላክቷል። ለመጠልሰሚያነት የሚውለውን የእንሰሳ ቆዳ እና ቀለም ለመምረጥና ጠልሳሚውን ሰው ለመጠቆም ኃላፊነት የሚሰጣቸው በአካባቢው የዚህ ጥበብ አዋቂ ተደርገው የሚታመንባቸው ሰዎች መሆናቸውንና እነዚህም ሰዎች ዓውደ ነገስት ገልጠውና ኮከብ ቆጥረው የታማሚውን እጣ ክፍል በማንበብ የመረጣ ሥራውን እንደሚከውኑ ለማስተዋል ተችሏል።

በዚህ መንገድ የተመረጠ ቆዳ ተልጎና ጸሎቶች ተጠልስመውበት ይቀርባል። ጠልሰም ህልው የሚሆነውና ፈዋሽነቱ በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲታመንበት የሚያደርጉትም በጠልሰሙ ላይ የሚጠለሰሙት የአምላክ ኅቡእ ስሞች እና ጸሎቶች የያዙት መለኮታዊ ሃይል ነው ተብሎ እንደሚታመንና ሁሉም ጸሎቶች መሰረታቸው ሃይማኖታዊ ተረኮች እና መጽሐፍት እንደሆኑም ጥናቱ አረጋግጧል። በጸሎቶቹ ውስጥ ከሚካተቱት አስማቶች በተጨማሪም ሕመሙን የሚያመጡትን መናፍስት የሚወክሉ ሥዕላትን (መናፍስቱን) መሳልም በጠልሰም የመድኃኒት ሥራ የተለመደ ሲሆን ይህ መደረጉ አንድም መንፈሱን ሥግው አድርጎ የማቅረብ ያህል ረቂቅ ጥበብ የተመላበት ክዋኔ መሆኑ አንድም ደግሞ ይህን ማድረጉ ታማሚው በሽታውን እንዳይፈራውና የመንፈስ ጭንቀት እንዳይጨነቅ የማድረግ ሥነ ልቡናዊ ሚና ጭምር እንዳለው ለማጤን ተችሏል። እንደ መድፍነ ጸር ላሉ መናፍስታዊ ሕመሞች በሚሰጡት ጠልሰሞች ላይ በሚጠለሰሙ አስማት እና ሥዕላት መካከልም አንድምታዊና ምሥጢራዊ ተዛምዶ እንዳለ ለማስተዋል ተችሏል። ከዚህም በመነሳት እልፎ እልፎ የሚጠለሰሙ ሥዕላት ከሕመሙ ጋር ተዛምዶ ያላቸው እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል። ሆኖም ግን ጠልሰምን ጠልሰም ሊያሰኘው የሚችለው በዋናነት ኃይል አዘል የሆኑት አስማት መሆናቸውና ምንም አይነት ሥዕል ባይካተትበትም ጠልሰም መሆኑን እንደማይሽረው በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በጻታ የሚከወነው ይህ የጠልሰም ጥበብ በቃል ብሎም በጽሑፍ ጭምር ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ እዚህ ቢደርስም አንዳንድ ጠልሳሚያን ዕውቀቱን ለእሉታዊ ተግባር በማዋላቸውና ማህበረሰቡም በዚህ ሳቢያ ጠልሳሚያኑን በመፍራቱና በመሸሹ ሳቢያ ይህ ጥበብ የሚጠበቅበትን ያህል ሊያድግ አለመቻሉን ጥናቱ አረጋግጧል። ከዚህ ባለፈም በጻታ ወረዳ የሚገኘው ይህ ዕውቀት በሀገር ደረጃ ወንበር ተዘርግቶለትና ብራና ተፍቆለት ሥርዓቱን በጠበቀና በተደራጀ ሁኔታ እምብዛም የማይሰጥ ይልቁንም ከአባት ወደ ልጅ፣ ከዘመድ ወደዘመድና ከመምህር ወደ ደቀመዝሙር ኢመደበኛ በሆነ መንገድ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ እዚህ የደረሰ እውቀት መሆኑንም በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል።

እነዚህን ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች ያጠናቀረው ይህ ጥናት ተግባራዊና ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳቦችን ማዕቀፍ በማድረግ የጻታ ማህበረሰብ የጠልሰም መድኃኒቶችን ለመጠቀም እስቦ ሲነሳ ከሚከውነው ሥርዓት ክዋኔ አንስቶ መድኃኒቱ ተጠልስሞ እስኪሰጠውና እስኪያጠልቀው ድረስ የሚያልፋቸውን ሥርዓት ክዋኔዎች ዳሷል። መድኃኒቱ የማህበረሰቡን የመንፈስ ሕመሞች የመፈወስ፣ የማህበረሰቡን ሥነ ልቡና ከመገንባትና እምነታዊና ባህላዊ ልማዶችን ከማጠንከር አንጻር ያለውን ማህበራዊ ፋይዳም አሳይቷል።

## ዋቢ ጽሑፎች


አቢሲኒካ መዝገበ ቃላት, አቢሲኒካ መዝገበ. አቢሲኒካ መዝገበ ቃላት. https://dictionery.abyssinica.com/ ጠልሰም, 2019.

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። መጽሐፈ፡ሰዋስው፡ወግስ፡ወመዝገበ፡ቃላት፡ሐዲስ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1948።

የጻታ ወረዳ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ሪፖርት፤ 2011።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። ዐዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፤ 1972።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት። አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም።

ዳንኤል ገድዮን መስፍን። የኢትዮጵያ አብነት ማንስክርፕቶች. ሀምቡርግ: ሀምቡርግ ዩኒቨርሲቲ, 2017።

ፈቃደ አዘዘ። የስነ-ቃል መምሪያ።. አዲስ አበባ፣ ቦሌ ፕርንቲንግ ኢንተርፕራይዝ፣ 1991።

ፍሥሐ ይሁን። ጥበበ ሐረግ። (ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ)፣ 2001።

Adrian P. and Bogdan B. "An Ethiopian Magical Manuscript at the University Library of Cluj, Romania." International Journal of African Historical Studies Vol. 45, No. 1 (2012) (2012): 103- 111.

Balicka-Witakowska, Ewa. “illustrating charms:a syriac manuscript with magic drawings in the collection” . UPPSALA: GoRGiaS pReSS, 2008.

Bouanga, A. Le Damot dans l’histoire de l’Ethiopie (XIIIe-XXesiècles): Recompositions religieuses, politiques et historiographiques. Paris : Paris i, Centre d’Etude des Mondes Africains (cemaf), 2013.

Boylston, T. The Shade of the Divine: Approaching the Sacred in an Ethiopian Orthodox Christian Community. London: London School of Economics. , 2012.

Derrillo, Eyob. "A handbook of Ethiopian magic incantations and talisman art ." 2017.

Dornyei, Z. (2007). *Research methods in Applied Linguistics*. New York: OUP.

Dawson, Catherine. (2002). *Practical research methods; A user friendly guide to Mastering research.* Magdalena Road, Oxford OX4 1RE. United Kingdom. How to books LTD.

Finnegan, Ruth. *Oral Poetry.* Cambridge: Cambridge university press, 1977.

Gidena, Mesfin Kebede. Ethiopian Abənnät Manuscripts: Organizational Structure, Language Use, and Orality. Hamburg: A dissertation submitted to the Faculty of Humanities of the University of Hamburg in partial fulfillment of the requirements for the degree of Doctor of Philosophy, 2017.

Graham, D. Lloyd. "The Magic Symbol Repertoire of Talismanic Rings from East andWestAfrica."ttps://www.academia.edu/7634962/The_Magic_Symbol_Repertoire_of_Talismanic_Rings_from_East_an (2014): v04_25.11.16.

Graham, Lloyd D. "In Islamic Talismans, Repeat-Letter Ciphers Representing the “Greatest Name” Relate to an Early Prototype of the Seven Seals and may Link the Seals with the Pleiades." Repeat-Letter Ciphers in Islamic Talismans፡ Epigraphic Society Occasional Papers (ESOP) (2011): 29, 70-91.

Gray, David. (2004). *Doing Research in the Real World*. London, Saga

Publication LTD.

Heidi Cutts, Lynne Harrison, Catherine Higgitt and Pippa Cruickshank. "The image revealed: study and conservation of a mid-nineteenth-century Ethiopian church painting." THE BRTISH MUSEUM: Techinical research Bulletin. 2010. 18.

Henze, P. Layers of Time: A History of Ethiopia. New York: Palgrave, 2000.

Hoskins, From. "Symbolism in Anthropology." International Encyclopedia of the Social & Behavioral Sciences, 2nd edition, Vol (2015 ): pp. 860–865.

Jon McGee & Richard L . Warms. ANTHROPOLOGICAL THEORY. San Marcos: Texas State University- San Marcos, 2008

Kebede, Gidena Mesfin. Ethiopian Abənnät Manuscripts: Organizational Structure, Language Use, and Orality. Hamburg, 2017.

Kothari, C.R. (2004). *Research Methodology: Method and Techniques*. New Delhi: New age International (P) Ltd, Publishers

Chernetsov, S. Ethiopian Magic Texts." Forum for Anthropology and Culture No.2 (2005): 189

Marcella A. Garcia probert and Hayat Ahlili. "Amulets and Telsmans in the Muslim world." First International Conferenace. 2016. 16.

Ménonville, Siena de. "In Search of the Debtera: An Intimate Narrative on Good and Evil in Ethiopia Today." Journal of Religion in Africa no 48 (2018): 105-144.

Munro-Hay, S. Ethiopia the Unknown Land: A cultural and historical guide. NewYork: I.B. Tauris and Co. Ltd., 2002.

Nosnitsin, Denis. "Deconstructing a manuscript collection: the case of Ara ero Takla Haymanot (Gulo Mak.ada, East T;)gray)." Alessandro Bausi, Alessandro Gori, and Denis Nosnitsin. Essays in Ethiopian Manuscript studies. Hamburg: Harrassowitz Verlag, 2014. 23- 55.

Sims, Martha and Martine Stephenes. *Living Folklore; an Introduction to The Study of People and Their Traditions.* Lagan Utah State University Press, 2005.

Spickard, James V. "A Guide to Mary Douglas's Three Versions of Grid/Group Theory." Sociological Analysis,Vol. 50, No. 2, Thematic Issue: A Durkheimian Miscellany፡ URL: https://www.jstor.org/stable/3710986 (1989): pp. 151-170.

Tamrat, Taddesse. 'Church and State in Ethiopia: The Early Centuries'. African Zion: The Sacred Art of Ethiopia. . New Haven, CT: Yale University Press., 1993.

Thomas A.green. *Folklore an encyclopedia of belefs, customs, tales, music And art*. England: Oxford. 1997.

Turner, Victor. Symbol studies. Annual Review of Anthropology 4,. Urbana: University of Illinois, Urbana, IL, 1975.

## አባሪዎች

### አባሪ አንድ፡- የቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዮች ስም | ዕድሜ | ጾታ | ሀይማኖት | መኖርያ ቦታ | መተዳደርያ ሥራ | ቃለመጠይቅ የተካሔደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አዕመረ ጸሐዩ | 45 | ወ | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ ቀበሌ | ጠልሳሚ | ሐምሌ 27-29/2012 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2. | መሪጌታ አፈወርቅ ነጋሽ | 52 | ወ | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ ቀበሌ | የአብነት መምህር እና ጠልሳሚ | ሐምሌ 27/2012 |
| 3. | ቄስ ደሳለኝ ገ/ሚካኤል | 63 | ወ | ኦርቶዶክስ | አርመር ቀበሌ | ጠልሳሚና የቅኔ መምህር | ሐምሌ 28/2012 |
| 4. | አቶ ገሰሰ ቢተው | 49 | ወ | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ ቀበሌ | አርሶአደር እና አዋቂ | ሐምሌ 25-27/2012 |
| 5. | አቶ ሸግነው ኪዴ | 48 | ወ | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ ቀበሌ | አርብቶአደር እና የንደር አዋቂ | ሐምሌ 27-ነሐሴ 02/2012 |
| 6. | ቄስ ኪሮስ አሰፋ | 51 | ወ | ኦርቶዶክስ | አርመር | የአብነት መምህርና ጠልሳሚ | ነሐሴ 27/2012 |

## አባሪ ሁለት፡- መድኃኒቱን የተጠቀሙ ህመምተኞች መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ ሰጪ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ሀይማኖት | መኖርያ ቦታ | መተዳደርያ ሥራ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ አለሚቱ ጫኔ | ሴ | 31 | ኦርቶዶክስ | አርመር ቀበሌ | የቤት እመቤት | ሐምሌ 3/2012 |
| 2. | ወ/ሮ ወርቅነሽ ንጉሱ | ሴ | 50 | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ ቀበሌ | ገበሬ ማህበር አባል | ነሐሴ 2/2012 |
| 3. | አቶ አድማሴ ወልዱ | ወ | 45 | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ ቀበሌ | አርሶአደር | ሐምሌ 29/2012 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4. | አቶ ጉብሩ አስራት | ወ | 47 | ኦርቶዶክስ | አርመር ቀበሌ | አርሶአደር | ነሐሴ 9/2012 |
| 5. | ወጣት አበባው ተበው | ወ | 39 | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ ቀበሌ | አርብቶአደር | ነሐሴ 11/2012 |
| 6. | ወ/ሮ ብልጫነሽ ተስፋዬ | ሴ | 32 | ኦርቶዶክስ | | የቤት እመቤት | ነሐሴ 7/2012 |
| 7. | ወ/ሮ አዳኑ ቸኮለ | ሴ | 28 | ኦርቶዶክስ | አርመር ቀበሌ | የቤት እመቤት | ሐምሌ 28/2012 |

## አባሪ ሶስት፡- የፃታ ወረዳን የሚመለከቱ መረጃዎችን የሰጡ የቢሮ ኃላፊዎችና የቀየው ነዋሪዎች መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ ሰጪ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ሀይማኖት | መኖርያ ቦታ | መተዳደርያ ሥራ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ክንድዬ ጫኔ | ወ | 44 | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ ቀበሌ | አርብቶአደር | ግንቦት 8/2013 |
| 2. | አቶ ቢተው ብሩ | ወ | 55 | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነቀ በሌ | አርሶአደር | ግንቦት 6/2013 |
| 3. | ቄስ እንዳለ አለልኝ | ወ | 36 | ኦርቶዶክስ | ጳግብጂ | የቤተክርስትያ | ግንቦት 12/2013 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ን አስተዳዳሪ | |
| 4. | አቶ አስራቴ ብርሃኑ | ወ | 62 | ኦርቶዶክስ | አርመር | የታሪክ አዋቂ | ግንቦት 12/2013 |
| 5. | አቶ ጌታወይ ሽመይ | ወ | 47 | ኦርቶዶክስ | ዳግብጂ | ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ | ግንቦት 5/3013 |
| 6. | አቶ ብርሃኑ አማረ | ወ | 46 | ኦርቶዶክስ | ዳምትኩነ | ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ | ግንቦት 9/3013 |
| 7. | አቶ በላይ ገ/ኪዳን | ወ | 39 | ኦርቶዶክስ | ዳግብጂ | የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ | ግንቦት 7/2013 |

**አባሪ አራት፦ ለቁልፍ መረጃ ሰጪዎች (ለጠልሳሚዎችና አዋቂዎች) የቀረበ የመስክ ምልከታ ጥያቄዎች ቅጽ**

- የመረጃ ሰጪ ማንነትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች
    1. የመረጃ ሰጪ ስም
    2. ዕድሜ
    3. ጾታ
    4. መኖርያ ቦታ
    5. መተዳደርያ ሥራ

- ጠልሰምን የተመለከቱ ጥያቄዎች

6. ጠልሰም ምንድን ነው?
7. ጠልሰምን ለማዘጋጀት ምን ምን ግብዓቶች ያስፈልጋሉ?
8. ለጠልሰም የሚሆኑ ግብዓቶች እንዴት ይዘጋጃሉ?
9. ሥንት ዓይነት የመልሰም ዓይነቶች አሉ? ስማቸው እና በእያንዳንዳቸው መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
10. በዚህ በጻታ አካባቢ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ሕመሞች ምን ምን ናቸው?
11. በዚህ አካባቢ ሰዎች ከምን ከምን ሕመሞች ለመፈወስ ወደ እናንተ ይመጣሉ?
12. አንድ ሰው ሕመም ተሰምቶት ሲመጣ የታመመው ምን እንደሆነ የምትለዩት በምን መንገድ ነው?
13. ሕመሙን ከለያችሁ በኋላ ቀጣይ የምታደርጉት ነገር ምንድን ነው?
14. ለሾተላይ የሚሰጥ ጠልሰም እንደምን ያለ ነው? በምን ዓይነት አኳኋንስ ይሰጣል?
15. ለዓይነ ጥላ እና ለገርጋሪ የሚሰጥ ጠልሰምስ ጸሎትና ትርጓሜ እንዲሁም የአሰጣጥ ሥርዓት ክዋኔ ምንድን ነው?
16. ደመ ከቲር ምንድን ነው? ለምን ዓይነት ሕመምተኛ ነው የሚሰጠው?
17. የደመ ከቲር ጸሎትና አሰጣጡ እንዴት ነው?
18. ለመግረሬ ጸርና መድፍነ ጸር የሚጠለሰም ጠልሰም ምን ዓይነት ነው? በጠልሰሙ ላይ የሚሰፍለው ሥዕል ትርጓሜ ምንድን ነው?
19. ለመፍትሔ ሥራይ እና ለማእሰረ አጋንንት የሚሰራ ጠልሰም እንዴት ይዘጋጃል? ሥርዓተ ክዋኔውስ እንደምን ያለ ነው?
20. ጠልሰም የሚጠለሰምበት ቀንና ሰዓት ልዩነት አለው ወይ? ወይስ በማንኛውም ጊዜና ሰዓት መዘጋጀት ይችላል?
21. እርሶ ይህን እውቀት እና ጥበብ እንዴት ባለ መንገድ አገኙት?
22. ለዚህ ሀገረሰባዊ እውቀት የዚህ አካባቢ ማህበረሰብ ምን ዓይነት አመለካከት አለው?

## አባሪ አምስት፡- ለሕመምተኞች (ለጠልሰም መድኃኒት ተጠቃሚዎች) የቀረበ ጥያቄ ቅጽ

1. ሥምህ/ሽ ማን ይባላል?

2. ዕድሜህ/ሽ ስንት ነው?
3. ጠልሰም ለማሰራ የመጣሽው እንዴት ነው (በሰው ጥቆማ፣ በራስ ዕውቀት፣ ከየት…)?
4. ሕመምህ/ሽ ምንድን ነው?
5. ሕመሙ እንዴት ዓይነት ስሜት ነበረው?
6. ምን ዓይነት የጠልሰም መድኃኒት ተሰጠህ/ሽ?
7. ከመድሃኒቱ በፊትና መድኃኒቱን ከወሰድህ/ሽ በኋላ ያለው ለውጥ ምንድን ነው?

## አባሪ ስድስት፡- የፎቶ ማስረጃዎች





መሪጌታ አፈወርቅ በጠልሰም ሥራ ላይ
እያሉ (ነሐሴ 28/2012)

መሪጌታ አፈወርቅ ለአጥኚዋ
የጠልሰምን አጠለሳሰም በማሳየት ላይ
(ነሐሴ 28/2012)



መሪጌታ አፈወርቅ ለአጥኚዋ መረጃ በመስጠት ላይ (ነሐሴ 28/2012)





የሾተላይ ሕመም የቁምክታብ

(ነሐሴ 29/2012)

የመግረሬ ጾር ጠልሰም (ነሐሴ 29/2012)



ቄስ ኪሮስ ለአጥኚዋ መረጃ በመስጠት ላይ እያሉ (ሐምሌ 7/2012)



የመግረሬ ጾር ጠልሰም (ሐምሌ 8/2012)